# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 121 ጥር 1 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ፎቶ - ኢዩብ ተፈሪ

አቶ ሚሊዮን ማትዮስ

## ኢትዮጵያ በቀጣዮቹ ስድስት ዓመታት 510 ሺህ ኪሎ ግራም ወርቅ ለማምረት እየሰራች ነው

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በሚቀጥሉት ስድስት ዓመታት 510ሺ ኪሎ ግራም ወርቅ ለማምረት እየሰራች መሆኑ ተገለጸ።

የማዕድን ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሚሊዮን ማትዮስ በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ኢትዮጵያ በሚቀጥሉት ስድስት ዓመታት ከ510ሺ ኪሎ ግራም የማያንስ ወርቅ በኩባንያ ደረጃ ይመረታል።

ይህን ሥራ የሚያከናውኑ ኩባንያዎችም በቅርቡ ሥራ ይጀምራሉ ያሉት አቶ ሚሊዮን፤ ለአብነትም ጋምቤላ ያለው ኢትዮ ማይንስ በሦስት ወራት ወደ ሥራ እንደሚገባና በቤንሻንጉል ያለው ኩርሙክ የወርቅ ኩባንያ በአምስት ዓመታት ውስጥም ወደ ምርት ይገባል ብለዋል።

በሌላ በኩል በአሁኑ ወቅት ያሉት ብረት ፋብሪካዎች ከ30 እስከ 40 የሚደርሱ መሆናቸውንና እነዚህ በሙሉ

ኢትዮጵያ በቀጣዮቹ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የሀብት ብክነትን ለመከላከል የግዢ ሥርዓት ላይ በትኩረት መስራት ይገባል

ታደሰ ብናልፈው

አዲስ አበባ፡- ለግዥ የሚውለው የሀገሪቱ 70 በመቶ በጀትን ከሙስና ለማዳን ግልፅ አሠራር ሊዘረጋ ይገባል ሲሉ የፓን አፍሪካ የንግድ ምክር ቤት ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ክቡር ገና ገለጹ።

የፓን አፍሪካ የንግድ ምክር ቤት ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ክቡር ገና ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከአጠቃላይ የሀገሪቱ በጀት 70 በመቶው የሚሆነው ለግዥ የሚውል ትልቅ በጀት ነው። ይህን በጀት ከሙስና መጠበቅ እንዲቻል ግልጽ የሆነ አሠራር ሊዘረጋ ይገባል።

ዋና ሥራ አስፈፃሚው፣ ሙስና የሚስፋፋው ግልጽ

የሀብት ብክነትን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ክቡር ገና

## ኢኮኖሚውን እያመሰ ያለው ደላልነት

ገጽ 4

## መንግስት በጦርነት ለተጎዱ አካባቢዎች የህክምና ግብአቶችን እያሟላ ነው

መስከረም ሰይፉ

አዲስ አበባ፡- መንግሥት በጦርነት የተጎዱ የጤና ተቋማት ለህብረተሰቡ ዳግም መሰረታዊ የህክምና አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ የህክምና ግብአቶችን እያሟላ እንደሚገኝ ጤና ሚኒስቴር ገለጸ።

በጤና ሚኒስቴር የህክምናው መሳሪያዎችና ግብአቶች ዳይሬክተር አቶ ረጋሳ በይሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ባለፉት ሁለት ዓመታት በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል በተካሄደው ጦርነት በርካታ የጤና ተቋማት ጉዳት ደርሶባቸዋል። በአሁኑ ጊዜም እነዚህ የጤና ተቋማት

መንግስት በጦርነት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ

ፀደይ ባንክ (አ.ማ) TSEDEY BANK (S.C)

የሁሉም ባንክ Bank for all !

የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !

በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia

eccs

የኢትዮጵያ የግንባታ ግብዓቶች አቅራቢ
ETHIOPIAN CONSTRUCTION COMMODITIES SUPPLY PLC.
የአርማታ ብረት እና ሌሎች ብረታብረቶች አከፋፋይ

Mob. 0911 225057/ 0989 343434
አድራሻ፡ ከሜክሲኮ አደባባይ ወደ መርካቶ በሚወስደው መንገድ ከዲ-አፍሪክ ሆቴል ፊት ለፊት

ኩሊ የእቃ አስተላላፊ

ማሸግ እና ማጓጓዝ

- የቤትና የቢሮ እቃዎችን የማሸግና የማጓጓዝ አገልግሎት
- በአደራ ተቀብሎ የማድረስ
- ለገቢና ወጪ እቃዎች የጉምሩክ /ትራንዚት አገልግሎት መስጠት።
- እቃዎችን እንልካለን ከውጭ የተላከሎትንም እንቀበላለን።
- ከአዲስ አበባ ወደ ክልሎች ከክልሎች ወደ አዲስ አበባ

0911010315
0930807777
0930907777
www.kulilogistic.com
melaku.bkl@gmail.com

ጉርድ ሾላ ተስፋዬ ወርቁ ህንፃ 1ኛ ፎቅ

ethio telecom

ቴሌብር telebirr

እንኳን ለብርሀነ ልደቱ በሰላም አደረሳችሁ!

አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
ADAMA STEEL FACTORY

ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር

0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565

VISIT OROMIA
LAND OF DIVERSE BEAUTY

OROMIA TOURISM COMMISSION
JOIN US ON
https://linktr.ee/visitoromia.org



አቶ ኡሞድ ኡጁሉ

# በጋምቤላ ክልል የተቋቋመው የፀረ ሙስና ኮሚቴ ወደ ስራ ገብቷል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ጋምቤላ፡- በጋምቤላ ክልል የተቋቋመው የፀረ ሙስና ኮሚቴ የሙስና ምንጭ ናቸው ተብለው በተለዩ ጉዳዮች ላይ እቅድ አዘጋጅቶ ወደ ስራ መግባቱ ተገለጸ።

በክልሉ የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴውን አጠናክሮ ለማስቀጠል ሰባት አባላት ያሉት ኮሚቴ ተቋቁሞ ወደ ስራ መገባቱን የገለጹት የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኡሞድ ኡጁሉ ናቸው።

በክልሉ በተለይም የአገልግሎት አሰጣጥን ጨምሮ በሌሎች ዘርፎች ውስብስብ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ችግሮች መኖራቸውን ጠቁመው፤ ኮሚቴውም የሙስና ወንጀሎች ምንጭ ናቸው ያላቸውን ጉዳዮች በመለየት እቅድ ነድፎ ወደ ስራ መግባቱን አስታውቀዋል።

ሙስና የሀገር ህልውና አደጋ በመሆኑ መላው የክልሉ ማህበረሰብ ከመንግስትና ከኮሚቴው ጎን በመሰለፍ የሚጠበቅበትን የዜግነት ኃላፊነት እንዲወጣም ርዕሰ መስተዳድሩ ጥሪ አቅርበዋል።

የክልሉ ፍትህ ቢሮና የኮሚቴው ሰብሳቢ አቶ አኳይ አቡቲ በበኩላቸው፤ ኮሚቴው ከተቋቋመ የአንድ ወር እድሜ ያለው ቢሆንም የተለያዩ ስራዎች ማከናወኑን ተናግረዋል።

ለስራው የሚያግዙትን በስሩ የመከላከል፣ የምርመራና የክስ ንዑሳን ኮሚቴዎችን በማቋቋም ወደ ስራ መግባቱን ለአብነት በማንሳት።

ኮሚቴው በክልሉ ለሙስናና ብልሹ አሰራሮች ምንጭ ናቸው ብሎ የለያቸውን የመሬት አስተዳደር፣ የንግድ፣ የገቢ አሰባሰብ፣ የህሰተኛ ትምህርት ማስረጃዎችና ሌሎች ዘርፎችን በመለየት እቅድ አዘጋጅቶ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ መግባቱን ገልጸዋል።

በእስካሁኑ ሂደትም ሶስት ጥቆማዎች ቀርበው በንዑሳን ኮሚቴው የማጣራትና የምርምራ ስራ እየተካሄደ መሆኑን ጠቁመው፤ ለኮሚቴው ስራ መቃናት የሁሉም አካላት ድጋፍና ትብብር ሊጠናከር እንደሚገባ አመላክተዋል።

# ዩኒቨርሲቲው የቡናና ቅመማ ቅመም የምርትና ጥራት ችግሮችን የሚፈታ ተቋም አቋቋመ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

ሚዛን አማን፡- የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ በቤንች ሸኮ ዞን የቡና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚረዳና የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል የቡናና ቅመማ ቅመም ምርምርና ልማት ተቋም መመስረቱን አስታወቀ።

የዩኒቨርሲቲው የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር አብዮት አስረስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ ዩኒቨርሲቲው የቡናና ቅመማ ቅመም ምርምርና ልማት ተቋምን ያቋቋመው የዘርፉን ልማት ለማስፋፋት መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህ እንዲሆን ለማስቻል የቴክኖሎጂና የተጠናከረ የኤክስቴንሽን አገልግሎት እንደሚሰጥና ጥራት ያለው ምርት እና ምርታማነትን በማሳደግ ከዘርፉ የሚገኘውን ጥቅም በላቀ ደረጃ ለማሳደግ እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

የገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂን መሠረት በማድረግ አርሶ አደሩ ገበያ መር የቡናና ቅመማ ቅመም ምርት እንዲያመርት ጥራቱ የተጠበቀ የኤክስፖርት ምርት በብዛት እንዲቀርብ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑም የቡናና ቅመማ ቅመም ምርምርና ልማት ተቋም ተመስርቷል ሲሉ አክለዋል።

የተመሰረተው ተቋም የቡና ምርት እያጋጠመው ያለውን ችግር ለመቅረፍና ለዓለም አቀፍ ገበያ የሚመጥን ቡና ለማቅረብ ጉልህ ሚና አለው ያሉት ዶክተር አብዮት፤ የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ በአካባቢው ያለውን የአመራረት፣ የዘርና የክሂሎት ችግርን ለመቅረፍ እየሠራ መሆኑን አንስተዋል።

እንደ ዶክተር አብዮት ገለፃ፣ የሀገሪቱ ዩኒቨርሲቲዎችና የምርምር ማዕከላት ዘርፉን በጥናትና ምርምር ማገዝና ከማህበረሰቡ ጋር በቅንጅት መሥራት አለባቸው። የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲም በዘርፉ የሚታየውን ችግር ለመቅረፍ በሚደረገው ርብርብ ለዞኑ ቡና አብቃይ አካባቢዎች ከፍተኛ ድጋፍ ለማድረግ ዝግጅቱን በማጠናቀቅ ላይ ነው።

አርሶ አደሩ ተለምዷዊ አሠራርን ተከትሎ በማምረቱና በጥናትና ምርምር የተደገፈ ምርጥ ተሞክሮ ማስፋፋት ባለመቻሉ ተጠቃሚነቱ እምብዛም ሆኖ መቆየቱን የተናገሩት ዶክተሩ፣ የተመሰረተው ተቋም በአካባቢው ከፍተኛ የሆነ የቡና ምርት እንዲኖር እንደሚያደርግ ገልጸዋል።

የሀገራችን ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት የሆነው የቡና ምርት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ከማስገኘት ባለፈ 25 በመቶ ለሚሆነው ህዝብ የኑሮ መሠረት እንደመሆኑ መጠን ከልማት ሰራተኛው እስከ ቡና አሰባሰብ ደረጃ ድረስ ያለውን የምርትና ምርታማነት ማነቆዎችን የመለየት ሥራ መስራት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

ተቋሙ በዋናነት የምርትና ምርታማነት ማነቆችን ለይቶና በጥናት አስደግፎ ምርቱ በስፋት ወደ ገበያ እንዲወጣና ጥራቱን የጠበቀ ቡና ለዓለም ገበያ እንዲቀርብ ከዓለም አቀፍ ተቋማትና ሀገር ውስጥ ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመሆን የሚሠራ ነው።

በዚህም የቡናና ቅመማ ቅመም ዝርያዎችን በመለየት በአካባቢው ምርትና ምርታማነትን በሚፈለገው መጠን ለማሳደግ ተቋሙ ጉልህ ሚና እንደሚኖረውም ይጠበቃል።

የቤንች ሸኮ ዞንን የቡና ምርትና ምርታማነትን ከማሳደግ አኳያ ዩኒቨርሲቲው በርካታ ሥራዎችን እየሠራ ነው ያሉት ዶክተር አብዮት፤ ቡና በዚህ አካባቢ ትልቅ ጸጋ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው ለብቻው የቡናና ቅመማ ቅመም ምርምርና ልማት ተቋም አቋቁሟል ብለዋል።



# ዘመናዊ የሴቶች የተሃድሶና ክህሎት ማበልጸጊያ ማዕከል ሊገነባ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ዘመናዊ የሴቶች የተሃድሶ እና የክህሎት ማበልጸጊያ ማዕከል ፕሮጀክት ግንባታ በትናንትናው ዕለት በአዲስ አበባ አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ተጀምሯል።

በማስጀመሪያ መርሐ-ግብሩ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ እና ሌሎች ከፍተኛ አመራሮች ተገኝተዋል።

ከንቲባ አዳነች በማህበረሰቡ ውስጥ በሚስተዋሉ ችግሮች ምክንያት ኑሯቸውን ጎዳና ላይ ላደረጉ እና ያለ ፍላጎታቸው ለወሲብ ንግድ የተዳረጉ ሴት እህቶች ላይ ከመፍረድ ይልቅ ሁላችንም ተባብረን ህይወታቸውን እንዲለውጡ መስራት ይገባል ብለዋል።

በ 3 ነጥብ 1 ቢሊየን ብር የሚገነባው ፕሮጀክቱ ፣ ከ400 በላይ ለሚሆኑ የጎዳና ተዳዳሪዎች እና ሴቶች የስራ ዕድል እንደሚፈጥር ተገልጿል።

ፕሮጀክቱ በ5 ነጥብ 1 ሄክታር መሬት ላይ የሚያርፍ ሲሆን፤ በውስጡ የስልጠና አዳራሾች፣ ማደሪያዎች ክፍሎች፣ መዝናኛ እና የገበያ አዳራሽ እንደሚኖሩት ተጠቁሟል።

ማዕከሉ በአንድ ጊዜ ለ2 ሺህ ሴቶች በ9 የተለያዩ ዘርፎች ስልጠና የመስጠት አቅም ያለው እንዲሁም በዓመት ለ10 ሺህ ሴቶች የሙያ እና የስነ ልቦና ስልጠና በመስጠት እና በማብቃት በሀገር ውስጥ እና በውጭ የስራ ስምሪቶችን ይሰጣል ተብሏል።

ከንቲባ አዳነች ጎዳና ላይ ኑሯቸውን ላደረጉ፣ በወሲብ ንግድ ላይ የተሰማሩ፣ አካል ጉዳተኞችን፣ አቅመ ደካሞች እና ድጋፍ የሚሹ ሴቶችን የሚረዱ የሀገር ውስጥና የውጭ ድርጅቶች እና ግለሰቦችን አመስግነዋል።

# ከጦርነት ያገገመችው ኮምቦልቻ 53 ቢሊዮን ብር ኢንቨስትመንት እየተካሄደባት ነው

## - 200 ሄክታር መሬት ለኢንዱስትሪ ተዘጋጅቷል

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

ኮምቦልቻ፡- በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል በነበረው ጦርነት ኢንዱስትሪዎቿ ጉዳት አጋጥሟቸው የነበረችው ኮምቦልቻ ከተማ በአሁኑ ወቅት 53 ቢሊዮን ብር ኢንቨስትመንት እየተካሄደባት መሆኑን የከተማ አስተዳደሩ ገለፀ።

የኮምቦልቻ ሪጂኦ ፖሊቲያን ከተማ አስተዳደር ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት መምሪያ ኃላፊ አቶ ሐብታሙ ኃይሌ በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ በከተማዋ ትልቅ የኢንቨስትመንት ፍሠት መኖሩን ጠቁመው፤ በአሁኑ ወቅት 53 ቢሊዮን ብር ኢንቨስትመንት እየተካሄደባት ነው። በክልሉ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ከሚካሄድባቸው አካባቢዎች ቀዳሚዎቹ ውስጥ አንዷ መሆኗንና በአሁኑ ወቅትም የቀድሞዋ እንቅስቃሴ ተጠናክሮ ቀጥሏል።

እንደ አቶ ሐብታሙ ገለፃ፤ በአሁኑ ወቅት በኮምቦልቻ ከተማ 131 አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚገኙ ሲሆን፤ 84ቱ በአነስተኛ አምራች ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ናቸው። ቀሪዎቹ ደግሞ በመካከለኛ እና ከፍተኛ አምራችነት ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ ደግሞ 44 ከመቶ የሚሆኑት ኢንዱስትሪዎች በማኑፋክቸሪንግ የተሰማሩ ናቸው።

በአሁኑ ወቅት 53 ቢሊዮን ብር የሚገመት መዕዋለ ንዋይ ያፈሰሱ ባለሀብቶች በከተማዋ እየተንቀሳቀሱ ሲሆን 8ሺ 200 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል ተፈጥሯል። ሁሉም ወደ ሥራ ሲገቡ ደግሞ የሥራ ዕድል ፈጠራውና የኢንቨስትመንት ካፒታል በብዙ እጥፍ እንደሚልቅ ጠቁመዋል።

መምሪያ ኃላፊው እንዳሉት፤ ከተማዋን ለኢንቨስትመንት ተመራጭ ካደረጓት ምክንያቶች መካከልም አዳጊ የመሰረተ ልማት ዕድሎች መኖራቸው



አቶ ሐብታሙ ኃይሌ

አንዱ ሲሆን፤ ከ100 ሜትር እስከ 150 ሜትር ድረስ ተቆፍሮ ተስማሚ ውሃ ይገኛል። በአሁኑ ወቅት ደግሞ 400 ሚሊዮን ብር ተጨማሪ የውሃ ፕሮጀክት እየተገነባ ነው።

ኮምቦልቻ-ወልዲያ- ሃራ ገበያ ያለው የባቡር ፕሮጀክትም በትራንስፖርት ዘርፍ ትልቅ በረከት የሚያመጣ ሲሆን፤ የአውሮፕላን በረራን ጨምሮ ሌሎች ምቹ የትራንስፖርት አገልግሎት መኖሩ ሌላው ምቹ ሁኔታ ነው። በዓመት 50 ቢሊዮን ብር ያላነሳ የገንዘብ ዝውውር የሚያስተናግድ የደረቅ ወደብም አገልግሎትም በኮምቦልቻ መኖሩ የአልሚዎችን ትኩረት እየሳበ ነው።

ኮምቦልቻ ከተማ ከጅቡቲ በአማካይ ከ480 እስከ 500 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ ሲሆን፤ ለአዲስ አበባ እና ለክልሉ ዋና ከተማ ባህርዳር በአማካይ ከ300 እስከ 400 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ መገኘቷ ማዕከላዊና ተመራጭ እንድትሆን አድርገዋታል። በአካባቢውም ኢንዱስትሪን ተቀብሎ የማስተናገድ ባህል የቆየ መሆኑና ማህበረሰቡም ተባባሪ መሆኑ ሌላው አመቺ ሁኔታ መሆኑን አቶ ሐብታሙ አብራርተዋል።

እንደ አቶ ሐብታሙ ገለጻ፤ በአካባቢው ለ37 ቀናት የተካሄደው ጦርነት የ10 ቢሊዮን ብር ኪሣራ አድርሷል። የሕወሓት ኃይሎች በኮምቦልቻ በሚገኙ በኢንዱስትሪዎችና አምራች ፕሮጀክቶች ላይ ዝርፊያ አካሂዷል። ጥሬ ግብዓቶች ለዘረፋ፣ ውድመት እና ብልሽት ተዳርገዋል። ይሁንና አሁን ባለው የሰላም ሁኔታ በርካቶች ወደ ሥራ እየተመለሱ ሲሆን 35 የሚሆኑት ኢንዱስትሪዎች ስራ ጀምረዋል፤ ቀሪዎቹ ደግሞ ወደ ሥራ ለመመለስ እንቅስቃሴ ጀምረዋል። ከባድ ውድመት የደረሰባቸውና አገግመው ወደ ሥራ ያልገቡ ስምንት ኢንዱስትሪዎች ደግሞ ከባንኮች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት አድርገው ወደ ሥራ የሚመለሱበት ዕድል እየተመቻቸ ነው።

በአሁኑ ወቅት በከተማና ከተማዋ ዙሪያ በኢንቨስትመንት ለመሠማራት ከፍተኛ ጥያቄ መኖሩን የተናገሩት አቶ ሐብታሙ፤ ጥያቄዎቹን ለማስተናገድም ከተማ አስተዳደሩ ካሣ በወቅቱ በመክፈል ለኢንዱስትሪ የሚሆን 200 ሄክታር መሬት ርክክብ ተፈጽሟል ብለዋል። የተሻለ አቅም ያላቸውና ለከተማዋ፣ ለክልሉና ለሀገር ፋይዳ ያላቸውን አካላት ወደ ሥራ የማስገባት ሂደትና አሠራር መኖሩንም አመልክተዋል።

ምንም እንኳ እነዚህ ሁሉ አምራቾች ቢኖሩም ለኢንዱስትሪዎች ከፍተኛ የብድር እጥረት መኖሩና ብድር በወቅቱ አለመገኘት፤ የጥሬ ዕቃ አቅርቦት አለመኖር፣ የውጭ ምንዛሪ እጥረት መኖር በሥራ ላይ ተጽዕኖ እየፈጠረ መሆኑንም አቶ ሐብታሙ አረጋግጠዋል።



ወይዘሮ ሰላማዊት ዳዊት

# የሰላም ስምምነቱ ቱሪዝሙን በዓለም አቀፍ ደረጃ ይበልጥ ለማስተዋወቅ መንገድ ከፍቷል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ የተደረገው የሰላም ስምምነት የኢትዮጵያን የቱሪዝም ዘርፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ በይበልጥ እንዲተዋወቅና እንዲነቃቃ መንገድ የከፈተ መሆኑን የቱሪዝም ሚኒስቴር አስታወቀ።

የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ እና የማስታወቂያና ገበያ ልማት ዘርፍ ተጠሪ ወይዘሮ ሰላማዊት ዳዊት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ የሰላም ስምምነቱ ከቱሪዝም ጋር በተያያዘ ከዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ጋር ላለው ግንኙነት መልካም መስተጋብርን ፈጥሯል።

በኮቪድ-19 እና በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት በቱሪዝም ዘርፉ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሮ ነበር ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ችግሮቹ በመቃለላቸው ቱሪስት ለመሳብ የሚረዱ የተለያዩ ዘመቻዎች በስፋት እየተከናወኑ መሆኑን ጠቁመዋል።

ከሰላም ስምምነቱ በኋላ በርካታ የውጭ ጎብኚዎች ወደኢትዮጵያ እንዲመጡ የተጠናከረ ስራ እየተከናወነ ይገኛል። በዲጂታል ሚዲያ፣ ዲያስፖራውን እንዲሁም የውጭ ሀገር አስጎብኚዎችን በመጠቀም የቱሪስት ፍሰቱን ለማሳደግና ኢትዮጵያ በቱሪዝም ዘርፉ በዓለም አቀፍ ደረጃ ይበልጥ እንድትታወቅ ጥረት እየተደረገ ነው ብለዋል።

ከሀምሌ ወር 2014 ዓ.ም እስከ መስከረም 2015 ዓ.ም በሶስት ወራት ከ230 ሺ በላይ የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ወደኢትዮጵያ መጥተው ጎብኝተዋል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ከሰላም ስምምነቱ ወዲህ የቱሪስት ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል ብለዋል።

እንደ ወይዘሮ ሰላማዊት ገለጻ በአሁኑ ሰዓት የቱሪዝም ሴክተሩ ከፍተኛ መነቃቃት እየታየበት ነው። የሀገር ውስጥ የቱሪስት ፍሰቱ ካለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የአስር በመቶ ዕድገት አሳይቷል።

በቀጣይም የተሻለ ዕድገት እንዲመጣ ጠንካራ ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛል። በተለይ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር በጋራ በሚከናወኑ ስራዎች፣ በዓለም አቀፍ ትልልቅ መገናኛ ብዙሃን አማካኝነት የማስታወቂያ ስራዎች እንደሚሰሩ ጠቁመዋል።

በተጨማሪ "ልወቅሽ ኢትዮጵያ" የተሰኘ የቱሪዝም እንቅስቃሴ በማከናወን እንዲሁም አክሱምንና ሌሎች ቅርሶችን ዳግም የማስተዋወቅ ዘመቻ በሀገር ውስጥና በውጪ አገራት እየተከናወኑ መሆኑን ገልጸዋል።

ከሰላም ስምምነቱ በኋላ መሰረተ-ልማቶች ተቋርጦባቸው በነበሩ አካባቢዎች የተከናወኑ የጥገና ስራዎች እንዳሉ ሁሉ በቱሪዝም ዘርፉም የቱሪስት መዳረሻዎች ላይ አገልግሎቶችን የማሟላት ስራ እየተከናወነ ይገኛል። የሆቴል ዘርፉ እንዲነቃቃና ተቋርጠው የቆዩ የቱሪስት መዳረሻ አገልግሎቶች ዳግም ስራ እንዲጀምሩ ጥረት ተደርጓል ብለዋል።

በቀጣይም ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ስለኢትዮጵያ የቱሪስት መስህቦች በቀላል መንገድ መረጃ የሚያገኙበትና ኢትዮጵያን የሚያውቁበት የሞባይል መተግበሪያ ከአጋር አካላት ጋር በመሆን የማበልፀግ ስራ እየተከናወነ መሆኑን አስታውቀዋል።

የቱሪዝም ዘርፉን ለማዘመን ባለፈው ሳምንት ኢትዮጵያን እንጎብኝ (visit Ethiopia) የተሰኘ የሞባይል መተግበሪያ ከልዩ ልዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ወደስራ መግባቱንና የጉዞ ማበረታቻዎች መደረጋቸውን አስታውቀዋል።

# የተማሪዎችን ክህሎት የሚያሳድጉ ሥልጠናዎችን በዲጂታል ማዕከላት ለመስጠት የሚያስችል ስምምነት ተፈረመ

**ታደሰ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮ ቴሌኮም የዲጂታል መማሪያ ማዕከላትን በመጠቀም የተማሪዎችን ክህሎት የሚያሳድጉ ስልጠናዎችን ለመስጠት የሚያስችል የአጋርነት ስምምነት ከጌትፋክት ኢትዮጵያ ጋር ተፈራረመ።

የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይዘሪት ፍሬህይወት ታምሩ በስምምነቱ ወቅት እንደተናገሩት፤ የቴክኖሎጂ አቅም አሟጦ በመጠቀም ኢትዮጵያ ወደ ዲጂታል ኢኮኖሚ የምታደርገውን ጉዞ በማጠናከር ጥራት ያለው ትምህርት ተደራሽ ለማድረግ ሲሠራ ቆይቷል። በዚህ እንቅስቃሴ መሰረትም ኢትዮ ቴሌኮም ከጌትፋክት ኢትዮጵያ ጋር የዲጂታል መማሪያ ማዕከላትን በመጠቀም የተማሪዎችን ክህሎት የሚያሳድጉ ስልጠናዎችን ለመስጠት የሚያስችል የአጋርነት ስምምነት ለመፈራረም በቅቷል።

ተቋሙ ተቀማጭነቱን አሜሪካ ሀገር ካደረገው ከጌትፋክት ኢትዮጵያ ድርጅት ጋር ያደረገው ስምምነት የዲጂታል መማሪያ ማዕከላትን በጋራ በመጠቀም የተለያዩ ሥልጠናዎችን ለከፍተኛና ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በትብብር ለመስጠት የሚያስችል መሆኑንም አብራርተዋል።

ከዚህ በፊት ባቋቋማቸው የዲጂታል መማሪያ ማዕከላት ሥልጠናውን በተደራጀ መንገድ ለመስጠት የሚያስፈልጉ ሙያዊ እና የቴክኖሎጂ እገዛ በማሟላት ሥልጠናዎቹ በቨርቹዋል እና በአካል እንዲሰጡ ድጋፍ እንደሚያደርግ ተናግረዋል።

በተጨማሪም የትብብር ስምምነቱ ለዲጂታል መማሪያ ማዕከላቱ የሚያስፈልጉ የዲጂታል የትምህርት ግብአቶች የማሟላት፣ የኃይል አቅርቦት አማራጮችን የማቅረብ እንዲሁም አስፈላጊ ቁሳቁሶችን በማሟላት



ወይዘሪት ፍሬህይወት ታምሩ

ዙሪያ በትብብር ለመሥራት የሚያስችል እንደሆነ ገልጸዋል።

እንደዚህ ዓይነት ስምምነቶች ተግባራዊ መደረጋቸውም በተለያዩ የዓለም ሀገራት የሚኖሩ አትዮጵያውያን ሀገራቸውን በገንዘብ፣ በዕውቀትና በጉልበት ለማገልገል እንዲሁም ዕውቀታቸውን ለዜጎቻቸው ለማካፈል ለሚፈልጉ ዕድል የሚፈጥር መሆኑን ጠቁመዋል።

በናሳ የጠፈር ምርምር ማዕከል ተመራማሪ እና የጌትፋክት ተቋም መስራች ዶክተር ብርሃኑ ቡልቻ በበኩላቸው፤ ስምምነቱ ሀገር ተረካቢ ወጣቶችን በዕውቀት ለመገንባት የዲያስፖራውን ማኅበረሰብ በማስተባበር በተለያዩ ጊዜያት የሚጠናቀቁ አጫጭር ሥልጠናዎች መዘጋጀታቸውን አስታውቀዋል። ሥልጠናዎቹ ለውጥ የሚያመጣ ተግባቦትና ለአመራር ብቁ የሆነ ጥልቅ አስተሳሰብ ያላቸው ወጣቶችን ለመፍጠር የሚያስችሉ መሆናቸውንም አብራርተዋል።

በተጨማሪም የኮምፒውተር ፕሮግራሚንግ ሥልጠናዎችን በመስጠት ሀገራቸውን የሚወዱና በታማኝነት የሚያገለግሉ ብቁ ዜጎች ለማፍራት እንደሚጥሩ ነው የጠቆሙት።

ዲያስፖራው ሀገሩን በሀቀኝነት ለማገልገል ፍላጎት ቢኖረውም የሚሠራበት መድረክ ባለመኖሩ ገንዘብ ከመላክ ባለፈ ዕውቀቱን ለዜጎች የሚያካፍልበት ምቹ ሁኔታ እንዳልነበረ የገለጹት ዶክተር ብርሃኑ፤ የጌትፋክት ትምህርትና ሥልጠና መጀመሩ ሀገራቸውን የሚወዱ ኢትዮጵያውያን በገንዘብና በዕውቀታቸው ማገልገል የሚችሉበት ሁኔታ ይፈጥራል ብለዋል ።


ከዚህ በተጓዳኝ ተማሪዎች በአካል ለማስተማር በዓለም ላይ ካሉ ታዋቂ ዩኒቨርሲቲ አንዱ ከሆነው ከኤምአይቴ (MIT) ዩኒቨርሲቲ የሚመጡ 120 ተማሪዎች ከኢትዮ-ቴሌኮም ሠራተኞች ጋር በመተባበር የኮምፒውተር ፕሮግራም ትምህርት ለተማሪዎች እንደሚያስተምሩ ገልጸዋል።

ተቋሙ ከተለያየ ቦታ የመጡ 104 ተማሪዎችን ለሦስት ወራት የቋንቋ ክህሎት፣ የአስተዳደር ብቁነት እንዲሁም በአካባቢያቸው የሚፈጠሩ ችግሮችን መፍታት የሚያስችላቸውን ክህሎት የማስጨበጥ ሥራ እንደተሠራ አብራርተዋል ።

ጌትፋክት ኢትዮጵያ ነዋሪነታቸው በውጪ ሀገራት የሆኑ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ያቋቋሙት ድርጅት ሲሆን የኢትዮጵያን መልካም ገጽታ ለማስተዋወቅ፤ በውጪው ዓለም ሚዲያዎች እና በተለያዩ መድረኮች ስለኢትዮጵያ በአሉታዊነት የሚነሱ ሃሳቦችን በመረጃ አስደግፎ በማስተካከል፤ ስለሀገሪቱ በጎ አመለካከቶች እንዲዳብሩ ለማገዝ የሚሠራ ድርጅት ነው።

# ኢኮኖሚውን እያመሰ ያለው ደላልነት

**ፋንታነሽ ክንዴ**



የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በእጅጉ እየፈተኑ ከሚገኙ ጉዳዮች አንዱ የደላሎች አሉታዊ ሚና ከፍ ማለት መሆኑ ተደጋግሞ ይገለጻል። ከግብርና ምርቶች እስከ ቤት፣ መኪናና ሌሎችም ተንቀሳቃሽና ተንቀሳቃሽ ባልሆኑ ንብረቶች ሽያጭ ላይ የደላሎች እጅ ረዝሞ የሚስተዋል ነው።

የገበያ ስርዓቱ በአብዛኛው በደላሎች የሚወሰን በመሆኑ ምክንያታዊ ባልሆነ የዋጋ ጭማሪ ምክንያት ዜጎች ላይ እየደረሰ ያለው ጫና ከፍተኛ ነው።

በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተገኝተው ከምክር ቤት አባላት ለተነሱ ጥያቄዎች በሰጡት ምላሽ ‹‹ኢትዮጵያ ውስጥ መሬት የመንግሥትም አይደለም፣ የሕዝብም አይደለም፣ የደላሎች እና የሌቦች ሹመኞች ነው›› ሲሉ የሰጡት ማብራሪያ የደላሎች ሚና በኢኮኖሚው ውስጥ ምን ያህል አሉታዊ ሚና እየተጫወተ እንደሆነ ማሳያ ነው።

በኮሮና ቫይረስና በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል በነበረው ጦርነት ከፍ ያለ ጫና ያስተናገደው አገራዊ ኢኮኖሚ የደላሎች ሚና ከፍ ማለት ችግሩን ‹በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ› ይሉት አይነት እንዳደረገው የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ይገልጻሉ።

መንግሥት በደላሎች ላይ የማያዳግም እርምጃ እንደሚወሰድ ደጋግሞ ቢገልጽም ይህ ነው የሚባል ውጤት እንዳልታየ የሚጠቅሱት ባለሙያዎቹ፤ ጠንካራ ተቋማትን መገንባትና የደላሎች ሚና በገበያ ስርዓቱና በአጠቃላይ ኢኮኖሚው ላይ ያላቸውን አሉታዊ ሚና መቆጣጠር እንደሚገባ ይጠቁማሉ።

የፖለቲካና ኢኮኖሚ ተንታኙ አቶ ሸዋፈራሁ ሽታሁን እንደሚሉት፤ በገበያ ስርዓቱ ላይ የደላሎች ሚና ከፍተኛ በመሆኑ አንድ ምርት ወደ ገበያ የሚወጣው ደላላ ሲፈልገው ብቻ ነው። ፍቃድ አውጥተው መደበኛ ንግድ ላይ የተሠማሩ በተደራቢነት ድለላ የሚሠሩም እንዳሉ ይገልጻሉ።

እንደ አቶ ሸዋፈራሁ ገለጻ፤ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ስርዓት የሚያዛባው ደላላ ብቻ ሳይሆን ስም ያልወጣላቸው ጥቂት የመንግሥት ሹማምንት ጭምር ናቸው። ይህም በመሆኑ ባለሀብቱና ባለስልጣናት ተመሳጥረው በገበያ ውስጥ ያለውን የምርትና አገልግሎት ፍላጎት አቅርቦትን የሚያዛባ ሥራ ይሠራሉ።

አንዳንድ የደላላ መዋቅሮች የረቀቁና መንግሥት መዋቅር ላይደርስባቸው የሚችል መሆናቸውን የሚጠቁሙት ባለሙያው፤ ሕብረተሰቡ ችግሩን ያውቀዋል ነገር ግን ከመንግሥት ሕጋዊ ከለላ ስለማያገኝ በዚህ ላይ ተሳታፊ ለመሆን ፍላጎት አያሳይም። በመሆኑም መንግሥት ለዜጎች አስፈላጊውን ከለላ በመስጠት ሕገወጦችን ለመከላከል የሚደረገውን ጥረት እንዲደግፉ ማድረግ ይገባል ይላሉ።

በተለይ በገበያው ላይ እየተስተዋለ ያለውን የደላሎች ሚና ለመቀነስ አምራቾች በየአካባቢው ለሚገኙ የግብርና ጽሕፈት ቤቶች ወይም ንግድና ኢንዱስትሪ ጽህፈት ቤቶች ምን ያህል ምርት እንዳላቸው መረጃ እንዲያቀርቡ ማድረግ ይቻላል። ጽህፈት ቤቶቹም ዘመኑ የሚፈቅዳቸውን የቴክኖሎጂ ዘዴዎች በመጠቀም በአካባቢው ያለውን ምርት በማሳወቅ ሸማቾች የአርሶ አደሩን ምርት በቀጥታ የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት የሚቻልበትን ሁኔታ ማጤን እንደሚስፈልግ ያመላክታሉ።

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የልማት ምጣኔ ሀብት ተባባሪ ፕሮፌሰር ካሣ ተሻገር(ዶ/ር) እንደሚሉት፤ እንደ አገር ያለው የገበያ ሁኔታ ተቋማዊ ሆኖ የሚመራ ነው ለማለት አያስችልም። በዚህም የተነሳ በገበያው ብሎም በአጠቃይ ኢኮኖሚው ላይ የደላሎችና የፖለቲከኞች እጅ እንዲረዝም እድል ፈጥሯል።

የገበያ ስርዓቱ ጤናማ ባለመሆኑ ምክንያት ብዙም ባልተራራቁ አካባቢዎች ላይ የሚስተዋለው የምርቶች ዋጋ የተራራቀ እንዲሆን አድርጎታል የሚሉት ዶክተር ካሣ፤ ይህን ችግር በዘላቂነት ለመቅረፍ መንግሥት ጠንካራ ተቋማትን መገንባትና ገበያው በእነዚህ ተቋማት በአግባቡ እንዲመራ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ይገልጻሉ።

በተጨማሪም በኢኮኖሚው ላይ ባለድርሻ የሆኑ አካላትን በአግባቡ ማሳተፍና የየድርሻቸውን አወንታዊ ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰው፤ ችግሮች እድሜ ባገኙ ቁጥር በሕዝቡ ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ እየጨመረ በአገራዊ ሰላም ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖም መጨመሩ አይቀርም። በመሆኑም ችግሩን ከመሠረቱ መለየትና የገበያ ስርአቱ በአጠቃላይም ኢኮኖሚው ላይ የሚስተዋለው እጅ ረጅም የደላሎችን ሚና መቆጣጠር ይገባል።

እንደ ባለሙያዎቹ ገለጻ፤ ደላሎች በሚፈጥሩት ችግር ዜጎች ላይ የሚደርሰው ጫና እየጨመረ ነው። አገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የሚያሳድሩት አሉታዊ ተጽዕኖም ኢኮኖሚውን ያዳክመዋል። ዜጎች ችግሩን ለዓመታት በተሸከሙት ቁጥር ከአቅማቸው በላይ ይሆንና ሌላ የሰላም መደፍረስ ምንጭ ሊሆን የሚችልበት እድል አለ።

በመሆኑም መንግሥት ጠንካራ ተቋማትን በመገንባትና ዜጎችን በማሳተፍ በገበያው ስርዓትና በአጠቃላይ አገራዊ ኢኮኖሚው ላይ የሚስተዋለውን የደላሎች ሚና መግታት አለበት ብለዋል።

# ኢትዮጵያ በቀጣዮቹ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መሰረታዊ ብረት ከውጭ አምጥተው የተለያየ ቅርፅ አውጥተው የሚሸጡ መሆናቸውን ተናግረዋል። ከአጭር ጊዜ አኳያ እየታሰበ ያለው እነዚህ ፋብሪካዎች እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ ሲሆን፤ ዘላቂ ልማት ከማሰብ አኳያ ግን ሀገሪቱ ያላትን የብረት ማዕድን ወደ ሥራ ማስገባት አለባት ነው ያሉት።

ኢትዮጵያ የ21ኛው ክፍለ ዘመን ቴክኖሎጂዎች የሚሰኙት መሳሪያዎች የሚሰሩባቸውና የተለያዩ መሠረተ ልማቶች የሚገነቡባቸው ማዕድናት ባለቤት መሆኗን የገለፁት አቶ ሚሊዮን፤ ማንጋነዝ፣ ኒኬል፣ ሊትየም፣ ታንታለምና ሌሎች የማዕድን ዓይነቶችም በኢትዮጵያ ስለመኖራቸው ገልፀዋል። በዚህም የተነሳ የውጭ ኢንቨስተሮች ከፍተኛ ፍላጎት እያሳዩ መሆኑን ተናግረዋል።



# መንግስት በጦርነት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ለህብረተሰቡ ዳግም የህክምና አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ለማድረግ የህክምና ግብአቶችን የማሟላት ስራ እየተሰራ ነው።

መንግስት ተቋማቱ መሰረታዊ የህክምና አገልግሎት እንዲጀምሩ ለማድረግም እንደ ስትሬቸር፣ ስቴትስኮፕ ያሉ የክህምና ግብአቶችና መድሀኒቶችን በማቅረብ ላይ እንደሚገኝ ጠቁመው፣ በዚህም ህብረተሰቡ አገልግሎቱን የሚያገኝበት ስርአት ተፈጥሯል ብለዋል።

የህክምና ግብአቶቹን ጤና ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ መድሀኒት አቅርቦት ድርጅት በዱቤ እየወሰደ ለጤና ተቋማቱ እያቀረበ እንደሚገኝ ገልጸው፤ በጦርነት ጉዳት ለደረሰባቸው የጤና ተቋማት ለሚደረግላቸው ድጋፍም ገንዘብ ሚኒስቴር ዱቤውን የሚመልስበት ሁኔታ እየተመቻቸ መሆኑን ገልፀዋል።

አንዳንድ መሳሪያዎች ለረጅም ጊዜ አገልግሎት ሳይሰጡ በመቆየታቸው እክል የገጠማቸው እንዳሉ ጠቁመው፤ እነዚህን የህክምና መሳሪዎች ባለሙያ ተልኮ ጥገና እያደረገላቸው መሆኑን ጠቅሰዋል።

እንደ አቶ ረጋሳ ገለጻ፤ በጦርነት በተጎዱ አካባቢዎች ያሉ የጤና ተቋማት አብዛኛዎቹ የመጀመሪያ ደረጃ የህክምና ድጋፍ መስጠት ጀምረዋል። በተለይ የጤና ተቋማቶቹ የእናቶች የወሊድ ክትትል፣የቤተሰብ ምጣኔ፣ ድንገተኛ ቀዶ ጥገና እና ሌሎችም አገልግሎቶች እየሰጡ ይገኛሉ።

በአማራና በአፋር ክልሎች በጦርነቱ ጉዳት የደረሰባቸው የጤና ተቋማትን ለማቋቋም ቀድሞ ስራ በመጀመሩ በአሁኑ ጊዜ ሁሉም በሚባል ደረጃ አገልግሎት መስጠት መጀመራቸውን አቶ ረጋሳ አውስተው፤ ከሰላም ስምምነቱ በኋላ በትግራይ ክልል ሽረ፣ አድዋ እና አክሱም ከተሞችና አካባቢያቸው ያሉ ጤና ተቋማት በሙሉ ወደ ስራ የሚገቡበት ሁኔታ እየተመቻቸ መሆኑን አመልክተዋል። በዚህም በክልሉ ባሉ ስምንት ሆስፒታሎችና 26 ጤና ጣቢያዎች መሰረታዊ የህክምና አገልግሎት መስጠት መጀመራቸውን ገልጸዋል።

በክልሉ ባሉ ሌሎች አካባቢዎችም በምግብ የተጎዱ ማህበረሰቦችን እንደ ፕላምፕሌት ያሉ አቅምን የሚያጎለብቱ መድሀኒቶኝን የማዳረስ ስራ እየተሰራ መሆኑን አቶ ረጋሳ ተናግረዋል።

አቶ ረጋሳ በጦርነት ጉዳት የደረሰባቸው የጤና ተቁዋማትን መሰረታዊ አገልግሎት ለማስጀመር ለመድሀኒት ግዢና ለአነስተኛ መሳሪያዎች ግዢ ሰባት ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር እንደሚያስፈልግ ጠቁመው፤ ለዚህም ከተለያዩ እርዳታ ሰጪ ተቋማት ጋር እየተሰራ ይገኛል ብለዋል።

# የሀብት ብክነትን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ያልሆነ የአሠራር ሥርዓት ሲዘረጋ መሆኑን ጠቁመው፤ ሌብነትን ለመከላከል ግልጽ አሠራር ሊኖር እንደሚገባ ተናግረዋል።

የሚዘረጋው የአሠራር ግልጽነትም የግዢ ጨረታ በማውጣት ሂደት ላይ የተድበሰበሱ ጥቄዎች እንዳይኖሩ ከማድረግ ጀምሮ ሌሎች ብዥታ የሚያስከትሉ አሠራሮችን በማፅዳት ጭምር ሊከወን እንደሚገባም ጠቁመዋል።

በአንድ የግዥ ኤጀንሲ ብቻ ግዥ መፈጸሙ ብቻውን በዘርፉ ለሚስተዋለው ችግር መንስዔ ላይሆን ይችላል ያሉት አቶ ከቡር፤ ችግሩ የአሠራር ቅልጥፍና አለመኖርና በጨረታ ወቅት ጨረታው ሰዓቱን ጠብቆ አለመከፈትና ከተከፈተም በኋላ ቶሎ መዘጋት አለመቻል የመሳሰሉ ችግሮች እንደሚታዩ ተናግረዋል።

የግዥ ጨረታዎች በዚህ መንገድ ሲከናወኑ ለሙስና ተጋላጭ ስለሚያደርጉና ተቋሙን ስለሚያስጠረጥሩ በቅልጥፍናና በግልፅ ሊሠሩ እንደሚገባ አብራርተዋል። እንደዚህ ዓይነት አሠራሮችን በማስተካከል ሲንጋፖር፣ ሞርሽየስና የመሳሰሉ ሀገራት በግዥ ላይ የሚፈፀም ሙስናን መቀነስ የቻሉ ሀገራት እንደሆኑ አብራርተዋል።

በዓለም ላይ በተቋም ደረጃ በማቋቋም ሁለት የግዢ ኤጀሲዎችን የሚጠቀሙ ሀገራት እንዳሉና ሀገራቱ ሁለት የግዢ ኤጀሲዎችን መጠቀማቸውም የጨረታ አማራጭ እንዲኖር፣ በመካከላቸው ፉክክርና ቀልጣፋ አሠራር እንዲሰፍን ያስችላል ተብሎ እንደሚገመት ጠቁመዋል።

በተጨማሪም ከሁለቱ አንዱ ብልሹ አሠራር ቢታይባቸው አንዱ ተቋም ከሌላው ተቋም የአሠራር ልምድ በመውሰድ ጠንካራና ተወዳዳሪ ሆኖ ወደ ተሻለ አገልግሎት አሰጣጥ ይመጣል ሲሉ አብራርተዋል።

አያይዘውም በሀገሪቱ ለግዥ የሚውለውን በጀት ለታሰበለት እቅድ እንዲውል ለማድረግ የሚዲያዎች ድርሻ የጎላ እንደሆነ አብራርተዋል። ሚዲያዎች በጨረታ ወቅት ድምጽ ለሌላቸው ድምጽ በመሆን ትክክል ያልሆኑ አሠራሮችን ለህዝብ በማጋለጥና ከህዝብና ከተዋናዮች የሚነሱ ቅሬታዎችን በሚዛዊነት ሽፋን በመስጠት የበኩላቸውን ከተወጡ በጀቱን ከምዝበራ መጠበቅ ይቻላል ብለዋል።

በተጨማሪም ሚዲያዎች በጨረታ ሰአት ተደባብሰው የሚቀሩ ድምጾችን ለህዝብ ተደራሽ በማድረግ ሚናቸውን በመወጣት በጀትን ከአላስፈላጊ ምዝበራ የመታደግ ሚናቸውን ሊወጡ እንደሚገባ መልእክት አስተላልፈዋል።

በተጨማሪም ፍርድ ቤቶች ነፃና ገለልተኛ በመሆን ሙስና ሲሠሩ በተገኙ አካላት ላይ አስተማሪና ከሙስና የሚያርቅ ከባድ የቅጣት ውሳኔ ማስተላለፍ እንደሚገባቸው ጠቁመዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለሕዝብና ለሀገር ጥቅም ስክነት የተሞላበት ፖለቲካዊ አካሄድ ወሳኝ ነው!

እንደ ሀገር በየዘመኑ ዋጋ እያስከፈሉን ካሉ ችግሮቻችን ወጥተን ለራሳችንም ሆነ ለመጭው ትውልድ የምንመኛትን የበለጸገች ሀገር ለመፍጠር ቆም ብለን ትናንቶቻችንን በሰከነ መንፈስና አእምሮ መመርመር ይጠበቅብናል። ዛሬ ላይ ለዚህ የሚሆን ዝግጁነት መፍጠር ካልቻልን በቀጣይ የተመሳሳይ ችግሮች ሰላባ ስላለመሆናችን ማስተማመኛ ሊኖረን አይችልም።

የሀገራችን ታሪክ በስፋት እንደሚዘክረው፤ በአንድ ዘመን እንደ ሀገር ከፍ ባለ የስልጣኔ/የዕድገት መንገድ ላይ የነበርን፤ የዚያኑ ያህል በተንሰላሰሉ ጦርነቶች የስልጣኔ መንገዳችንን አበላሽተን ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የድህነት እና የኋላ ቀርነት ማሳያ ለመሆን የተገደድን ሕዝቦች ነን። በዚህም የከፈልነው እና እየከፈልን ያለው ዋጋ ከፍ ያለ ነው።

በተለይም ባለፈው የአገዛዝ ዘመን የነበረው ትውልድ የተቃኘበት፣ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰብ፤ አስተሳሰቡ የወለደው ድርጊት ከሀገር ይልቅ ሰፈርና መንደርን ፤ማንነትንና ከዚህ የሚመነጭ ክብርን መሰረት ያደረገ መሆኑ ለአሁን ዘመን የሰለጠነ አስተሳሰብ ዋነኛ ተግዳሮት በመሆን ሀገር በሚፈለገው መጠን እንዳትራመድ አስገድዷታል።

ይህንን ያገነነ ታሪክ በመለወጥ፣ አዲስ የታሪክ ምእራፍ ለመጻፍ የተደረጉ ጥረቶችም፤በቀደሙት ችግሮች ላይ ተደርበው ሀገርንና ሕዝብን የበለጠ ዋጋ አስከፍለዋል።

ከ1950ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ ያለውን ሀገራዊ እውነታ ብንመለከት እንኳን፤ በዚህ የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ የነበሩ ትውልዶች፤ በአጣብቂኝ ውስጥ ቆማ የቀረችውን ሀገር ከፍርስራሽ ውስጥ አውጥተው ፤አዲስ በሆነ የጉዞ ምዕራፍ ውስጥ ለማስገባት የሄዱባቸው እልህ አስጨራሽ ትግሎች ያልተጠበቀና ያልተገባ ዋጋ ከማስከፈል ያለፈ ፋይዳ አልነበራቸውም።

በእነዚህ የታሪክ ዓመታት ውስጥ በነጻነት እና በዴሞክራሲ ስም የተካሄዱ የአደባባይም ሆነ የትጥቅ ትግሎች ፤ በብዙ መፈክሮች፣ የሕዝብ መሻትና ተስፋዎች ታጅበው፤ ብዙ መስዋዕትነት ቢከፈልባቸውም ፍጻሜያቸው ግን የተጠበቀውን ያህል ሀገርና ሕዝብን አዲስ የታሪክ ምእራፍ ውስጥ ማስገባት አላስቻለም። እንዲያውም "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ " የሆኑበት ሁኔታ ተስተውሏል።

ይህ ከትናንት ጥፋቶቻችን ካለመማር የመነጨው ሀገራዊ ችግራችን በለውጡ ማግስት መልኩን ሳይለውጥ፣ በተለመደው መንገድ የለውጡ ዋነኛ ተግዳሮት ሆኖ ሳንወድ በግድ መክፈል የተገደድነውን ዋጋ እንድንከፍል፤ ሀገርን እንደ ሀገር በከፋ መልኩ የመበተን አደጋ ውስጥ እንድትወድቅ አድርጓታል። ዛሬም ቢሆን ለሀገራዊ ነገዎቻችን ተግዳሮት ሆኖ እየፈተነን ይገኛል።

ይህን ዘመን እየተሻገረ የመጣ፤ የትውልዶችን ህልም ቅዥት በማድረግ ፤ በማይፈቅዱት የታሪክ ምእራፍ ውስጥ እንዲያልፉ እያስገደዳቸው ያለው ያለ መስከን ፣ ሰክኖ ትናንትን በሰከነ መንፈስ ያለመመርመር እና ከትናንት ስህተቶች ያለመማር ሀገራዊ ችግር በዚህ ዘመንና በዚህ ትውልድ ማብቂያ ሊበጅለት ይገባል። ይህ ትውልድ ለዚህ ችግር ተጨማሪ ዋጋ መክፈል አይጠበቅበትም።

ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ እድገት ሀገራዊ ስክነት ወሳኝ ነው። ባልሰከነ ማህበረሰባዊ ስብእና የሰከነ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ስርአት መፍጠር አይቻልም። ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ደግሞ የተለወጠ ሀገርና ሕዝብ ማየት የሚታሰብ አይደለም። ስለ ሀገር ከፍ ያለ ሕልም አልሞ ዋጋ መክፈልም ትርጉም የሚኖረው አይሆንም።

ከዚህ በመነሳት መንግስት የወደፊቷን የበለጸገች ኢትዮጵያ እውን ለማድረግ እያንዳንዱ ዜጋ በሀገራዊ ጉዳይ ላይ የሚነጋገርበትና በሚያግባቡ ጉዳዮች ላይ በጋራ እየሰራ ወደፊት የሚጓዝበትን ምቹ መደላድል መፍጠር ወሳኝ መሆኑን ያምናል። ለዚህ ደግሞ ሀገራዊ የምክክር መድረኩ ወሳኝ ነው።

ይህ መድረክ እያንዳንዱ ዜጋ በጋራ ጉዳዮቹ ላይ በመነጋገር እና ችግሮቹን በውይይት በመፍታት ለጋራ ዓላማ በጋራ ለመሰለፍ ትልቅ መንገድ እንደሚሆን ይታመናል። የበለጸገች ኢትዮጵያን በጋራ ለመገንባትም ትልቅ እድል ይፈጥራል።

ከዚህ አንጻር መላው ሕዝባችን ፤በተለይም ደግሞ በሀገራዊ የፖለቲካ መድረክ ውስጥ ተዋንያን የሆኑ ፖለቲከኞች ፣ የሙብት ተቆርቋሪዎች እና ሁሉም የኅብረተሰቡ አካላት፤ ሕዝባችን በየዘመኑ ብዙ ዋጋ ለከፈለበትና ዛሬም እየከፈለበት ላለው ምኞቱ ስኬት ከሁሉም በላይ መስከንና ሀገርን በሚጠቅሙ ጉዳዮች ዙሪያ መተባበር፤ ከዚህም አልፎ ችግሮችን በውይይትና በሰከነ መንፈስ የመፍታት ባህልን በማዳበር በሀገር ግንባታ ስራዎች ላይ በጋራ ሊረባረብ ይገባል።

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

# የመንግሥት የጸረ-ሙስና ትግል ፍሬ እንዲያፈራ

ደበል ከሳ

ስለትምህርት በተነሳ ቁጥር "ዓለምን መለወጥ የሚያስችል ብቸኛው መሣሪያ ትምህርት ነው" የሚለው የታላቁ የነጻነት ታጋይና የፖለቲካ መሪ የቀድሞው ደቡብ አፍሪካ ፕሬዚዳንት ኔልሰን ማንዴላ አባባል ሳይጠቀስ አይታለፍም። በእርግጥም ትምህርት ሰው ራሱን፣ አካባቢውን፣ አገሩንና ወገኑን ከፍ ሲልም ዓለሙን መለወጥ የሚችልበት ታላቅ ኃይሉ ነው።

ትምህርት ይህንን ኃይሉን የሚያከናውነው ደግሞ የሰውን ልጅ የአስተሳሰብ አድማሱን በማስፋት፣ ዓለምን የሚመለከትበትን ዕይታውን ወይንም አመለካከቱን በማስተካከልና ነገሮችን የመከወን ክህሎቱን በማሳደግ ነው። ይህም የሰው አዕምሮ ችግር ፈች በሆነ አስተሳሰብ እንዲሞላ ስለሚያደርገው አዳዲስ ነገሮችን የመፍጠር ብቃትን ያላብሰዋል።

እስካሁን ድረስ ዓለማችን ያለፈችባቸው የዕድገት ሂደቶችና የስልጣኔ ደረጃዎችም የሰው ልጆች በትምህርት አማካኝነት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በመፍታትና ለሕይወታቸው መሻሻል አስፈላጊ የሆኑ አዳዲስ ዕሴቶችን በመፍጠር ወደፊት በድል የመጓዝ ውጤቶች ናቸው።

ይሁን እንጂ ትምህርት የሚጠበቅበትን ዓላማ ማሳካት እንዲችልና የለውጥ መሣሪያ ሆኖ እንዲያገለግል ይህንኑ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ መቀረፅና ተግባር ላይ መዋል አለበት። በዚህ ረገድ የሩቁን ትተን ከቅርቡ ብንነሳ እንኳን ከዚያ በፊት የነበረው የደርግ መንግሥት የትምህርት ፖሊሲ "ተገቢና ውጤታማ አልነበረም" በሚል አዲስ ፖሊሲ ተቀርጾ ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ ባለፉት ሃያ ዘጠኝ ዓመታት በእኛ ሃገር ሲተገበር የቆየው ትምህርት ከላይ የጠቀስነውን የትምህርት ዓላማ ማሳካት የቻለ እንዳልነበረ መገንዘብ ይቻላል። እንዲያውም ከትክክለኛው የትምህርት ዓላማ በተቃራኒ ፍሬ ያፈራ ስለመሆኑ አሁን ላይ ሁሉም በሚባል ደረጃ የሃገሪቱ ዜጎች የሚስማሙበት ሐቅ መሆኑን ታዝበናል።

የትምህርት ሥርዓቱ ትኩረት ያደረገው ትክክለኛውን የመማርና የማወቅ መንገድ ተከትለው፣ መማርና ማወቅ የሚገባቸውን ያህል ተምረውና አውቀው፣ በአግባቡ ተመዝነውና ተገቢውን ዕውቀትና ክህሎት ብሎም ግብረ ገብና ሞራል ገንብተው፣ ያገኙትን ዕውቀትና ክህሎትም ለመልካም ነገር ለመጠቀም በሚያስችል መንገድ በሥርዓት ታንጸው፣ ተኮትኩተውና በስለውና በቅተው የሚመረቁ ዜጎችን ማፍራት ላይ አልነበረም።

ከዚህ ይልቅ ለሃገር ጥቅም ሳይሆን ትምህርትን ለዜጎች አስፋፋሁና አዳረስኩ በሚል ርካሽ ፖለቲካዊ ትርፍ ለማግኘትና አላፊ ጠፊ ስልጣንን ለማራዘም ፤ከከንቱ ስልጣኔ አስፋፊዎችና ከንቱ ውዳሴ፣ ከታይታ ዕድገት ደጋፊዎች ከውድቀት የማያስጥል ከንቱ ድጋፍ ለማግኘት በሚያስችል ስሁት ቀመር ላይ የተመሠረተ የትምህርት ፖሊሲ ነበር።

በተቃራኒው የፖሊሲው ዋነኛ ትኩረት ተማሩ ለመባል ያህል ፊደልና ክፍል ብቻ ቆጥረው፣ ለይስሙላ ተመዝነውና በግብር ይውጣ ታንጸው ለርካሽ ዓላማ በርካሽ መንገድ ተምረው በብዛትና በስፋት ለገበያ የሚቀርብ "ርካሽ የሰው ኃይል"ን ማምረት ላይ ነበር ማለት ይቻላል። በመሆኑም ፖሊሲው "የግለሰብንና የማኅበረሰብን የአካልና አዕምሮ ተሰጥዖ በማጎልበት ችግሮችን የማወቅ፣ የመፍታት አቅም፣ ችሎታና ዝንባሌ ያዳበሩ ዜጎችን ማፍራት" በሚል ፍልስፍና ላይ የተመሰረትኩ ነኝ ቢልም መሬት ላይ በተግባር የሆነው ግን ተቃራኒው ነበር።

በዚህ የተነሳም የትምህርት ሥርዓቱ ለብዛት እንጅ ለጥራት እምብዛም ትኩረት አለመስጠቱ የትምህርትን ዋነኛ ዓላማ ግቡን እንዲስትና ችግር ፈችና የፈጠራ አስተሳሰብንና ክህሎትን የተላበሰ ትውልድ ማፍራት እንዳይቻል ደንቃራ ሆኖ ቆይቷል። "ችግሮችን የማወቅ፣ የመፍታት አቅም፣ ችሎታና ዝንባሌ ያዳበሩ" ዜጎችን ሳይሆን በብዛት ችግር የመፍታት አቅምና አመለካከት የሌላቸው በተቃራኒው ያሉ መልካም ነገሮችን መጠበቅ የማይችሉ በመፍትሔ ፋንታ ችግር የሚፈጥሩ ደካማ ዜጎችን ማፍራቱን ነው የተገነዘብነው።

ይህም አሁን ላይ እንደምናየው በአስተሳሰባቸው ምክንያታዊ ያልሆኑ፣በዕውቀታቸውና በችሎታቸው ሳይሆን በማጭበርበርና በሌብነት፣ በሥራቸውና በጥረታቸው ሳይሆን ሌላው በሠራው በአቋራጭ ለማደግ የሚፈልጉ፣ በራሳቸው የማይተማመኑ፣ ጥገኛና አቅመ ቢስ የሆኑ፣ የልማት ሳይሆን የጥፋት መሣሪያ የሆኑ ከንቱ ዜጎችን እንዲፈጠሩ አድርጓል።

ስንፍናውና ሌብነቱም ከሰሞኑ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት እጅጉን አታካች ሆኗል። ሌብነት ልምምድ ብቻ ሳይሆን እንደ መብት የሚወሰድበት አደገኛ ደረጃ ላይ ተደርሷል። የኢኮኖሚ ነቀዝ፣ የዕድገት ነቀርሳ ሆኗል። በዚህም በገጠሩም በከተማውም፣ በተማሪውም በሠራተኛውም፣ በድሃውም በሃብታሙም፣ በነጋዴውም በባለስልጣኑም፣ በገበያውም በፖለቲካውም ሳይሠሩ መብላት፣ አጭበርባሪነት፣ ቀማኛነት፣ ስርቆትና ሌብነት ሥር ሰድዶ ተንሰራፍቷል።

በተለይም የትምህርት፣ የዕውቀትና የስልጣኔ ማዕከል በሆኑት ከተሞችማ ጠቅላይ ሚኒስትር ዓቢይ እንዳሉት ሌብነትና ሳይሠሩ በልነትና ሕገ ወጥነት ከመጠን በላይ በመንገሡና ሁኔታውን ወደሥርቶ አደርነትንና ሕጋዊነት ለመመለስ የማይቻልበት ደረጃ ላይ በመድረሱ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት መገለጫ ከእኛም አልፋ የአፍሪካና የዓለም የዲፕሎማሲ ማዕከል በሆነችው በውቧ መዲናችን አዲስ አበባማ ነገሩ ከዚህም የከፋ ሆኗል።

አዲስ አበባ የሌቦቿና ቁጥርና ተግባር እጅጉን ከመብዛቱና አታካች ደረጃ ላይ ከመድረሱ የተነሳ ለብዙኃኑ ነዋሪዎቿ እንደከበረ ማዕድን የሚታዩትና "ወርቅ አልማዝ ሆንሽብኝ እኮ" ተብሎ የሚዘፈንላቸው ለማግኘት እንደሰማይ ሩቅ የሆኑት ቤቶቿ ብቻ ሳይሆኑ ከዚያም በላይ የሆኑት እጅግ ብርቅየዎቹ ሰማይ ጠቀስ ፎቆቿ ሳይቀሩ እንደ ውሾቿ ባለቤት አልባ ሆነዋል። እንዲያው በአጠቃላይ ለዚህ ሁሉ ችግር መንስኤ ለሆነው የትምህርት ሥርዓትና አሁን ላይ በኢትዮጵያ የተፈጠረው ማኅበረ ፖለቲካ ሥርዓት አባት የሆኑት ታላቁ መሪያችን እንዳሉትና እንዳለሙት ሌብነት ሥራ ሆኗል።

ይህም ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ ሄዱ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ እንዳሉት በአሁኑ ሰዓት የሌብነት ባለቤት "ከሕጋዊ ባለቤቶቹ" ከዋነኞቹ ሌቦች ወይንም ግለሰቦች እጅ ወጥቶ የማኅበረሰቡ "የጋራ ዕሴት" ወደመሆን እየተሸጋገረ ይገኛል። በየሁሉም ተቋማት ውስጥ እንደማኅበረሰብ ሌብነትን እየተለማመድን እንገኛለን። በመሆኑም ድሮ ሳይሠሩ የሚበሉ ሌቦች ብቻ ነበር የነበሩት፤ አሁን ግን ሳይሠሩ የሚበሉ ብቻ ሳይሆን የሚሠራውን ሰው መርጠው የሚበሉ፤ ተቀምጠው የሚበሉ፣ ሠው በሚሠራው የሚጠቀሙና የሚያድጉ ብቻ ሳይሆኑ የሚሠራን ሰው በተለያየ መንገድ ጠልፈው የሚጥሉ፤ ሠራተኛ ሰው ብቻ ሳይሆን ሥራን ራሱን የሚበሉ በሁሉም መስክ በስፋት እየታዩ ነው።

ችግሩ ከአቅም በላይ ሆኖ ሃገርን እንደሃገር፣ ሕዝብን እንደሕዝብ ከማጥፋቱ በፊት ፈጣንና ዘላቂ መፍትሔ ማበጀት ያሻል። መንግሥት እንደመንግሥት መፍትሔ ይሆናል ያለውን በስድስተኛው መደበኛ የእንደራሴዎች ምክር ቤት ጉባኤው በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በኩል ለሕዝብ ይፋ አድርጓል። ለዚህም ብሔራዊ የፀረ ሌብነት/ፀረ-ሙስና/ ኮሚቴ ተቋቁሞ በአስቸኳይ ወደሥራ እንደሚገባ ተገልጿል።

በተባለው መሠረትም ከሁለት ቀናት በኋላ ዓርብ ጥቅምት 8 ቀን 2015 ኮሚቴው መቋቋሙ ይፋ ሆኗል። ጅምሩ ይበል የሚያስብል መልካም ጅምር ነው። የኮሚቴው ተልዕኮ ትርጉም ያለው ፍሬ እንዲያፈራ ግን ሁሉም ዜጋ በጸረ-ሙስና ትግሉ በንቃት ሊሳተፍ ይገባል።ይህን የማድረግ የሞራልም ፤ የዜግነትም ግዴታ አለበትም። ፈጣሪ ኢትዮጵያን፣ ሠርቶ መብላትን፣ እውነትንና ፍትሕን ለዘላለም ይባርክ። አሜን።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

# ፈርጧ የፋሽን ባለውለታ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ሁሉም ሰው የተፈጠረበት አንድ ትልቅ ዓላማ አላው፤ ለዚህ የሚታደሉት ግን ጥቂቶች ብቻ ናቸው። የሁሉም ስኬቶች መጀመሪያና መጨረሻ ደግሞ እራስን መስሎ መኖር ነው። ከምንም በላይ ስኬታችን ከራስና ከአካባቢ አልፎ ለሀገር መትረፍ ሲችል ደግሞ ይሄ ትክክለኛው የስኬት ጥግ ነው። ለዚህ ከታደሉት ጥቂት ሰዎች መካከል የዛሬው የፋሽን አምድ ርዕሳችን የሆኑት የባህል አልባሳት ባለውለታ አንዷ ናቸው።

ታዲያ ስለፋሽን እያወራን በኢትዮጵያ ባሕላዊ የፋሽን ጥበብ ውስጥ ግዙፍ አሻራቸውን ማሳረፍ ስለቻሉት ስለ እኚህ ታላቅ ሴት ባናነሳ ታሪክና የሠሩት ሥራዎቻቸው ይወቅሱናልና በዛሬው የፋሽን ገጻችን ስለታላቋ የባሕል ልብስ ዲዛይን ሥራቸው ታሪካቸውን አስደግፈን ልናስነብባችሁ ወደድን።

አብዛኛዎቻችን ማለት ይቻላል የባሕል ልብሶቻችን ትዝ የሚሉንና ከየመስቀያው እያወረድን የምንለብሳቸው በበዓላት ቀን ነው። ለእኚህ ሴት ግን የባሕል አልባሳት ከመድመቂያነት አልፎ ልዩ ትርጉም አላቸው። ለእርሳቸው ሁሌም በዓል ነውና በዓመት ለ365 ቀናት በባሕል ልብስ ተውበው፣ ውብ የሆነውን የኢትዮጵያን ባህል ለዓለም አሳይተዋል። ታላቋ፣ የመጀመሪያዋ የሀገራችን የፋሽን ልብስ ዲዛይነርና የባህል አምባሳደር ወይዘሮ ጽዮን አምዶም(እማማ ጽዮን)።

እማማ ጽዮን አንዶም፣ በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ስለሚወደሰው የሌላኛው የሀገር ባለውለታና የጦር ጀግናው አማን ሚካኤል አንዶም ታላቅ እህት ናቸው።

የተወለዱት በሱዳንዋ የካርቱም ከተማ ውስጥ ቢሆንም ለሀገራቸው ከነበራቸው ጥልቅ ፍቅር የተነሳ ሁሉንም ነገር ትተው የሴቶችን የባሕል ልብስ ዲዛይን ወደማድረግና ባሕላቸውን ወደ ማስተዋወቅ ሥራ ገቡ።



**ወይዘሮ ጽዮን አንዶም**

ስለሀገራቸው ባሕል ለማወቅና ለመጨነቅ የነበራቸው ዕድል በጣም ጠባብ ብትሆንም እሳቸው ግን በመርፌ ቀዳዳ አምልጠው ብዙዎች ትኩረት ወዳልሰጡት የባሕል ፋሽን ፊታቸውን አዞሩ። ሀሳቡ ከብዙ ነገሮች አንጻር ከባድ ቢሆንም ሁሉንም በጽናት ተቋቁመው በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያዋ የሴቶች የባሕል ልብስ ዲዛይነር፣ እንዲሁም እንቁ የባሕል ፈርጥ ለመሆን በቅተዋል።

ብዙዎች የባሕል ልብሳቸውን በመልበስ ለቀናትና ለሳምንታት በተለያዩ መድረኮች ሀገራቸውን ባሕላቸውን አስተዋውቀው ሊሆን ይችላል፤ እሳቸው ግን በሳሎን፣ በጓዳው ለ365 ቀናት በመልበስ ሰለቸኝ ታከተኝ ሳይሉ እድሜ ዘመናቸውን ኖረዋል። ይህንን የሚያደርጉት ከየልብስ መደብሩ ሸምተው ሳይሆን ከቤታቸው ውስጥ በራሳቸው ፈጠራ ዲዛይን እያደረጉ በማዘጋጀት ነበር። ከወጣትነት እስከ እርጅናቸው ለዚህ ዓላማቸው የሚሆን ልዩ ልዩ ዲዛይኖችን በመፍጠርና በመሥራት ያሳለፉት እማማ ጽዮን በየቀኑ በአዳዲስ የባሕል ልብስ ይታዩ ነበርና በዚህ ድርጊታቸው የሚገረሙ ወዳጅ ዘመዶቻቸውም ‹‹እማማ አሁን እኮ እድሜዎ ገፍቶ ጥቁር ሀር ጸጉርዎም ቀለሙን ቀይሮ ጥጥ መስሏል እርሶ ግን ሁሌም በባህል ልብስ ተውበው እንደ ልጅ የሚፈነድቁበት ምስጢር ምንድነው?›› ብለው ሲሏቸው የእሳቸውም ምላሽ “ከቤቴ መሶብ ሙሉ እንጀራ እያለ አመል ካልሆነብኝ በቀር እንዴት ለልመና ጎረቤት እሄዳለሁ፣ ሀገሬ ለኔ አይደለም ለማንም የሚተርፍ የሸማ ጥበብ አላት። ሁሉ ነገር በእጄ እያለ የባዕዱን ከቋመጥኩማ ይሄ ነውር ነው። እንዲያው የፈረንጁን ስለብስ ሰውነቴን ይኮሰኩሰዋል። የባሕል ልብሴን በለበስኩ ጊዜ ግን መንፈሴ ይታደሳል ገና አንድ ፍሬ ልጅ እንደሆንኩ ያህል ይሰማኛል።” በማለት ይመልሱ ነበር።

ይህንን የሚያደርጉበት ዓላማ ለሰዎች አምሮ ለመታየት ወይንም ለመወደስ አልነበረም፤ ይልቁንስ ከጅምር እስከ ፍጻሜ የነበራቸው ዓላማ በሀገር ኩራት፣ በፋሽን ፈጠራና በባሕል ማስተዋወቅ ሥራ ከራስ አልፎ ለሌሎች ምሳሌ መሆንና ሀገራቸውን በራሷ ባሕል ከፍ ማድረግ ነበር። ሕልማቸው ከስም አልቀረምና ሀገር በቀል የሆኑ ቁሳቁሶችን በመጠቀም ብቻ የኢትዮጵያ የባሕል አልባሳት በዘመናዊ መልኩ ለገበያ እንዲቀርቡ ያደረጉ የሀገር ባለውለታ ናቸው።

በተለያዩ ጊዜያት ወደተለያዩ ሀገራት ይጓዙ ስለነበረ በሄዱበት ሁሉ የባሕል አልባሳቱን በመልበስ የኢትዮጵያን ውብ ባሕል በተዋበ መልኩ ለማሳየት ችለዋል።

በኢትዮጵያ አሁን የሚለበሱትን የሴት ባሕላዊ አልባሳት ሸማኔ ግቢያቸው ቀጥረው፣ ዲዛይን አድርገው እራሳቸው እየሰፉ፣ እየለበሱ ሌላውም እንዲለብስ ትልቁን አስተዋጽዖ አድርገዋል!!!

የእርሳቸው የጥለት ዲዛይን ሥራዎች ዘመን ተሻጋሪና በብዙ የባሕል ተከታዮች ዘንድ ተወዳጅነትን ያተረፉ በመሆናቸው አሁንም ድረስ በባሕላዊ አልባሳት ገበያ ላይ ይገኛሉ። ለእርሳቸው እውቅናና ክብር ሳንሰጥም እየተጠቀምንባቸው ነው።

ለ60 ዓመታት ያህል ከሀበሻ ጥበብ ውጭ ምንም አይነት የፈረንጅም ሆነ ሌላ ልብስ ለብሰው የማያውቁት እማማ ጽዮን የራሳቸው የሆነውን ጽዮን ጥበብን በማቋቋም በመኖሪያ ቤታቸው ሸማኔዎችን ቀጥረው በተለያዩ ዲዛይን ፈጠራዎች እየተጠበቡ አልባሳቱን ያመርቱ ነበር። ታዲያ ያመረቱትን የሴቶች የባሕል ልብስ ጽዮን ጥበብ ከተሰኘው ከሀገር ውስጥ ሱቆቻቸው አልፎ በአውሮፖ ሀገራት ውስጥም በራሳቸው መደብር ለባሕል ልብስ ተከታዮች ያቀርባሉ።

እንደ ሚለብሱት ልብስ ሥነ ምግባራቸውና አነጋገራቸውም የተዋበ እና በበጎ አድራጎት ሥራቸውም የተመሰገኑ እንደነበሩ የሚነገርላቸው እማማ ጽዮን አማርኛ፣ ትግሪኛ፣ እንግሊዝኛ፣ ዓረቢኛና ጣሊያንኛ አቀላጥፈው ይናገራሉ። ብዙዎች ስማቸውን እንኳን ለማስታወስ በሚከብዳቸውና ምርኩዝ ተደግፈው በሚቆሙበት በዚያ እድሜ እሳቸው ግን ዓላማቸውን ሳይዘነጉ ለኖሩለት ዓላማ በወኔ ቆመው ሀገራዊ መውደዳቸውን አሳይተዋል። እድሜያቸው 90 ከሞላ በኋላ እንኳን መኪና ያሽከረክራሉ። ምግብ ማብሰልና ጽዳትም ሌላው የሚያስደስታቸው የየዕለት ተግባራቸው ነበር።

የሕይወት ዘመን ሩጫቸውን በድል ያጠናቀቁት እኚህ ሴት የሀገር ባህል ልብሳቸውን ለብሰው እንደተዋቡ አይቀሬውን ሞትን ሲጠባበቁት ቆይተው፣ በስተመጨረሻም በአንድ መቶ ዓመታቸው ኅዳር 29 ቀን 2015 ዓ.ም ዳግም ላይመለሱ ከነግርማ ሞገሳቸው አሸለቡ። በሕይወት ዘመናቸው በኢትዮጵያ ባሕላዊ የፋሽን እድገት ውስጥ የሠሩት ሥራም ለኢትዮጵያ ሴቶች ብቻ ሳይሆን ለሙሉ ትውልድ ማሳያና ዓርአያ ነው። ለሠሩት ሠራ የሚገባቸውን እውቅና ባያገኙም ሕያው ሥራዎቻቸው ለትውልድ ተርፏልና ክብር ለባሕል አምባሳደራችን!

# ትዝብት/ ማረፊያ

# በቤት የሌለ ነገርን በሀገር መጠበቅ

**አቤል ገ/ኪዳን**

የእኛ ነገር በጣም አስገራሚ ነው። ብዙ ነገራችን የተቃረነ ነው። የምንፈልገው እና የምንሆነው ለየቅል ነው። ነገሩ ሰፊ ስለሆነ ዛሬ እሱን አንተነትንም። ብቻ ከሚስገርሙ የእኛ ባህሪዎች መካከል አንዱን ብቻ ዛሬ ላንሳ። እሱም ምንድን ነው ከተባለ በቤት የሌለ ነገራችን በሀገር ደረጃ የምንጠብቀው ነገር ነው።

ይህ ነገር በምን ትዝ አለኝ መሰላችሁ ፤ በቀደም ከአምባሳደር ወደ አራት ኪሎ የሚሄድ ታክሲ እየጠበቅኩ ነበር። ከብዙ ቆይታ በኋላ አንድ ታክሲ መጣ። ታክሲው ረዳት የለውም። ሹፌሩ መኪናውን አቁሞ የተሳፋሪ መግቢያውን ሊከፍት መጣ። ከዚያም በሰልፍ አስገባና ገንዘብ መሰብሰብ ጀመረ። ገንዘቡን ሰብስቦ ሲጨርስ በሩን ዘግቶ ወደ ቦታው ተመለሰ። መኪናውን አስነስቶ ሄደ። ገረመኝ። ለምንድን ነው ረዳት የሌለው። መቼም ረዳት አጥቶ አይደለም። ለረዳት ላለመክፈል ብቻ ነው የሚሆነው። ከኮሮና ወዲህ ከተለመዱ ነገሮች መካከል አንዱ ይህ ነው። ሾፌሮች ረዳቶቻቸውን ቀንሰዋል። ያለ ረዳት መሥራት ተመችቷቸዋል። ገቢ የሚካፈላቸው አይኖርም። ግን ግን ያለ ረዳት ሆኖ በሚያገኞት ገንዘብ የሚኖር ወጣትስ ምን ሠርቶ ይብላ። ያ ወጣት ነገ ሥራ ፈትቶ የሚበላው ሲያጣ የመኪናቸውን ስፖኪዮ ቢሰርቀው ይፈረድበታል?

የሚገርመው ረዳቱን ያባረረው ሰውዬም መንግሥት ለወጣቱ ሥራ እንዳልፈጠረ እና ሕዝብ እንደተቸገረ ሲናገር መስማት የተለመደ ነው። ወንደሜ አንተ ያባረርከውን ሰው መንግሥት ከየት ያመጣውን ሥራ ይቅጠረው፣ መንግሥት የራሱ ታክሲ የለው እንዴት ነው ይህን ሰው ሥራ ሊሰጠው የሚችለው መልስ የለም። አንተ ማድረግ ያልፈለግከውን ነገር መንግሥት ሊያደርግ አይችልም።

ደግሞ ወደ ቦሌ ስሄድ አንዱ ባለሀብት ያሠራውን ሕንጻ የመኪና ማቆሚያ ሱፐር ማርኬት አድርጎት አየሁ። ሱፐር ማርኬቱ ያረፈበት የሕንጻው የታችኛው ወለል ቢያንስ 50 መኪና ሊይዝ የሚችል ነው። አሁን ባለመኪና ሰዎች መጥተው ከሱፐር ማርኬቱ እቃ ይገዛሉ።መኪናቸውን በር ላይ አቁመው ለአላፊ አግዳሚ መንገድ ዘግተው ነው ገብተው የሚገዙት። የሕንጻቸውን የመኪና ማቆሚያ ለጭፈራ ቤት ፤ ለጂምናዚየም ፤ ለሌላም ያከራዩ ሰዎች ብዙ ናቸው።እነዚህ ሰዎች ጎዳናው በመኪና እንደተጨናነቀ እና በዚህ ምክንያት የፈለጉበት ቦታ በፈለጉት ሰዓት መድረስ እንዳልቻሉ ይናገራሉ። ወገኖቼ መንግሥት እነሱ ሕንጻ ጋር የሚመጣ ሰው መኪና የሚያቆምበትን ቦታ የት ይሥራ፣ በሀገሪቱ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ መኪኖች አሉ። መንግሥት ለነዚህ ሁሉ መኪና ማቆሚያ መሥራት ይችላል አይችልም። አንተ በገዛ ንብረትህ ላይ ማድረግ ያልፈለግከውን መንግሥት በሕዝብ ንብረት ላይ እንዲያዝ ስለምን ትጠብቃለህ።

ደግሞ የቤት እመቤቶች አሉ። ሥራ በዛብን ብለው የቤት ሠራተኛ የሚቀጥሩ። ሠራተኛ የሚቀጥሩት እነሱ ዕረፍት ፈልገው ነው። ነገር ግን አንድም ቀን ሠራተኛቸው ዕረፍት እንደሚያስፈልጋት የማያውቁ። እንዲያውም በተደጋጋሚ የቤት ሠራተኞች ሥራ ሲበዛባቸው እንደሚወዱ እና ዕረፍትም ሆነ ክብካቤ ሊሰጣቸው እንደማይገባ የሚናገሩ ሰዎች አጋጥመውኛል። እነዚሁ ሰዎች በመሥሪያ ቤታቸው ሥራ በዛብን ብለው የሚያማርሩ አሁንም አሁንም ዕረፍት የሚጠይቁ ሰዎች ናቸው። እነዚሁ ሰዎች በማኅበራዊ ሚዲያ መንግሥት የዜጎችን መብት ማክበር እንዳለበት የሚናገሩ ናቸው። እነዚሁ ሰዎች በሳዑዲ ዓረቢያ ያሉ ዜጎች ወደ ሀገር ቤት መመለስ እንዳለባቸው የሚወተውቱ ናቸው። እነዚሁ ዜጎች ናቸው ደግሞ የገዛ የሀገራቸውን ልጅ ጉልበት ከሰኞ እስከ እሁድ የሚበዘብዙት። እኛ በቤታችን ያላከበርነውን የሰው ልጅ መብት መንግሥት እንዲያከበር ስለምን እንጠብቃለን። አይሆንም። መጀመሪያ እና በግለሰብ ደረጃ ልንየራው የሚገባ ሥራ በሀገር ደረጃ አይከበርም።

ብዙ ሰው መንግሥት የሚባለው ተቋም ከግለሰብ በሚሰበሰቡ መብት ድምር ጉልበቱን ያገኘ መሆኑን ይረሳል። መንግሥት ይህን ያድርግ ያን ያድርግ እያልክ የቤት ሥራውን ወደ መንግሥት ባበዛህ ቁጥር መንግሥትም ካንተ የሚወስደው መብት እየጨመረ ይመጣል። ከዚያም አምባገነን ሥርዓት ይፈጠራል።

በሰለጠነው ዓለም የመንግሥት ድርሻ ምን ይሁን በሚለው ላይ ሁሌም የጦፈ ክርክር አለ። መንግሥት ብዙ መብት ሲሰጠው አምባገነን እንደሚሆን ስለሚያውቁ የመንግሥት ስልጣን በሕግ እንዲገደብ ለማድረግ ብዙ ርብርብ ይደረጋል። እንዲያውም መንግሥት ከተቆጣጣሪነት ያለፈ ድርሻ እንዲኖረው አይፈለግም። እኛ ጋር በተቃራኒው ነው። መንግሥት ሁሉንም ነገር እንዲያደርግ እንጠብቃለን። እስኪ ይታያችሁ፤የቤት ሠራተኞቻችንን እኛ ጉልበታቸውን ስለምንበዘብዝ መንግሥት ገብቶ የቤት ሠራተኛ አያያዝ የሚል ሕግ ማውጣት አለበት? እኛ ስግብግብ ሰለሆንን መንግሥት የፓርኪንግ ቦታዎች አስተዳደር የሚል መመሪያ ማዘጋጀት አለበት? እና ራስ ወዳድ ስለሆንን መንግሥት ሁሉም ታክሲ ረዳት እንዲኖረው የሚያስገድድ ደንብ ማዘጋጀት አለበት? እንደዚያ አይነት ሂደት ውስጥ ከገባን እኮ መንግሥት ምን መብላት መቼ መተኛት የት መሄድ እንዳለብን ሁሉ የሚወስንበትን ስልጣን ወደ ማግኘት ነው የሚሄደው። ይሄ ደግሞ የለየለት አምባገነንነትን ይፈጥራል።

ስለዚህም ጓዶች እንታረም። እኛ በቤታችን የማናደርገውን ነገር መንግሥት እንዲያደርገው አንጠብቅ። እኛ በቤታችን የማናደርገውን ነገር መንግሥት ግን እንዲያደርገው ከፈለግን መንግሥትን ኃላፊነቱን እናበዛበታለን። መንግሥት ደግሞ ከኛ ኃላፊነትን ብቻ ሳይሆን መብትንም አብሮ ነው የሚወስደውና የእኛ መብት እየሚሸሸ ለመንግሥት በሰጠነው መብት የተነሳም የመንግሥት ጉልበት እያየለ ይሄዳል።

ይህ ነገር ከመንግሥት እና ሕዝብ ግንኙነት ባለፈም በሞራልም በመንፈሳዊም አይን ቢታይ ውጤቱ ተመሳሳይ ነው የሚሆነው። አንተ ልታደርግ የማትወደውን ነገር ሌላ ሰው እንዲያደርግ አትጠብቅ ከሚለው የሃይማኖትም የሞራልም ሕግ ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ነው።አንተ ያባረርከውን ረዳት መንግሥትም ሆነ ሌላ ሰው እንዲቀጥረው አትጠብቅ። አንተ የዘጋከውን የመኪና መቆሚያ ሌላ ባለ ሕንጻ እንዲከፍት አትጠብቅ። አንተ የሠራተኛህን የማረፍ እና የመዝናናት መብት እንዳላከበርክ ሁሉ ሌላው ሰው ያንተን የማረፍ እና የመዝናናት መብት እንዲያከብርልህ አትጠብቅ ማለት ነው። ስለዚህ እንታረም። እኛ መሆን አለበት ብለን የምናስበውን ነገር ራሳችን ከመፈጸም እንጀምር!

**ቸር እንሰንብት!**

## ነፃ ሃሳብ

# ወቅታዊ ትኩሳቶቻችን እና መፍትሔዎቻቸው

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጽ)**

ሀገር ትኩሳት አታጣም..የሆነ ቦታ ላይ ሕመምና ቁርጥማት፣ ውጋትና ወለምታ አያጣትም። ዋናውና ትልቁ መፍትሔ ሊሆነን የሚችለው ነገር ያ ትኩሳት፣ ያ ቁርጥማት፣ ያ ውጋትና ወለምታ በምን ምክንያት እንደተነሳ ማወቁ ነው። ምክንያቱን ሳናውቅ ለሀገራችን የምንሰጣት ኪኒን፣ መነሻውን ሳናውቅ ለሀገራችን የምንሰጣት መድኃኒት ፈውስ አያመጣልንም። ትኩሳቶቻችን እንዲበርዱ ፤የትኩሳቶቻችንን መነሻ ምንጭ ማወቅ አለብን።

እስከዛሬ ዋጋ ያስከፈሉን ችግሮቻችን መነሻቸውን ሳናውቅ መፍትሔ ለመስጠት የሄድንባቸው ርቀት ነው። በየትኛውም መስፈርት ብንለካው የሀገራችን ትኩሳት ፈጣሪዎች እኛው ነን። ሀገር በራሷ አትታመምም። ሀገር በራሷ አትፈወስም። የፈውሷና የስቃይዋ ምንጭ እኛ ዜጎቿ ነን። ሐኪም ሆነን ትኩሳቷን ማዳን አሊያም ደግሞ ወጌሻና አዋቂ ሆነን ችግሯን መጋራት የእኛ ምርጫ ነው። ባተኮሳት ቁጥር መጋኛ ነው እያልን ያልተገባ መድኃኒት የምንሰጣት ከሆነ፣ ወለም ባላት ቁጥር ብርድ ነው እያልን አጥሚት የምናሞቅላት ከሆነ ልንፈውሳት አንችልም። ይልቁንም ሌላ ችግርና ሌላ በሽታን ነው የምንደርብባት።

ትኩሳቶቻችንን ለመፈወስ መነሻ ምክንያቱን ማወቅ ግዴታችን ነው። በተለይ ባለፉት አራት ዓመታት ውስጥ በብዙ ነገር ላይ ታመን ሰንብተናል። ሕመሞቻችን ሌላ ሕመም እየፈጠሩ ዛሬ ላይ ደርሰናል። የሕመሞቻችንን ምንጭ፣ የትኩሳቶቻችንን መነሻ መርምረን የማያዳግም መፍትሔ መስጠት ከመንገዳገድ ያወጣናል ብዬ አምናለሁ። ይሄ ብቻ አይደለም አሁን ላይ እዛም እዚም የምንሰማቸው ለማንገዳገድ የማይበቁ አሉባልታዎች የሻረውን ቁስላችንን እንዳያመረቅዙብን እፈራለሁ። መታከም ካለብን ችግራችንን በሚያደርቅ መድኃኒት ይሁን። ማስታገሻ መድኃኒት አያስፈልገንም..እንደ ሀገር፣ እንደ ማኅበረሰብ የሚያስፈልገን መዳኛ መድኃኒት ነው።

የምንድንበትን ለማወቅ ደግሞ የምንታመምባቸውን ማወቅ አለብን። እንዲህ ሲሆን ነው የምንድነው። አንዳንድ ጊዜ ልንታመምባቸው አቅም በሌላቸው ነገሮች ነው የምንታመመው። አንዳንድ ጊዜ ሊያንገዳግዱን ጉልበት በሌላቸው ነገሮች ነው የምንገዳገደው። ኢትዮጵያን የሚያክል ትልቅ ታሪክ ያላት ሀገር፣ በብዙ አንድ አይነት ባህልና ሥርዓት የተሳሰረ ማኅበረሰብ ትንሽ ነገር ሲንገዳገድ ሳይ ምን ነካን እንድል ያደርገኛል።

የምንገዳገደው አጽንቶ የሚያቆም የመፍትሔ ሀሳብ ስላልፈጠርን ነው። የምንገዳገደው ሁልጊዜ ስለችግር ስለምናወራና ለችግሮቻችን የሚሆን የውይይት ጠረጴዛ ስለሌለን ነው። የምንገዳገደው በአንድ ሀገር ላይ አንድ አድርጎ የሚያኖር የአንድነት ሀሳብ መፍጠር ስላቃተን ነው። የመንገዳገዳችን ምስጢር ይሄ ነው። ሁሌ የምንታመመው፣ ሁሌ የሚያተኩሰን ለዚህ ነው። ሰው እኮ ልማዱን ነው። ሰው እኮ ያደገበትንና የኖረበትን ነው። ሰው የሚመስለው እኮ ትላንቱን ነው። ትላንታችን ምን አይነት እንደሆነ ደግሞ ሁላችንን የምናውቀው ነው።

የመጣንበት..የኖርንበት ጎዳና አንድ አይነት ነው። ለዚህ ነው በጽናት የሚያቆም የመፍትሔ ሀሳብ ያጣነው። እንንቃ..ትናንሽ ሀሳቦች እንዲያንገዳግዱን ዕድል መስጠት የለብንም። ትናንሽ ችግሮች እንዲለያዩን መፍቀድ የለብንም። ኢትዮጵያ የምትባለው ሀገር ከሀሳብ በላይ ናት። ትናንሽ ሀሳቦች ሊያንገዳግዷት ከቶ አይቻላቸውም።

በዓለም ላይ ያለ ችግር የሚኖር ሀገር የለም። ሁሉም መጠኑ ይለያይ እንጂ የየራሳቸው የሆነ ችግር..ትኩሳት አላቸው። ዋናው ነገር ግን እንዴት ያን ትኩሳት ማብረድ ቻሉ የሚለው ነው። እኛና ሌሎች ሀገራት /መፍትሔ ተኮር ሀገራት/ የምንለያየው በችግሮቻችን መጠን ብቻ ሳይሆን ለችግሮቻችን በምንሰጠው ምላሽም ጭምር ነው። እኛ ሀገር ችግር እንጂ መፍትሔ ብዙም ትኩረት አይሰጠውም ። ቢሰጠውም ለችግሩ የሚመጥን አይደለም ።

**ትኩሳቶቻችን ሊድኑ በሚችሉ ነገሮች ላይ ብቻ እናተኩር። እንደ ሀገራዊ ምክክር ሊያግባቡን የሚችሉ ውይይቶች ያስፈልጉናል። ስንወያይ ለመግባባትና የአንድነት ሀሳብ ለመፍጠር እንጂ ትኩሳት ለመፍጠር አይሁን። እኛ ሀገር ካልሆነ በየትኛውም የምድር ክፍል ውይይትን ከሰላም ውጪ ለትኩሳት የሚጠቀም ፖለቲከኛ አላውቅም**

መቶ ዓመት ወደ ኋላ ተመልሰን፣ ሁለት መቶ ዓመታትን አስታውሰን --- ሩቅ ትላንቶችን በርብረን የምንጋጭባቸው ችግሮች አሉን፤ትላንትን ለትላንት መተው ያቃተን ነን። ትላንትን ለትላንት ብንተወው ዛሬን እንዴት መኖር እንዳለብን አይጠፋንም ነበር። ድሮን ለድሮ ብንተወው ዛሬ ላይ የምንፈልጋትን ሀገር መፍጠር ይቻለን ነበር። ከትላንት ያልወጣ ጭንቅላት ዛሬ የለውም። ከትላንት ያልወጣ አስተሳሰብ ለዘመኑ የሚመጥን ወቅታዊ እሳቤን ማራመድ አይቻለውም። ለዛም ነው በሀሳብ እየወደቅን በችግር የምንቆመው። ለዛም ነው በመፍትሔ እያነስን በችግር የጎለመስነው። ለዛም ነው በለውጥ እየኮሰስን በነውጥ የቀደምነው።

በአንድ ሀገር ላይ ችግር ሊፈጠር ይችላል ፣ጥልቁ ጉዳይ ለችግሩ የምንሰጠው አፋጣኝ ምላሽ ነው ።እሱ ነው የሀገራችንን የወደፊት ዕጣ ፈንታ ሊወስን የሚችለው። ያለፉት አራት ዓመታት እንደሀገር በብዙ ነገሮች ላይ የተንገዳገድንባቸው ናቸው። ደግነቱ ግን ተንገዳግደን አልወደቅንም። እንዳንወድቅ ሆነን ቆምን እንጂ። ችግሩ መንገዳገዳችንና አለመውደቃችን አይደለም። ችግሩ ወቅታዊም ሆነ ለነባር ችግሮቻችን አፋጣኝ ምላሽ አለመስጠታችን ነው።

ኮሮና የአንበጣ መንጋ የአንድ ወቅት ሰሞነኛ ችግሮቻችን ነበሩ። የህዳሴ ግድባችን፣ የግብጽና ሱዳን አተካራ የአንድ ሰሞን መነጋገሪያ አጀንዳዎቻችን ነበሩ። ከዛ ስንወጣ የሰሜኑ ጦርነት መጣ..ከሰሜኑ ጦርነት ጋር ተያይዞ የአሜሪካና የምዕራባውያን ጫና ተከተለ። በአግዋ፣ በኤች አር 16 አበሳ አየን። ይሄ ብቻ አይደለም የአውሮፓ ኅብረትና የተባበሩት መንግሥታት ማዕቀብና ክልከላ ተከተለ። ይሄ ብቻ አይደለም ጦርነቱን ታኮ የኑሮ ውድነት፣ የታሪፍ ጭማሪ ተከተለ። በሰሜኑ ጦርነትና ይዟቸው በመጣው የምዕራባውያን ጣጣ እየተሰቃየን ሁለት ዓመታትን በመከራ አሳለፍን። ከብዙ ትግል በኋላ ሰላም አገኘን።

ሰላማችንን አጣጥመን ሳንጨርስ የተወካዮች ምክር ቤት አሸባሪ ብሎ በፈረጀው ሸኔ በወለጋና በአጎራባች አካባቢዎች ብሔር ተኮር የሆነ የንጹሓንን ሞትና እልቂት ሰማን..መስማት ብቻ አይደለም ደጋገምነው። ከዚህ ሕመም ሳናገግም የባንዲራ መሰቀል ጉዳይ ሌላ ትኩሳት ሆኖ መጣ። በዚህ ሳናበቃ በሃይማኖት ጉዳይ አተካራዎችን መስማት ጀመርን። ይህ በእንዲህ እንዳለ ስር የሰደደ የሙስና ጉዳይ ወቅታዊ ዜና ሆኖ ቤታችን መጣ። ትኩሳቷ በማያልቅ ሀገር ላይ ነን..ሌላ ትኩሳት ላለመስማታችን ምንም ማረጋገጫ የለንም።

የሚጠቅመን የትኩሳት ዜና መስማት አይደለም.. የሚጠቅመን ትኩሳት የሌለባትን ሀገር ቢኖርባትም ቶሎ የሚሽርባትን ሀገር መፍጠር ነው። እየተንገዳገድን ወዴትም መሄድ አንችልም። መሄድ ያለው በመቆም ውስጥ ነው። ለመሄድ መቆም አለብን..ለመቆም ደግሞ መንገዳገዳችንን መተው አለብን። ላለመንገዳገድ ደግሞ የሚያንገዳግዱን ችግሮቻችንን በመፍትሔ ማስወገድ አለብን። በቃ ይሄው ነው።

ያቃተን ምንድነው? ችግር ፈጣሪ አዕምሯችን መፍትሔ ማምጣት ለምን ተሳነው? እስኪ ወደመፍትሔዎቻችን እንያ..ካስተማሩን፣ ካቆሰሉን ታሪኮቻችን ተምረን አዲስ ዛሬን፣ አዲስ ሀገርን እንሥራ። ሁልጊዜ ሞት፣ ሁልጊዜ መከራ ለምን? ሁልጊዜ አበሳ.. ሁልጊዜ ኃዘን ለምን? አጀንዳ እየፈጠርን ሁልጊዜ መናቆር..ሁልጊዜ መገፋፋት ለምን? እስኪ ደግሞ የሰላምና የአብሮነት አጀንዳዎችን እንቅረጽ። እስኪ ደግሞ ሊያስታርቁንና ሊያፋቅሩን የሚችሉ የጋራ ታሪኮቻችንን እናውራ።

ትኩሳቶቻችን ሊድኑ በሚችሉ ነገሮች ላይ ብቻ እናተኩር። እንደ ሀገራዊ ምክክር ሊያግባቡን የሚችሉ ውይይቶች ያስፈልጉናል። ስንወያይ ለመግባባትና የአንድነት ሀሳብ ለመፍጠር እንጂ ትኩሳት ለመፍጠር አይሁን። እኛ ሀገር ካልሆነ በየትኛውም የምድር ክፍል ውይይትን ከሰላም ውጪ ለትኩሳት የሚጠቀም ፖለቲከኛ አላውቅም። እስከዛሬ የተቀመጥናቸው ስብሰባዎች፣ የተወያየናቸው ውይይቶች ሰላም ፈጣሪ ቢሆኑ ኖሮ ዛሬ የት በደረስን ነበር። ግን ለስብሰባ በተቀመጥን ማግስት ወደ ጦርነት የምንገባ ነን። ተወያይተን አጨብጭበን በጨረስን ማግስት የማይሽሩ ጠባሳዎችን የምንፈጥር ነን።

መማር ከቻልን የመጣንባቸው መንገዶች አስተማሪዎቻችን ናቸው። ማንም ሳይነግረን፣ ማንም ምዕራፍ ሳይጠቅስልን ልንማርባቸው የሚገቡ ብዙ ታሪኮች አሉን። ዛሬ ላይ እነዛን ታሪኮች መድገም ሀገር ከመሸጥ ባንዳነት የሚለይ አይደለም ። የሚያስፈልገን ሰላም ብቻ ነው። የሚያስፈልገን ችግሮቻችንን በውይይት እየፈታን የጋራ ሀገር መገንባት ብቻ ነው። የሚያስፈልገን ሀገራዊ ምክክር፣ ሀገራዊ እርቅ፣ ሀገራዊ አንድነት ነው። የሚያስፈልገን ሕዝብን ማዕከል ያደረገ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰብ ነው።

ለፖለቲካ ንግድም ሆነ ለስልጣን ማራዘሚያነት እየተባሉ እዚህም እዛም የሚፈበረኩ የውሸት ዜናዎች ሀገር ከመጉዳት ባለፈ ፋይዳ ስለሌላቸው ይበቁናል። በብዙ ነገር ላይ ደክመናል። በብዙ ነገር ላይ ታክተናል። አሁን ሰላም ነው የሚያስፈልገን። አሁን እፎይ የምንልበት ፖለቲካና ፖለቲከኛ ነው የሚያስፈልገን። ልማት፣ብልጽግና ነው የሚያስፈልገን። ፍቅር ወንድማማችነት ነው ግድ የሚለን። በእነኚህ እውነት ውስጥ ስንቆም ነው ትኩሳቶቻችን የሚበርዱት.. መፍትሔ የምናመጣው።

አንገት እንቅርትና ጆሮ ደግፍ ታክሎበት፤ ሀገር ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና አየር ወለድ ችግሮች ተደራርበውባት አስቧት..? በሁሉም መስክ እንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍን አስተናግደን ቆይተናል። ወይ እንቅርት ወይ ጆሮ ደግፉ ይበቃናል.. ለሁለት የሚበቃ አንገት እንደሌለ ሁሉ ለፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ማኅበራዊም ችግሮች የምትበቃ ሀገር የለችም። ችግሮቻችንን በውይይት እየፈታን በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ የሆነ መከራችንን መቅረፍ ይኖርብናል።

ለመግባባት ከተወያየን፣ ለመስማማት ከተቀመጥን ችግሮቻችን አይከብዱንም። ችግሮቻችን እየከበዱን ያሉት ለመስማማት ስለማንቀመጥ ነው። ትኩሳቶቻችን ሌላ ትኩሳት እየወለዱ የሚያቃጥሉን ለመግባባት ስለማንወያይ ነው። ስንዝር ለማይሞላ አንገት እንቅርትና ጆሮ ደግፍ ምኑ ነው? በኢኮኖሚዋ ዳዴ ለምትል፣ በፖለቲካው ባልበረታች ሀገር ላይ እነዚህ ሁሉ ችግሮች፣ እነዚህ ሁሉ ትኩሳቶች ከአቅሟ በላይ ናቸውና ልናስተውል ይገባል። ሀገር ሰው ናት..እንደ ሰው ናት። ስሜት አላት..ከተቻለ ድህነቷን የሚቀርፍ፣ ኋላ ቀርነቷን የሚያስቀር ሀሳብና ተግባቦት እናውርሳት። ካልተቻለ ደግሞ ለድህነቷ የሚመጥን ትኩሳትን እንጂ ከአቅሟ በላይ የሆነ መከራን አንስጣት።

አንዳንዴ ጭር ሲል አንወድም አይነት እየሆነብን ነው። ጭር ሲል አጀንዳ እየቀረጽን፣ አሉባልታ እየነዛን የሀገርን ሰላም፣ የማኅበረሰቡን መረጋጋት የምናውክ ከሆነ ልክ አይደለንም። መልፋት ያለብን፣ መድከም ያለብን ለሰላም ብቻ ነው። በደቡብ አፍሪካው የሰላም ድርድር በመጣው ሰላም ደስ ያልተሰኙ አንዳንድ ግለሰቦችና ቡድኖች አሉባልታ ሲያሰራጩ ነበር። አሁንም ሰላም ሆኖ የሰላም አየር በሚነፍስበት ሰማይ ላይ አንዳንድ ጭር ሲል አልወድም አይነት ሁኔታዎች እየታዩ ነው።

እኚህ ችግሮች ትኩሳት ከመፍጠር ባለፈ ፋይዳ ስለሌላቸው ሊቆሙ ይገባል። ወቅታዊውና ይዘነው የመጣነው ሀገራዊ ትኩሳት ይበቃናል። ሌላ ትኩሳት ለማስተናገድ የሚሆን አቅም የለንም። ሀገር በመፍትሔ እንጂ በአጀንዳ አትቀጥልም። ሀገር ተቀራርቦ በመነጋገር እንጂ ተራርቆ በመፎካከር አትቀጥልም። ለሀገራችን ሰላም፣ ለሀገራችን አንድነት እጃችን ላይ ካለው ውዱን እናዋጣ። ካለሰላም ቤት የምንሠራበት፣ ሀገር የምናስቀጥልበት ሌላ አማራጭ የለንም። ካለፍቅር ትኩሳቶቻችንን የምንፈውስበት ሌላ መድኃኒት የለንም። በፍቅር ማጣት እንደመጡ ሁሉ የሚድኑትም በፍቅር ነው። ከእንግዲህ የምንለፋውና የምንደክመው ለሰላም ብቻ ነው። ከእንግዲህ የምንታትረው ትኩሳቶቻችንን ለማከም ብቻ ይሁን።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# የተፋሰስ ልማትን የማጠናከር ሥራዎች

**ስምስም መንግሥቱ**

በሀገራችን በግብርናው ዘርፍ እየተከናወኑ ከሚገኙ ታላላቅ ሥራዎች መካከል አንዱ የተፋሰስ ልማት መሆኑ ይታወቃል። የተፋሰስ ልማት መካሄድ ከጀመረ ዓመታት ተቆጥረዋል። ልማቱ እንደ ኮንሶ ባሉ አንዳንድ ማኅበረሰቦች ዘንድ ባሕል ተደርጎ ሲሠራበት የኖረ ሲሆን፣ በሌሎች ማኅበረሰቦችም በስፋት ይከናወናል።

የተፋሰስ ልማቱ በማኅበረሰብ ደረጃ የተለመደ ቢሆንም፣ ከ1970ዎቹ ጀምሮ ግን በመንግሥት ፕሮጀክት፣መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና በማኅበረሰብ ተሳትፎ፣በስፋት ሲከናወን መቆየቱ ይታወቃል። በመንግሥት ደረጃ በስፋት መከናወን ከጀመረም በርካታ ዓመታት ተቆጥረዋል።

በደርግ መንግሥት የተፋሰስ ልማት በተለይ እርከን በመሥራት ይፈጸም ነበር። በኢሕአዴግ መንግሥት ደግሞ ልማቱ ይበልጥ እየተጠናከረ የመጣ ሲሆን፣ በዘመቻ መልክ እንዲሁም በሴፍትኔት መርሐ ግብር ሲከናወን ቆይቷል። የዓባይ ግድብን ከደለል ለመጠበቅ በሚል ሰፊ የተፋሰስ ልማት ሥራ ሲከናወንም ነበር። የተፋሰስ ልማቱ በተለይ ከጥር ወር አንስቶ ለአንድ ወር ይካሄዳል።

በልማቱም በተፈጥሮ፣በሰው ሰራሽና በተለያየ ምክንያቶች የተጎዱ መሬቶች አገግመው ለልማት መዋል መቻላቸውንም መረጃዎች ይጠቁማሉ። የተፋሰስ ልማት ሥራ ዘንድሮም እንደ ሀገር ይካሄዳል።

የተፋሰስ ልማት ሥራው እንደ ሀገር በስፋት እንደሚካሄድ በሚጠበቅበት በአሁኑ ወቅት በልማቱ እየተከናወነ ስላለው ተግባር በግብርና ሚኒስቴር የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ሊድ ኤክስክዩቲቭ ክፍል የተፋሰስ ልማት ዴስክ ኃላፊ ከሆኑት ከአቶ ዮሴፍ አሰፋ ጋር ቆይታ ያደረግነውን ቆይታ በዛሬው ግብርና ዓምዳችን ይዘን ቀርበናል።

አቶ ዮሴፍ እንዳሉት ፤ በተፋሰስ ልማት ሥራ ውስጥ የአፈር ለምነትን የሚያሻሽሉ በርካታ ተግባራት ይከናወናሉ። የመሬት መሸርሸርን ለመከላከል የእርከን ሥራ፣የተለያዩ የዕፅዋት ችግኞችን የማዘጋጀትና ተያያዥ ተግባራት ይፈጸማሉ። የተፋሰስ ልማቱም የሚከናወነው በአነስተኛ ተፋሰስ ሲሆን፣ለጅረት እና ለትላልቅ ወንዞች የሚጠራቀም ውሃ የሚይዝ የመሬት ስፋትም ይለያያል።

አንድ የተፈጥሮ ገጽታ ያለው መሬት ከዝናብ የሚገኘ ውሃን ሰብስቦ የሚይዝ መሆኑንና ለወንዝ መፈጠርም ምክንያት እንደሆነ የጠቆሙት አቶ ዮሴፍ፣ አንድን ወንዝ፣ ወንዝ የሚያሰኘው በዚህ መልኩ ከተለያየ አካባቢ የተጠራቀመ ጅረት ውሃ እንደሆነ ያመለክታሉ። በዚህ መልኩ በተጠራቀመ አነስተኛ ተፋሰስ ልማቱ እንደሚከናወን ይጠቁማሉ።

እንደ አቶ ዮሴፍ ማብራሪያ፤ የተፋሰስ ልማት ሥራ በባሕላዊ መንገድ ሲከናወን የቆየ ቢሆንም፣ ከ1970ዎቹ ጀምሮ ግን በተደራጀና በተጠናከረ መልኩ የማኅበረሰብ ንቅናቄ በመፍጠር በስፋት እየተከናወነ ይገኛል። በተሠሩት ሥራዎችም በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ተፋሰሶች አገግመዋል። በማኅበረሰቡ ዘንድ ያለው የተፋሰስ ልማት አስፈላጊነት ግንዛቤ ጨምሯል።

በመንግሥትና በተለያዩ ባለድርሻ አካላት ለተፋሰስ ልማት ሥራው ልዩ ትኩረት እየተሰጠው ነው። በልማቱ ለውጦች ቢመዘገቡም ገና የተፋሰስ ልማት ሥራ የሚያስፈልጋቸው አካባቢዎች በመኖራቸው አሁንም የተጠናከረ ሥራ ይጠበቃል። ልማቱ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ እንዲሁም በማኅበረሰብ ንቅናቄ እየተሠራ ይገኛል፤ ሥራዎቹም መንግሥት ከተለያዩ ዓለምአቀፍ ድርጅቶችና ተቋማት በሚያገኘው የገንዘብ ብድርና ድጋፍ የሚከናወኑ ሲሆን፣ ግብርና ሚኒስቴር ሥራ ላይ ለማዋል የነደፋቸው የተለያዩ ፕሮጀክቶች በዚህ መልኩ ታግዘው ነው ሥራ ላይ የሚውሉት።

የፕሮጀክት ድጋፉ እንደሚለያይ የጠቆሙት አቶ ዮሴፍ፣ አንዳንዱ ፕሮጀክት በቀጥታ ክፍያ በመፈጸም የሚከናወን ሲሆን፣ክፍያውም የሚፈጸመው በተፋሰስ ልማቱ ላይ በሥራ ለሚሳተፉ የማኅበረሰብ ክፍሎች ነው። እንዲህ ያለው ፕሮጀክት ለልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል። የምግብ ችግር ባለበት አካባቢ የሚኖረውን ማኅበረሰብ ክፍተት በመሙላት በልማቱ በማሳተፍ ማኅበረሰቡ ክፍያ እንዲያገኝ ይደረጋል። ሌላው ፕሮጀክት ደግሞ



ፎቶ - ፀሐይ ገ/ጊ

አቶ ዮሴፍ አሰፋ

ለተፋሰሱ ሥራ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በማሟላት፣ የማኅበረሰብና የልማት ሠራተኛን በስልጠና ግንዛቤ ለማዳበርና ለማብቃት እንዲውል የሚያስችል ነው።

በግብርና ሚኒስቴር በተቀረጸ ለአምስት ዓመት ለሚተገበር ፕሮጀክት የዓለምባንክ ወደ 500 ሚሊዮን / አምስት መቶ ሚሊዮን/ ዶላር አካባቢ ብድር መስጠቱን አቶ ዮሴፍ ይጠቁማሉ። ወደ ሥራ ከገባ ሁለት ዓመት ባስቆጠረው በዚህ ፕሮጀክት ወደ አምስት ሺ ተፋሰሶችን ለማልማት መታቀዱን አመልክተዋል።

እንደ አቶ ዮሴፍ ገለጻ፤ የተፋሰሱ ልማቱ በማኅበር በተደራጁ የማኅበረሰብ ክፍሎች እንደሚከናወንና ለማኅበራቸውም ተቀማጭ ገንዘብ ይሰጣል። ማኅበራቱ ተቀማጭ ገንዘቡን ለአባሎቻቸው በብድር በመስጠት ኑሯቸውን እንዲያሻሽሉ እገዛ ያደርጋሉ። ተፋሰሱ ከለማ በኋላም መልሶ ለማኅበረሰቡ ጥቅም የሚሰጥ ሲሆን፣ በተለይም በተፋሰሱ ውስጥ የገቢ ማስገኛ ፕሮግራሞችን በመተግበር በተለያየ መልክ ተጠቃሚ ይሆናሉ።

በዚህ መልኩ ታቅዶ እየተተገበረ ባለው በዚህ ፕሮጀክት ከአፋርና ከሶማሌ ክልሎች በስተቀር በተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች ያለው ማኅበረሰብ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል። ሁለቱ ክልሎች በፕሮጀክቱ ያልተካተቱት በሌላ ፕሮጀክት በመታቀፋቸው ነው።

ፕሮጀክቱ ከተጠቀሱት ክልሎች በስተቀር በሁሉም ክልሎች መተግበሩ ይታወቃል። ፕሮጀክቱ በተተገበረበት ጊዜ ደግሞ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በነበረው ጦርነት አብዛኞቹ አካባቢዎች በጦርነት ቀጠና ውስጥ ነበሩ።

በዓለም ላይ የተከሰተው ኮቪድ 19 ቫይረስ ወረርሽኝም በልማት እንቅስቃሴው ላይ ተጽዕኖ መፈጠሩ አይቀርም። ይህን አስመልክተው አቶ ዮሴፍ እንደገለጹት፤ በጦርነት ቀጠና ውስጥ ከነበሩት ውጭ የተፋሰስ ልማቱ ሥራ አልተቋረጠም። ኮቪድ በጉዳት ደረጃ የሚገለጽ ችግር አላስከተለም። ፕሮጀክቱ ገና በመሆኑ ወደኋላ የቀሩትም ቢሆኑ ወደፊት ሊሸፈኑ የሚችሉበት እድል ይኖራል። በጦርነቱ ምክንያት ለልማቱ የሚደረገው እንክብካቤ በመቋረጡ፣ዕፅዋቶችም የመቆራረጥና እርከኖችም የመፍረስ ሁኔታ ስለሚያጋጥማቸው ውድመቱ አይቀርም።

በአጠቃላይ እንዲህ ያሉ ፕሮጀክቶችን ጨምሮ በሴፍትኔት የሚካሄዱ ፕሮግራሞች ሳይደራረቡ ራሳቸውን ችለው እንዲሄዱ በማድረግ ነው የልማት ሥራው የሚከናወነው። የተፋሰስ ልማት ፕሮግራሙ የሚከናወነው ለክልሎች ኮታ በመስጠት ሲሆን፣ ክልሎች ለወረዳ፣ወረዳ ደግሞ ለቀበሌ በመስጠት በቅደም ተከተል ችግሩ በሚብስባቸው አካባቢዎች እንዲተገበር ይደረጋል። ግብርና ሚኒስቴርም የልማቱ ሥራ በተቀመጠለት የአሠራር ስልትና መርሐግብር መተግበሩን በመከታተልና በመቆጣጠር፣በስልጠናና በተለያየ ድጋፍ ኃላፊነቱን ይወጣል።

የተፋሰስ ልማት ሥራን ውጤታማ ማድረግ የሚቻለው በእቅድ መምራት ሲቻል መሆኑን ጠቅሰው፣ ክልሎች የየራሳቸውን እቅድ አውጥተው ወደ ሥራ እንደሚገቡም አቶ ዮሴፍ ይጠቁማሉ። እቅዱ የሚመራበት አሠራርም በፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር መዘጋጀቱንና ያንን መሠረት በማድረግ ሥራው እንደሚከናወን ይገልጻሉ።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ አንድ የተፋሰስ ልማት ከሁለት መቶ ሄክታር ያላነሰ፣በአማካይ ደግሞ ከአንድ ሺ ያልበለጠ ሄክታር ይለያል። ለዚህም የአምስት ዓመት እቅድ ይዘጋጃል። በየዓመቱም ምን ያህል እንደሚከናወን በእቅዱ ይካተታል። እቅዱ በማኅበረሰብ ተሳትፎ ወይንም በፕሮጀክትና በፕሮግራሞች ሊተገበር ይችላል።

የማኅበረሰብ ተሳትፎን ጨምሮ በተለያዩ አካላት ድጋፍና ትብብር ሲከናወን ከቆየው የተፋሰስ ልማት ውጤታማ ሆኖ የተገኘው በየትኛው ተሳትፎ እንደሆነ አቶ ዮሴፍ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፤የፕሮጀክቶች የቆይታ ጊዜ አጭር በመሆኑና ፕሮጀክቱ ሲያበቃም ሥራው እንዲቀጥል በማድረግ ላይ ክፍተቶች መኖራቸውን ተሞክሮዎች ያሳያሉ ሲሉ ጠቅሰው፣ የማኅበረሰብ ተሳትፎ አዋጭነቱ የተሻለ መሆኑን ነው ያመለከቱት።

ለመሬት ለምነት ማጣት፣በጎርፍ ለመሸርሸር በአጠቃላይ ለመሬት መጎዳት የሚያጋልጡ ችግሮች ምን እንደሆኑና በሀገሪቱም ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎች የትኞቹ እንደሆኑ አቶ ዮሴፍ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ ፤በአንድ ወቅት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሥር በሚገኝ «ዋተር ኤንድ ላንድ ሪሶርስ ሴንተር»በተባለ ክፍል በተለይ ተራራማ በሆኑ (ኃይላንድ) አካባቢዎች ላይ ጥናት መደረጉን ጠቅሰው፣በተለያየ ጊዜ ሌሎች ጥናቶች ሠሰራታቸውንም ተናግረዋል። በእነዚህ ላይ ተመሥርተው በተደራጀ ሁኔታ ምላሽ ለመስጠት እንደሚቸገሩ ጠቅሰው፣ ካለው ተሞክሮ ግን በተለያየ ደረጃ የሚገለጽ የተጎዱ መሬቶች መኖራቸውን ጠቅሰዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ተራራ የሚበዛባቸው የሀገሪቱ አካባቢዎች ለጉዳት ተጋላጭ ናቸው። ለአብነትም በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ላስታ፣ዋግ አካባቢዎች በመሬት መራቆት የተጎዱ ናቸው። የመሬት አያያዝ በተለይም በተደጋጋሚ የሚታረስ መሬት፣የዕፅዋት ሽፋን መመናመን እየከፋ መሄድም ለጉዳት የመጋለጥ እድሉን እንዲጨምር ያደርጋል። መሬቱ ተዳፋታማ ከሆነና የሚያስፈልገው የአፈር ጥበቃ እና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ሥራ ካልተሠራ በአጠቃላይ ተገቢው እንክብካቤ ካልተደረገ መሬቱ ይጎዳል።

እስካሁን በተከናወነው የተፋሰስ ልማት ሥራ በመሬቱ ለምነትና ምርታማነት ላይ ያመጣው ለውጥ በጥናት፣ልማቱ በተካሄደባቸው አካባቢዎች ከማኅበረሰብ በተሰበሰበ መረጃና በባለሙያዎች የመስክ ምልከታ መሻሻሎች መኖራቸውን ማረጋገጥ ተችሏል ሲሉ አቶ ዮሴፍ ይጠቅሳሉ። ለአብነትም ትግራይ፣በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሐረርጌ፣በአማራና በደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች በተሠራው ሥራ ያገገሙ አካባቢዎች መኖራቸውን ያመለክታሉ። እነዚህ መረጃዎች የተበታተኑ ሊሆኑ እንደሚችሉም ጠቅሰው፣ የተደራጀ መረጃ ለመስጠት ግን በጥናት የተደገፈ መሆን ይኖርበታል።ወደፊትም ሰፊ የጥናት ሥራ ይጠይቃል ሲሉ አስታወቀዋል።

የተፋሰስ ልማት ሥራ አንዴ ከተከናወነ በኋላ ወደ ኋላ ሊመለስ የሚችልበት ዕድል እንደሚኖግ አቶ ዮሴፍ ይገልጻሉ። በ1970ዎቹ የተፋሰስ ልማት ሥራ ሲጀመር እቅድ የሚነደፈውም ሆነ አጠቃላይ ሥራው በማዕከል ነበር የሚከናወነው ያሉት አቶ ዮሴፍ፣ በወቅቱ በነበረው አሠራርም ብዛት ያላቸውን አካባቢዎች ተደራሽ ማድረግ ያስቻለ አልነበረም ብለዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ በወቅቱ ማኅበረሰቡንም በበቂ ሁኔታ ለማሳተፍም አልተቻለም። ዕቅዱም በባለሙያዎች ነበር የሚዘጋጀው። ይታቀድ የነበረውም በ30 እና 40 ሺ ሄክታር መሬት ላይ ነበር። የልማቱን ሥራ ለመሥራት የማያስችሉ አንዳንድ እንቅፋቶች ሲከሰቱም የተሠራው የልማት ሥራ የወደመበት አጋጣሚም አለ። ይሄ ልማቱ ወደኋላ እንዲመለስ ከሚያደርጉ ምክንያቶች አንዱ ነው።

በሥራ ሂደት አሠራሩ የማያዋጣ ሆኖ በመገኘቱ አሠራሩን መከለስ የግድ እንደሆነም ገልጸዋል። ማኅበረሰብን ያሳተፈ ሥራ ሲሠራ ችግሮች የቱ ጋ እንደሆኑ ማየት ይቻላል ያሉት አቶ ዮሴፍ፣ ማኅበረሰቡን ያሳተፈ ሥራ ሲጀመር አቅም መፍጠር መቻሉን ነው የተናገሩት። ማኅበረሰቡን በማሳተፍ ሥራ ቀደም ሲል የነበሩ ክፍተቶችን መቅረፍ ተችሏል። የጎላ ችግርም አላጋጠመም ሲሉም ያመለከታሉ።

ኃላፊው በክትትልና ቁጥጥር ልማቱን ማስቀጠል ይጠበቃል ሲሉም ያስገነዝባሉ። እንደ እሳቸው ገለጻ፤ በተለይም ማኅበረሰቡ ከልማቱ ተጠቃሚ መሆን ሲችል ውጤታማነቱ የበለጠ ይሆናል። በባለቤትነት ስሜት ስለሚሠራ ልማቱን ይጠብቃል፤ ለመሥራትም ይነሳሳል።

ላለፉት አምስትና ስድስት ዓመታት በአንዳንድ ፕሮጀክቶች በተከናወኑት የሙከራ (ፓይለት) የተፋሰስ ልማት ሥራዎች ገቢ በማስገኘት ለውጥ ያመጡ እንዳሉም ይጠቅሳሉ። ጎጃም ውስጥ በፕሮጀክት ድጋፍ ተደርጎላቸው በጣም የተጎዳ መሬት እንዲያገግም በማድረግ ውጤታማ መሆን የቻሉ እንዳሉ በአብነት ጠቅሰው፣ ማኅበረሰቡ የተከናወነው የተፋሰስ ልማት በከብቶች እንዳይጎዳ ማኅበረሰቡም አላአግባብ ዛፍ እንዳይቆርጥ በማድረግ ጭምር ነበር ተሳትፎውን አጠናክሮ የሠራው ሲሉ ያብራራሉ። ይህ በመሆኑም የመሬቱ ምርታማነት ከመጨመሩ በተጨማሪ ማኅበረሰቡ ለከብቶቹ ግጦሽ እና ማገዶም ማግኘት ችሏል ይላሉ። ከልማቱ ጎን ለጎን ከብት ማድለብና ንብ ማነብ ሥራ እንዲሠሩም ዕድል ፈጥሮላቸዋል ብለዋል።

እንደ አቶ ዮሴፍ ማብራሪያ፤ የልማቱን ዘላቂነት ለማረጋገጥ አምስት ሺ የማኅበረሰብ ተፋሰሶችን ለማልማት ከሁለት ዓመት በፊት በተጀመረውና ለአምስት ዓመት በተቀረፀው ፕሮጀክት፤ማኅበረሰቡ በኅብረት ሥራ ማኅበር ተደራጅቶ እንዲያለማ እየተደረገ ነው፤ ማኅበረሰቡ በፕሮጀክቱ ድጋፍ ተደርጎለት በራሱ አቅዶ እንዲንቀሳቀስ ነው የተደረገው።

ይህም ቀደም ሲል ተስተውሎ የነበረውን የባለቤትነት ማጣት ክፍተት ለመቅረፍ እንደ አንድ ስልት የተያዘ መሆኑን አቶ ዮሴፍ አስረድተዋል። በተፋሰስ ልማቱ በአማካይ በአንድ ተፋሰስ አምስት መቶ ሄክታር እንደሚሸፈን የጠቆሙት አቶ ዮሴፍ፣ ይሄ በአምስት ሺ የተፋሰስ ማኅበረሰብ ሲሰላ ሽፋኑ ከፍተኛ እንደሆነም አመልክተዋል።

በሌሎች ፕሮጀክቶች የሚከናወነው ሲጨመር ደግሞ ልማቱ ሰፊ ይሆናል ብለዋል። የተፋሰስ ልማት ሥራው በበጋ እንደ እርከን ያለ ውጫዊው ሥራ፣ በክረምት ደግሞ የዕፅዋት ተከላ እንዲሁም በሁለቱም ወቅቶች የሚሠሩ ሥራዎችን በማከናወን ያልተቋረጠ እንቅስቃሴ እንደሚካሄድበት አስረድተዋል።

በተፋሰስ ልማት ሥራው እንደ ጥንካሬና ክፍተት የሚነሱትንም አቶ ዮሴፍ አብራርተዋል።በአንዳንድ አካባቢዎች ልማቱ የሚፈልገውን በቂ ግንዛቤ ይዞ ያለመሥራት አንዱ ተግዳሮት መሆኑን ጠቅሰው፣ ሥራውን ለመሥራት የሚያስፈልግ የገንዘብና የተለያየ አቅም በበቂ ሁኔታ አለመኖር ደግሞ ሌላው ክፍተት መሆኑን ይገልጻሉ። የፀጥታ መደፍረስም ለልማቱ እንቅፋት መሆኑን ጠቅሰዋል።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ማኅበረሰቡ ልማቱን እንደ ባህል ይዞ ማስቀጠሉ በጥንካሬ ይነሳል። አረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብርም ለልማቱ አስተዋፅዖ አድርጓል። መንግሥትም በልዩ ትኩረት እየሠራ መሆኑም ፕሮጀክቶች ድጋፍ እንዲያገኙ እያስቻለ ነው።

አሁን ወቅቱ የአፈር ጥበቃ ሥራ የሚከናወንበት ጊዜ እንደሆነም ጠቅሰው፣ በፌዴራልና በክልል ደረጃ ሥልጠናዎች በመሰጠት አጠቃላይ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል። በጥር ወር ሁሉም ክልሎች ወደተፋሰስ ልማት ሥራ እንደሚገቡም አመልክተዋል።

የዚህ ወቅት ሥራም ፊዚካል የሚባለው ወይም ውጫዊው የልማት ሥራ ላይ ያተኮረ መሆኑም ገልጸዋል። ግብርና ሚኒስቴርም ሥራው በጥራት መሠራቱንና አስፈላጊ ድጋፎችንም ለማድረግ ዋና ዋና በሆኑ ጉዳዮች ላይ በቦታው ተገኝቶ ክትትል እንደሚያደርግ አመልክተዋል።

እንደ ሀገር ለተያዘው ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ጥረትም በጉዳት ከልማት ውጭ የሆነ መሬት የአፈር ጥበቃ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የመሬት አቅርቦትን የማሻሻል ሥራ ባለፉት ሦስት ዓመታት መሥራቱን ኃላፊው ጠቅሰዋል።

ሚኒስቴሩ የክትትል ሥራውን ለማጠናከር የመረጃ ቋት ወይንም መሰብሰቢያ ሥርዓት(ዳታቤዝ) መዘርጋቱን ጠቅሰው፣ በዚህ ዘዴም መረጃ ከሁሉም አካባቢዎች ወደ ማዕከል እንደሚገባ ተናግረዋል። በሀገሪቱ የሚከናወነውን የተፋሰስ ልማት በኮድ (በመለያ) መዝግቦ ለመያዝ ሥራ መጀመሩንም አመልክተዋል።

# በእውቀትና እውነት ሀገርን የመገንባት ተልዕኮ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፍልስፍናና የአንትሮፖሎጂ ምሑሩ ፕሮፌሰር ምንዳርያለው ዘውዴ በመለስ ዜናዊ አመራር ወቅት ከተባረሩ 40 ምሑራን መካከል አንዱ ናቸው። በአንድ ወቅት ከኢቲቪ ጋር በነበራቸው ቆይታ እንዳነሱት የመባረራቸው መንስኤ ምክንያት የለሽ ነው። ለዚህም ማሳያ ያደረጉት የተባረሩበትን ደብዳቤ ጭብጥ ሲሆን፤ ቃል በቃል ባላስታውሰውም እንዲህ ይላል ሲሉ ጭብጡን ያስቀምጣሉ።

« ሀገርዎን በከፍተኛ ብቃትና ትጋት በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በማገልገልዎ የኢትዮጵያ ሽግግር መንግሥት ከፍተኛ አክብሮት አለው። ነገር ግን ዩኒቨርሲቲው በአዲስ መልክ እንዲደራጅ መንግሥት በወሰነው መሰረት ዩኒቨርሲቲውን እንዲያስተዳድር የሰየምነው ቦርድ የእርስዎን ውል ላለማደስ ወስኗል» ይላል። ምስጋና ችሮ፣ እውቀትና እምቅ አቅም እንዳለ አምኖ ልታስተምር አትችልም ማለት ዩኒቨርሲቲው እንዲተገብረው የሚፈለገው ሌላ ተልዕኮ አለ ማለት ነው።

ምሑር ደግሞ ሀገራዊ ጉዳይ ላይ ያገባኛል የሚል፣ በምርምር አገርን ከፍ ለማድረግ የሚጥርና ሁልጊዜ መልካም ዜጋን ለመፍጠር የሚችል ነው። እናም አዲስ ተልዕኮውን አላስፈጽምም ስለሚል በአንድ ብጣሽ ወረቀት እሳቸውን ጨምሮ 40 የዩኒቨርስቲ መምህራን ተመርጠው እንዲባረሩ ሆነዋል ይላሉ የነበረውን ሁነት ሲያስታውሱ።

ይቀጥሉና በጣም የሚገርመው በብቃታቸው ካመነና ካመሰገነ በኋላ በአባሪ ወረቀት የተጻፈውን ደብዳቤ ጭብጥ ያነሳሉ። «በእጅዎ የሚገኘውን ማንኛውንም ንብረት በ24 ሰዓት ውስጥ አስረክበው በአስቸኳይ ግቢውን ለቀው ይውጡ» ማለቱም እጅግ የሚያሳዝንና ለሀገር በለፉ ምሑሩን ያሳቀቁበት ተግባራቸው መሆኑን ያብራራሉ። ነገር ግን ምሑር መቼም በሀገሩ ተስፋ የሚቆርጥ እንዳልሆነም በተግባር ማረጋገጣቸውን ያወሳሉ። ምክንያቱም እሳቸውም ሆኑ ሌሎች የተባረሩ ሰዎች ቁጭ ብለው በተሠራባቸው ሴራ አልቆዘሙም። ይበልጥ የሚጎሉበትንና ለሀገራቸው የሚያበረክቱበትን ሥራ መርጠው ወደ መተግበሩ ገቡ እንጂ።

ለምሳሌ፡- ፕሮፌሰር ምንዳርያለውን የብዙ ሀገራት የሥራ ልምድና ተሞክሮ እንዲሁም በሀገራቸውም አንቱታን ያተረፉ መምህር ቢሆኑም ሀገራቸውን ትተው ባህር ማዶ አልተጓዙም እንደውም ወደ ትውልድ ቀያቸው ሄደው ግብርና ሥራ ላይ ተሠማሩ እንጂ። ይህ ደግሞ ፕሮፌሰሩን አርሶ አደር አሰኝቷቸው የብዙዎች መነጋገሪያ አድርጓቸው ቆይቷል። በዚህ ሳያበቁም አንባቢ ትውልድ ለመፍጠር የመጽሐፍ ሥራቸውን ቀጥለዋል። ከመባረራቸው በፊትም ሆነ በኋላ 25 የተለያዩ መጽሐፍትን ጽፈዋል። አብዛኞቹን መጽሐፍት የጻፉት ከዩኒቨርስቲ ከተባረሩ በኋላ ከግብርና ሥራቸው ጎን ለጎን ነው።

እሳቸው እንደሚያስረዱት፤ የመባረራቸው ምክንያት ሞጋች ምሑራን እንዲኖሩ የመንግሥት አለመፈለግ ነው። ፍራቻው ብዙ የባከነ ትውልድ እንዲፈጠርና መንግሥትና ምሑሩ እንዳይናበብ አድርጓል። ከዚያም በላይ ዛሬ ድረስ የዘለቀ መገፋፋቶች እንዲኖሩ ምክንያት መሆናቸውን ፕሮፌሰሩ ይናገራሉ። ግን ይህ ነገር በዶክተር ዓቢይ አሕመድ አመራር በመጠኑ የተፈታ ይመስላል ባይም ናቸው። በምክንያትነት የሚያነሱትም እርሳቸው ከተሾሙ ብዙ ሳይቆዩ የተባረሩትን ምሑራን ሰብስበው «እኛ ነን ይቅርታ መጠየቅ ያለብን» በማለት በአደባባይ ይቅርታ ጠይቀዋል። ከዚያም አልፈው ወደ ሥራ የሚመለሱበትን ሁኔታ አመቻችተዋል። ይህ ደግሞ በእጅጉ የመንግሥትንና የምሑራንን ቅርርብ የሚያጠናክር ነው።

«ሰው የባርነት ምቾትን ከመረጠ ለውሻ አሟሟት መፈረሙ የተረጋገጠ ነገር ነው። በባርነት ምቾት የኖረ ኑሮው ያሳማ ነው ሞቱም የውሻ። ተንገላቶ ያለው ደግሞ ኑሮው የጀግና ሲሆን፤ ሞቱ የሰማዕት ነው።» የሚሉት ፕሮፌሰር ምንዳርያለው፤ የሰው ልጅ የተፈጠረው እንዲያስብ ነው። ነገር ግን ማሰብን በሆዱ ተክቶ ከኖረ ሁሉን ነገር ይሸጣል። ፈጣሪውን ጨምሮ።



ፎቶ - በገባቦ ገብሬ

የውይይት መድረኩ በኮተቤ ዩኒቨርስቲ በተካሄደበት ወቅት

ምሑር ደግሞ ይህንን አያደርግም የተፈጠረበትን ዓላማ ያስታውሳል። ስለዚህም ምሑራን በምንም ተዓምር ነጻነታቸውን ለማንም አሳልፈው መስጠት የለባቸውም። ታግለው እስከሚያሸንፉ ድረስ ሀገራቸውን በማቆም ተግባር ላይ መሥራት አለባቸው። አንድ ጊዜ ነጻነትህን ለአምባገነን ከሰጠህ መልሶ ለማግኘት ከእርሱ መበደር ግድ ነው። ስለዚህ ነጻነትን ከአምባገነን ከመበደር መታቀብ የሁሉም ምሑር ግዴታ መሆን እንዳለበትም ይመክራሉ።

እስከመጨረሻው የጸና እርሱ ይድናል ነውና በስተመጨረሻ በዶክተር ዓቢይ አሕመድ ይህ ነገር ተፈቶላቸው ዛሬ የጥንቱ የሥራ ቦታቸው ላይ የሚገኙት በርካታ ናቸው። አሁንም የምሁራን ድርሻ በዚህ ልክ መታየት ይኖርበታል የሚባለው ለዚህ ነው። ምሑር ከሌለ በዕውቀት የበለጸገ ትውልድ አይኖርም፤ በስነምግባር የተኮተኮተ ዜጋ አይፈጠርም። አገር ወዳድ ትውልድም ማፍራት የማይታሰብ ነው። እየታሰበ ያለው አገርን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት መካከል ማሰለፍም ሕልም ይሆናል።

ምሑር የሌለበት ዩኒቨርሲቲ ተጠያቂነት አይኖርበትም፤ ሙስናና ብልሹ አሠራሩ እንደልብ ይንሰራፋል። በቀደሙት ጊዜያት የታየውም ይህ ነው። ሞጋቾች በመባረራቸው የተነሳ በዩኒቨርሲቲዎች አስተዳደር ውስጥ በብዙ ቢሊዮን የሚቆጠር ብር መዘረፉን ዋናው የኦዲተር መሥሪያ ቤት ለተወካዮች ምክር ቤት በተደጋጋሚ ሲያሳውቅ ነበር። ስለሆነም በኢትዮጵያ ውጤታማ የአገር ግንባታ ሥራ እንዲከናወን ምሑራንን ማበረታትና ወደ ሥራ ማስገባት ከምንም በላይ አስፈላጊ ነው። በተለይም እንደመንግሥት ይህ ሊታሰብበት ይገባል።

በእርግጥ መንግሥት አሁን ላይ ይህ ጉዳይ የገባው ይመስላል። ለዚህም ማሳያው በምሑራንና መንግሥት መካከል ያለውን መገፋፋት ለመቀነስ እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ አንዱ ማሳያ ነው። በመንግሥትና በምሑራን መካከል ጥብቅ ግንኙነት እንዲኖርም መንግሥት የተለያዩ መድረኮችን እየፈጠረ የድርሻቸውን እንዲያበረክቱ እየጠየቀ ይገኛል። ሰሞኑን በብሔራዊ ደረጃ በዩኒቨርሲቲዎች ለውይይት የቀረበው «ለአገር ግንባታ የምሑራን ሚና» የሚለው ሰነድ ለዚህ አንዱ አብነት ነው።

በመድረኩ ላይ ያገኘናቸው በኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ዲን የሆኑት ዶክተር ኃይለሚካኤል ሙሌ እንደነዚህ አይነት የውይይት መድረኮች እጅግ አስፈላጊና የሚደገፉ እንደሆኑ ያነሳሉ። ውይይቱ በምሑራንና መንግሥት መካከል ያለውን መገፋፋትም እንደሚያጠበው ያምናሉ። እስከዛሬ በነበሩት ሁኔታዎች ሁለቱ አካላት እርስ በእርስ ሲኳኑ ነበር። ሲገፋፉና ለሀገር ማበርከት ያለባቸውን ሳያበረክቱ ቀርተዋል። አሁን ግን ጅማሮዎቹ እጅግ ያስደስታሉ። ቀጣይነቱ ግን አጠያያቂ ነው። ምክንያቱም መንግሥትና ምሑራት ተቀራርበው ሠሩ የሚባለው የምሑሩ ሥራ ከመደርደሪያ ወርዶ መሬት ላይ ደርሶ የማኀበረሰቡን ችግር ሲፈታ ነው።

ምሑራን ሀሳባቸው ተቀባይነት አግኝቶ ለሀገር ግንባታ ሥራ ሲውል ነው። እናም መንግሥት በውይይቱ ልክ ቀርቦ ሥራዎችን ወደተግባር የሚቀየርበትን መንገድ መዘርጋት እንዳለበት ያነሳሉ። ቀጥለውም ምሑራን በምርምር ሥራዎቻቸው ብዙ ነገሮችን መለወጥ ይችላሉና ያንን በማድረጉ ዙሪያ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ አለባቸው ይላሉ።

ምሑራን በሙያም፣ በፖለቲካውም ፤በማኀበራዊውም ሆነ በኢኮኖሚው ላይ የዳበረ እውቀት አላቸው። በዚህም ሀገርን ልጥቀም ብለው ከተነሱ የሚያግዳቸው አካል አይኖርም። መንግሥትን ጭምር ማሸነፍ የሚችል ኃይል ባለቤት ናቸው። እናም መጠቀሙ ላይ መትጋት አለባቸው። ከምንም በላይ ግን መንግሥት ነገሩን ተረድቶ በመናበብ ቢሠራ የበለጠ ሀገርን በመገንባቱ ዙሪያ ጥሩ ውጤት ማምጣት ይቻላል ይላሉ።

ምሑራን ለሀገር መረጋጋት ግድ አስፈላጊ ናቸው። መፍትሔ አመንጪ ብቻ ሳይሆኑ መፍትሔ አውራጅና ማኀበረሰቡን አሳማኝ ናቸው። ምክንያቱም ሕዝብ ይሰማቸዋል፤ ተማሪዎቻቸው ደግሞ ይቀበሏቸዋል። ከዚያም አለፍ ብሎ በአካባቢያቸው ሰዎችን ማሳመን በሚችሉት ልክ መጓዝ ይችላሉ። እናም ይህንን ሁሉ ተቀባይነታቸውን ከብሔርም ሆነ ከፖለቲካው ነጻ አድርገው ሙያቸው ላይ ብቻ ተንተርሰው ለአገር ማበርከት ያለባቸውን ማበርከት አለባቸው ሲሉም ይመክራሉ።

እውነተኛ ምሁር አይዋሽም፣አድርባይና ወላዋይም አይደለም ስለዚህም ሀገር ችግር ውስጥ በሆነችበት ጊዜ የመፍትሔ ሀሳብ በማመንጨት ሕዝብን ይታደጋልና ዛሬ ላይ ያለን ምሑራን ይህንን ማድረግ ይጠበቅብናል የሚሉት ዶክተር ኃይለሚካኤል፤ ምሑራን ለሀገራችን አሳቢ ነን ብለው ካመኑ የፖሊሲ ግብዓት የሚሆኑ ምርምሮችን በማቅረብ፤ ሚዲያዎችን በመጠቀም የተሻሉ ሀሳቦችን ለማኀበረሰቡና ለመንግሥት ማቅረብ ይኖርባቸዋል። ታግሎ ማታገል የእነርሱ ድርሻ መሆኑን አምነው በእውቀት ሌሎችን ማሻገር ይገባቸዋል። በትምህርት የሚገነቡት አዕምሮ፣ በባህሪ የሚያንጹት ትውልድ አመለካከቱን የሚቀይሩት ሀገር ተረካቢ ትውልድ ይዘው የሚጓዙ በመሆኑ ትክክለኛ መስመርን ተከትለው ለሀገራቸው ውለታ መዋል ይኖርባቸዋል። ሀገር ስትፈርስ አብሮ መፍረስ አለና ከአሁኑ ጀምሮ መገፋፋቱን ማቆም አለባቸውም መልዕክታቸው ነው።

በኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ ለውይይት የቀረበውን ሰነድ ያቀረቡት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማዕከል አስተባባሪ አቶ መለሰ ዓለሙም በዶክተሩ ሀሳብ ይስማማሉ። የሀገር ግንባታ ጉዳይ ለአንድ አካል የሚተው አይደለም። እንደውም ትልቁን ድርሻ የሚወስዱት ምሑራን እንደሆኑ ያነሳሉ።

የሥርዓተ መንግሥት ግንባታ በምሑራን ሥራ የሚረጋገጥ ነው። ምክንያቱም ምሑራን በተሠማሩባቸው መስኮች ብዙ ለሀገር ግንባታ የሚጠቅሙ ምርምሮችን ይሠራሉ። መልካም ውጤቶችን ያሳያሉ፣ ምክረ ሃሳቦችን በማቅረብ ሀገራቸውን ይበልጥ መጥቀም የሚችሉም ናቸው። በተለይም ዕውቀታቸውን በመጠቀም የሀገራቸውን ኢኮኖሚ የተቃና እንዲሆን፣ ፖለቲካዊ ሥርዓቶች ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ እንዲቀጥሉ እንዲሁም የዜጎች ደህንነትና የሀገር አንድነት እንዲከበር በማድረግ በኩል ትልቅ ኃይል አላቸው። እናም በዚህ ጉዳይ ላይ አበክረው ሊሠሩ ይገባል።

የሀገር ግንባታ ሂደት በተሳካ ሁኔታ ያከናወኑ በርካታ አገራት የስኬታቸው መሠረት ምሑራን ናቸው። እነርሱ በተሠማሩበት የሥራ መስክ ሁሉ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ሲያደርጉ ሀገራቸውም በዚያው ልክ አድጋለች። የእኛም የሀገር ግንባታ ሥራ የተደራጀ የምሑራንን ሚና ይሻል። በመሆኑም ምሑራን ከመንግሥት ጋር ተቀራርበው መሥራትን ይበልጥ ሊላመዱ ይገባል። ምክንያቱም ከለውጡ በኋላ ሀገር የሚገነባው በእውቀት እና በሀሳብ ነው የሚለው ጉዳይ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶታል። እነዚህ ነገሮች ደግሞ ከምሑራን ጋር ያሉ ናቸው።

ስለዚህ መንግሥት እንደመንግሥት የእነርሱን ሀሳብ ተቀብሎ ለመተግበር ቁርጠኛ ነው። እየተገበረም እንደሆነ ብዙ ማሳያዎች አሉ። ለአብነት ዘላቂ መፍትሔዎችን በምርምር አምጥቶ የሚቀጥለው ትውልድ በዚያ ችግር ውስጥ እንዳያልፍ ለማድረግ የሚሠሩ ሥራዎች መበራከታቸው፤ ዩኒቨርሲቲዎች የምርምርና የችግር መፍቻ ማዕከላት እንዲሆኑ ለማድረግ ነጻነታቸውን ማወጅ የሚሉት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው። ስለሆነም ኢትዮጵያ ለሁሉም የምትመች፤ ዜጎቿ የሚኮሩባትና ታሪኮቿ የተጠበቁላት ማድረግ ላይ እጅግ ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው። በተጨማሪም ጊዜው የቴክኖሎጂ በመሆኑ ሰውን ከቴክኖሎጂው ጋር በማዋሐድ መሥራት ይጠበቅባቸዋልና እነዚህና መሰል ነገሮች ቀጣይነት እንዲኖራቸው ጠንካራ ግንኙነትን ፈጥሮ መሥራት ያስፈልጋል ባይ ናቸው።

አቶ መለሰ በእርግጥ ይላሉ፤ በእርግጥ በአገር ግንባታ ጉዳይ ላይ በርካታ ችግሮች አሉብን። እነዚህን ችግሮች ነቅሶ ለማውጣትና የመፍትሔ ሃሳቦችን ወደተግባር ለመቀየር ደግሞ የምክክር መድረኮች አስፈላጊ ናቸው። በተለይም ከምሑራን ጋር መወያየት ውዴታ ሳይሆን ግዴታ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። እናም እንደመንግሥት ይህ እቅድ ወርዶ ለውይይት ቀርቧል። ከውይይቱ በኋላ ደግሞ መልካም ሥራዎች እንደሚኖሩም ይታመናል።

አሁን አገር የምሑራንን ተሳትፎ በእጅጉ ትፈልጋለች። ምክንያቱም የተለያዩ ችግሮችን ስታሳልፍ ቆይታለች። እናም ይህንን የሚያክም አካልን ትሻለች። ይህንን ማድረግ የሚችለው ደግሞ ሙያ ያለው በእውቀቱ መሥራት የሚችለው ምሑር ነው። ስለሆነም አገርን ለመፈወስ ምሑሩ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል ይላሉ።

የኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ብርሃነመስቀል ጠናም ያላቸው ምልከታ ልክ እንደአቶ መለሠ ነው። ቀደም ባለው ጊዜ ምሑራን የዳር ተመልካች ነበሩ። እንዳይሠሩም ይደረጋሉ። በዚህም ስር የሰደደ ቅሬታ ውስጥ ሆነው ዘልቀዋል። ይህ ግን ሊሆን አይገባም ነበር። ምክንያቱም ምሑሩን አግልሎ የሚገነባ ሀገር የለምና።

አይደለም እንደሀገር እንደ ተፈጥሮም ብዙ ነገራችን ሁለት ነገሮችን የያዘ ነው። ለወንድ ሴት ፤ ለጨለማ ብርሃን፤ ለእጅ ቀኝና ግራ እየተባለ ይዘረዘራል። ይህ ግን ሥራው ቢለያይም ተፈጥሮነቱን መቀየር አይችልም። በፖለቲካና በርዕዮተ ዓለም ምልከታችን ቢለያይም በሀገር ጉዳይ ግን የማንቀይራቸው በርካታ ነገሮች አሉ የሚሉት ዶክተር ብርሃነመስቀል፤ ሌላ ሀገርም ሀብትም ስለሌለን በሥራችን፣ በምርምራችን መውጣት አለብን። ይህ ሲሆን ደግሞ የሚሠራውን ሰው ጉልበት በመስበር፣ አቅም በማሳጣት ሳይሆን እርሱን በመደገፍ መሆን አለበት።

ትናንት በመንግሥትም ሆነ እንደሀገር በርካታ ችግሮች ነበሩ። ምሑር ደግሞ አስተማሪ ነውና ስህተቱን ማሳየት ይገባዋል። የመፍትሔ መንገዱንም ማመላከት ግዴታው ነው። ስለዚህም ጥቂቶች በጩኸታቸው አደንቁረውን አገራችንን አሳልፈን እንዳንሰጥ ዛሬ በግንባታው ላይ የተቻለንን ማበርከት ይገባናል። ቀጣይ ብዙ ተባብረን የምንፈታቸው ችግሮች አሉ። ስለሆነም ጣት በመቀሳሰር ሳይሆን በመተሳሰብ ለስኬቱ መትጋት ይገባናል ሲሉም ይመክራሉ።

# «ሀገራዊ ምክክሩ ለዓመታት የተንከባለለን ችግር በማቃለል መስመር ያስይዛል»

*ዶክተር ቃለወንጌል ምንአለ የፖለቲካ ምሑር*

ምሕረት ሞገስ



**ዶክተር ቃለወንጌል ምንአለ ይባላሉ። የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርታቸውን በፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተከታትለዋል። ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በኖርዌይ አገር የሰላም እና ግጭት ትራንስፎርሜሽን ላይ አተኩረው ሠርተዋል። የሦስተኛ ዲግሪያቸውን የተማሩት በጣሊያን አገር ሲሆን፤ በፖለቲክስ ሂውማን ራይትስ ኤንድ ኢንቫይሮመንታል ሰስተነብሊቲ ላይ የተመሠረተ ነው።**

**ባሕርዳር ዩኒቨርስቲ በመምህርነት እና በማኅበራዊ ሳይንስ ጥናት ትምህርት ክፍል በምክትል ዲንነት እና ዋና ዲን ሆነውም አገልግለዋል። አሁን ደግሞ በኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት የፕሮግራምና ልማት አማካሪ ሆነው በመሥራት ላይ ይገኛሉ። ከሰላም ጋር ተያይዞ በተለይም የአገሪቱ የሰሜኑ ክፍል ላይ የተደረሰውን ስምምነት በተመለከተ እና ወደፊትም ምን መሆን አለበት በሚለው ላይ ቃለመጠይቅ አድርገን እንዲህ አቅርበንላችኋል።**

**አዲስ ዘመን፡- በፌዴራል መንግሥት እና በሕወሓት መካከል የተደረሰው የሰላም ስምምነትን ከሳይንስ አንፃር በምን መልኩ ይታያል?**

**ዶክተር ቃለወንጌል፤-** ስምምነቱን ከሳይንስ አንፃር ካየነው በበጎ መንገድ የሚወሰድ ነው። ምክንያቱም ግጭቶች ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳሉ። የኢትዮጵያም የሰሜኑ ጦርነት በተመሳሳይ መልኩ ሰፊ ሰብዓዊ ጉዳት አስከትሏል። የኢኮኖሚ ቀውስ መፍጠሩ የሚዘነጋ አይደለም። ቁሳዊ እና ማኅበራዊ ጉዳትን ትቶ ማለፉ አያጠያይቅም። ስለዚህ ስምምነቱ በብዙ ረገድ ጥፋት የሚቆምበት ሁኔታን ፈጥሯል። ግን ደግሞ ይህ ስምምነቱ ቀድሞ ወደ ኃይል እርምጃ ከመግባቱ በፊቱ የተካሔደ ቢሆን ጥሩ ነበር።

ሳይንሱን በደንብ ስናየው ደግሞ ብዙ ጊዜ ሁለት የሚቀናቀኑ ኃይላትን ወደ ሰላም ለማምጣት መጀመሪያ መሞከር አለባቸው። ወይም በሀገሪቱ ስር የሰደደ ግጭቶችን በሰላማዊ አማራጭ የመፍታት ባሕል ካለ ወደ ሰላም ሊመጡ ይችላሉ። ስር የሰደደ ግጭቶችን በሰላማዊ አማራጭ የመፍታት ባሕል በሌለባቸው ሀገራት ደግሞ የምናየው በሁለት ተቀናቃኞች መካከል መገዳደር ይኖራል። ወደ ኃይል እርምጃ ይገባሉ። በኃይል እርምጃው ሲዳከሙ ወይም አሸናፊ የማይኖርበት ጦርነት ሲሆን ወደ ድርድር የሚመለሱበት ሁኔታ አለ። ይህ በብዙ አገሮችም ታይቷል።

አገራችን ውስጥ ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ የሚፈቱበት ሁኔታ ቢኖር ጥሩ ነበር። ነገር ግን ዋናው መታወቅ ያለበት ስምምነቱ ግጭቱ ቀጥሎ ወደማያባራ አዙሪት ከምንገባበት ሁኔታ ውስጥ አውጥቶናል። ይህ ደግሞ ብዙ ኢትዮጵያውያን በበጎ የሚመለከቱት እንደሆነ መናገር እችላለሁ። በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ማኅበረሰቡም ዘንድ በበጎ የሚታይ ነው። በተለያየ መንገድ የሰላም ስምምነቱን የሚቃወሙ እና የሚፈታተኑ የሉም ማለት አይደለም። ነገር ግን በአብዛኛው የሰላም ስምምነቱ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጪ ሰፊ ማኅበረሰባዊ ድጋፍ እና ተቀባይነት ያለው ነው።

**አዲስ ዘመን፡-ሕወሓትም ሆነ መንግሥት ለሰላም ስምምነቱ ተፈፃሚነት ቁርጠኛ ከመሆንና ዘላቂ ሰላምን ከማስፈን አንፃር ከማን ምን ይጠበቃል ይላሉ?**

**ዶክተር ቃለወንጌል፤-** ብዙዎቻችን ባልጠበቅነው መንገድ የሰላም ስምምነቱ ተፈፅሟል። ስለዚህ ዘላቂ እንዲሆን የመጀመሪያው ነገር የሰላም ስምምነቱን ተግባራዊ ማድረግ ነው። ለቀናት ፊት ለፊት ተገናኝተው ተወያይተው የመጣ ስምምነት ነው። ይህ ስምምነት ተፈፃሚነቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የሰላም ስምምነቱ ላይ የተካተቱ ነጥቦች አሉ። አንደኛው በሰላም ስምምነቱ ውስጥ በቋሚነት የጦርነት አማራጩን ዝግ አድግገውታል። ከስምምነቱ ትልቅ ያተረፍነው ነገር የትኛውም ዓይነት ልዩነት በሰላማዊ መንገድ ይፈታል ተብሎ ጦርነት መቆሙ ዋነኛው ነው። ከዚህ በኋላ የሚሞት የሚቆስል እና የሚፈናቀል አለመኖሩ መልካም ነው።

የፖለቲካ ንግግሩ፣ የተፈናቀሉ ሰዎች ወደ ቦታቸው ይመለሱ የሚለውና ሌላዎቹ ጉዳዮች በሂደት የሚከናወኑ ናቸው። በተረፈ አከራካሪ እና አወዛጋቢ ጉዳዮቹ ጊዜ ወስዶ መፍታት ነው። እንደተባለው ሁለት ዓመት ሊወስድ ይችላል። ያንን ጊዜ ወስዶ ችግሩን መፍታት መቀጠል አለበት።

በሰላም ስምምነቱ ላይ የተቀመጡት ማለትም ትጥቅ መፍታት፤ ከመከላከያ ውጪ ያሉ ኃይሎች እንዲወጡ መጠየቅ፤ አከራካሪ የሆኑ ቦታዎች ጉዳይ፣ የስልጣን ክፍፍል፣ ጊዜያዊ አስተዳደር ወዘተ የሚሉ ዝርዝር ጉዳዮች አሉ። እነዛን በሂደት መቀጠል ያስፈልጋል። ከዚህ ውጪ መሠራት ያለባቸው በርካታ ሥራዎች አሉ። ለምሳሌ የመልሶ ግንባታ ሥራዎች መሠራት አለባቸው።

**አዲስ ዘመን፡- እዚህ ላይ በተለየ ሁኔታ መንግሥት የወሰደውን እርምጃ እንዴት ያዩታል? በተለይ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ወደ ትግራይ መሄዳቸውን እና የመሠረተ ልማት መልሶ ግንባታውን በተመለከተ ምን ይላሉ?**

**ዶክተር ቃለወንጌል፡-** ይሄ በጎ ተግባር ነው። አንደኛ በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ላይ ከተፈረመ በኋላ እንደውም መዘግየት ታይቷል። ናይሮቢ ላይ ከተገናኙ በኋላ አፈፃፀሙ ትንሽ ተጓቶ ነበር። ለምሳሌ በጊዜ ተከፋፍለው የሚከናወኑ ጉዳዮች አሉ። በ30 ቀን መፈፀም ያለበት በስምምነቱ ላይ የተቀመጠ ነገር ነበር። በዛ ጊዜ በሁለቱም በኩል መቀዛቀዝና መጠራጠር ነበረ።

ሌላው ከትግራይ ሕዝብ አንፃር መመልከት አለብን። ስለመሠረታዊ አገልግሎቶች ስናወራ በአፋጣኝ እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው። መብራትም ሆነ ውሃ ሌሎችም መሠረተ ልማቶችን ለማሟላት ጊዜ መውሰድ አይገባም። ስለዚህ በፌዴራል መንግሥት የተወሰደው እርምጃ ተገቢ ነው። አንዳንድ ሰው ‹‹በቅደም ተከተል በሥርዓት መሆን አለበት›› ይላል። ነገር ግን ከዛ የበለጠ የተራበ የተጎዳ ሕዝብ አለ። ሰው ተቸግሮ ስለሥነሥርዓት ቅደም ተከተል ማሰብ ቅንጦት ነው። ጊዜው ካለ በምክር ቤት ሽብርተኝነቱን አስነስቶ መሄድ ጥሩ ነው ፤ ግን እንደውም በአፈጉባኤው መሪነት የሔደው ልዑክ ዘግይቷል ባይ ነኝ።

**አዲስ ዘመን፡-የትግራይ ሕዝብም ሆነ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዚህ ጦርነት በብዙ መልኩ መጎዳቱ ይታወቃል? በቀጣይ ከዚህ ጦርነት መማር ያለብን ምንድን ነው?**

**ዶክተር ቃለወንጌል፤-** ይሄ በጣም አስፈላጊ ጥያቄ ነው። ትልቅ ቁምነገር የምንወስድበት እንደሆነ ማሰብ ያስፈልጋል። እንዲህ ዓይነት አውዳሚ ጦርነት ውስጥ እንዳንገባ ምን ማድረግ አለብን? በሚለው ላይ ውይይት ያስፈልጋል። በስሜት መጋለብ እና የሚያጋጥሙ ችግሮችን በችኮላ እና በኃይል መፍታት አውዳሚ እና ጎጂ እንደሆነ መማር መቻል አለብን። የኃይል አማራጭ ወደ ባሰ ውስብስብ ነገር እንደሚያስገባ እና መፍትሔ እንደማይሆን ማሰብ አለብን። ስለዚህ ችግር ሲመጣ ተረጋግቶ በሰላማዊ አማራጭ የመፍታት ጥበብን ባሕል አድርገን መቀጠል አለብን።

እኔ ጦርነቱ በተካሔደበት አካባቢ ነበርኩ። የመንግሥት በጀት ሳይቀር አጠቃላይ ሁሉም ወደ ጦርነት የሚል ነበር። በቀላል አማርኛ እብደት ውስጥ ነበርን። ‹‹ይህንን ሁኔታ በሰላማዊ መንገድ እንፍታው›› የሚል ሕዝብም፣ ሚዲያም ሆነ አመራር አልነበረም። ሄዶ ግን ችግሩ የተፈታው ኢትዮጵያውያን መነጋገር ሲጀምሩ ነው። አሜሪካም ሆነች አፍሪካ ኅብረት ሥራቸው ሁኔታውን ማመቻቸት ነበር። እንደውም ከስምምነት ፈፃሚዎቹ አንዱ ዶክተር ጌዲዮን እንደገለፁት፤ ‹‹ውይይቱ የተካሄደው በአማርኛ ነው።›› ብለዋል። መጀመሪያ የነበረው የሆነ አካል ጣልቃ እንዲገባ ተፈልጎ ነበር። ነገር ግን ያ አልሆነም፤ በትክክል ኢትዮጵያውያን ተገናኝተው ሲወያዩ መፍትሔ ተገኘ።

ችግሮቻችን ውስጣዊ ናቸው፤ መፍትሔዎቻችንም ውስጣዊ መሆን ይችላሉ የሚለውን ማሰብ ያስፈልጋል። ሌላው በጦርነት አሸናፊ በመሆን ዘላቂ መፍትሔ አይሰፍንም። ዘላቂ መፍትሔ የሚገኘው በውይይት እና በፍትሐዊነት ነው። አጠቃላይ የእርስ በእርስ ግጭት አውዳሚ ነው። ችግሮቻችን በሰላም፤ ሰጥቶ በመቀበል መፍታት ጥሩ አማራጭ መሆኑን ለትውልድም ማስተማር ይገባል። ከዚህ የምንማረው በሰላማዊ መንገድ ችግሮችን ለመፍታት ዘላቂ የባሕል ግንባታ ሥራ መሥራት አለብን። የተፈናቀለው ከተመለሰ በኋላ ወደ ኋላ መለስ ብለን ምን አጣን የሚለውንም በማየት በቀጣይ ብዙ መሥራት ይገባናል።

**አዲስ ዘመን፡- ጦርነት በተከሰተባቸው አካባቢዎች በርካታ ሰዎች አካላዊና ኢኮኖሚያዊ ብቻ ሳይሆን የስነልቦና ጉዳትም ደርሶባቸዋል። በቀጣይ ከዓመታት በኋላም ቁርሾ ተይዞ ችግሩ እንዳይቀጥል እና የተጀመረውን የሰላም መንገድ ዘላቂ ለማድረግ ምን መሠራት አለበት?**

**ዶክተር ቃለወንጌል፡-** ትክክል ነው። በእርግጥ ትኩረታችን የሰሜኑን ችግር የተመለከተ ነው። ይህንን ምዕራፍ ለመዝጋት፣ ሰላም እና መረጋጋቱን ለማስቀጠል የተፈረመውን የሰላም ስምምነት ወደ ተግባር መለወጥን መቀጠል ነው። ሁለቱም ተስማሚዎች የገቡትን ውል አክብረው በቅንነት

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

**ንግግር ትልቅ የሰላም ግንባታ መሣሪያ ነው። ሰላምን የምንገነባበት ትልቅ ስትራቴጂ ነው። ያሉ የፖለቲካ ውዝግቦች ወደ ኃይል እርምጃ እንዳይሔዱ አስቀድሞ መከላከያ ሲሆን፤ ይህ ባሕል ለማድረግ ትልቅ አጋጣሚ ነው**

የሰላም ስምምነቱን ማስፈፀምን መቀጠል አለባቸው። ይህ ግን በቂ አይደለም። አብረው መሠራት ያለባቸው ሥራዎች አሉ።

አሁን ያለውን መረጋጋት ለማጠናከር የሚያስችሉ ሥራዎች መሠራት አለባቸው። ለምሳሌ የተፈናቀሉ ዜጎችን ወደ ተረጋጋ ኑሯቸው እንዲመለሱ እና የሚበሉት ያጡ ሰዎችም የሚመገቡትን የሚያገኙበት ሁኔታ መፈጠር አለበት። ይህ ሲሆን የሰላም ስምምነቱ ተቋዳሾች ብዙ ይሆናሉ። ሰብዓዊ አገልግሎት እና የዕለት ደራሽ እርዳታ በመስጠት ካለው ሁኔታ እንዲጠቀሙ ማስቻል ያስፈልጋል። ለምሳሌ የተቃጠሉ ቤቶችን መገንባት እና አሁን ያለውን ሰላም ማጠናከር የሰላም ስምምነቱን መሠረት ያስይዛል። መሪዎች ቢስማሙም በግጭቱ የተጎዱትን የኅብረተሰብ ክፍሎች መልሰው እንዲደራጁ በተጨባጭ መሥራት የግድ ነው።

ይህንን ተከትሎ የመልሶ ግንባታ ሥራ መሠራት አለበት። ቢያንስ መሠረታዊ ፍላጎት ከተመለሰ በኋላ ትምህርት ቤቶችን መገንባት፣ ሆስፒታሎችን ማደራጀት እና የአገልግሎት ዘርፉ ወደ ሥራ የሚገባበትን መንገድ ማመቻቸት እንዲሁም ተጨባጭ ርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል።

ሌላው የሰላም ግንባታ ላይ ከመጀመሪያውም ወደ ግጭት ያስገቡን መሠረታዊ ምክንያቶችን የምንለይበትም መንገድ ነው። በሳይንሱ ድሕረ ግጭት የሰላም ግንባታ የሚባል ነገር አለ። እዚህ ላይ በስፋት የሚሠራው የችግሩን ምንጭ በመፍታት ነው። ሌላው ተዋጊ የነበሩ እና ወደ መንግሥታዊ የፀጥታ መዋቅር የሚገቡ ሚሊሻ እና ሌሎችንም የተሐድሶ ስልጠና መስጠት ወደ ማኅበረሰቡ የሚቀላቀሉ ካሉ እነሱ ላይም በቅደም ተከተል መሥራት ያስፈልጋል። ስለዚህ በአጠቃላይ የሰላም ስምምነቱን መተግበር፣ ያንን የሚያጠናክሩ እርምጃዎችን መውሰድ እና የድሕረ ሰላም ግንባታ እንዲሁም ለጦርነት መንስኤ የሆነውን ችግር ለይቶ መፍታት ላይ መሠራት አለበት።

በተጨማሪ መዘንጋት የሌለበት የማኅበረሰብ ዕርቅ ላይም መታሰብ አለበት። ከላይ በመንግሥት ደረጃ የተደረሰው ስምምነት የተጠቁ የኅብረተሰብ ክፍሎች ከሰላም ስምምነቱ የሚጠቀሙበት ሁኔታ ከተፈጠረ ከሰላም ስምምነቱ ተጠቃሚ መሆን ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- ከታሪክ እንደምንረዳው ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ግጭቶች ነበሩ። የአሁኑን የሰሜን ግጭትን ጨምሮ ሌሎችም የሰላም መደፍረስ በተለያዩ አጋጣሚዎች ተስተውለዋል። ይህ ሁሉ ለምን ሆነ? ኢትዮጵያውያን የተለየን ነን?**

**ዶክተር ቃለወንጌል፤-** ይሔ በጣም ከባድ ጥያቄ ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ በአብዛኛው በጦርነት የተሞላ የፖለቲካ ችግር ነው። ስለዚህ ችግሩ ምንድን ነው? ወይስ እኛ ከዓለም ማኅበረሰብ ከሌላው አፍሪካዊ የተለየ የቁጡነት ባህሪ ስላለን ነው ወይስ በመዋቅር ደረጃ ያልፈታነው ችግር በመኖሩ ነው? ወይስ የእነዚህ የሁለቱም ነገሮች ቅንጅት ነው? የሚለውን ማወቅ በጣም ወሳኝ ጉዳይ ነው። ይሔ በደንብ በትክክል ተጠንቷል ወይ? ለምሳሌ ኢትዮጵያ በጣም አውዳሚ እና ደም አፋሳሽ ጦርነቶችን አስተናግዳለች። በእኔ ግምት ምክንያቱ ሁለት ነው። አንደኛው መዋቅራዊ ሲሆን ሌላኛው ከአስተሳሰባችን የሚቀዳ ነው።

መዋቅራዊ ስንል በተከታታይ ፖለቲካችንና ታሪካችን ኢኮኖሚያችን እያሉ እየለዩ ማየት ይቻላል። አንደኛ ነገር ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ብዝኃነት በደንብ አድርጎ የሚያስተናግድ ሥርዓት እና የፖለቲካ መዋቅር ማረጋገጥ አልተቻለም። በአጼ ኃይለሥላሴ ጊዜ ፊውዳሊዝም ነው። ልዩነቶችን በኃይል ወደ አንድነት የማምጣት ዝንባሌ ነበር። በዛ ጊዜ አንድ ሀገራዊ ኢትዮጵያዊ ማንነት መገንባት ላይ ያተኮረ ነበር። በደርግ ጊዜ ለየት ባለ መልኩ ብዝኃነት እውቅና ቢሰጠውም ከሥልጣን አንፃር አሐዳዊነት በስፋት ነበረ። ደርግ ሲወድቅ ብሔር ላይ ያተኮረ ሥርዓት ተመሠረተ። ነገር ግን በተከታታይ ዓመታት ብዝኃነትን በቅጡ ሊያስተናግድ የሚችል ጠንካራ ፖለቲካ መገንባት አለመቻላችን ችግር ፈጥሯል። በሌላ በኩል የኅጠኝነትና የብሔርተኝነት ስሜት እንዲጠናከር የአንድነት ስሜት እንዲዳከም ተደርጓል። ይሔ ደግሞ ወደ ግጭት እያስገባን ነው የሚል ቅሬታ አለ።

አሁንም ቢሆን ብዝኃነትን የሚያስተናግድ ሥርዓት መኖር አለበት። የፌዴራል ሥርዓቱ መከለስ አለበት። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ብዝኃነት ሊያስተናግድ የሚችል መዋቅር እስከ አሁን መገንባት አልቻልንም። ይሔ የሚያሳየው እዚም እዚያም ያሉ የብሔር ጥያቄዎች አልተመለሱም ማለት ነው። ሌላው እዚሁ ላይ የምናየው ዴሞክራሲ እና ሰላም የተሳሰሩ ናቸው። በዘርፉ የዴሞክራሲ ሰላም ፅንሰ ሃሳብ አለ። የተሻለ የዴሞክራሲ ሥርዓት ያላቸው አገራት የተሻለ ሰላም አላቸው።

**አዲስ ዘመን፡- የተሻለ ኢኮኖሚ ያላቸው ሀገራትም የተሻለ ሰላም አላቸው ተብሎ ይታሰባል?**

**ዶክተር ቃለወንጌል፤-** አዎ ትክክል ነው። ወደዛም እመጣበታለሁ። ከዛ አንፃርም ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው አምባገነን ሥርዓት የአሁኑን ውጤት አምጥቷል። በተከታታይ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችለን የዴሞክራሲ ሥርዓትን ከመገንባት አንፃር ችግር መኖሩም በተመሳሳይ መልኩ ለግጭት እየዳረገን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለኢትዮጵያ የሰላም መደፍረስም ሆነ የሰላም መሆን ጉዳይ ከውስጥ ብቻ ሳይሆን ከውጪ ተፅዕኖ አንፃርስ ማየት የለብንም?**

**ዶክተር ቃለወንጌል፤-** አዎ ልክ ነው። ኢትዮጵያ ያለችበት ቀጣና፤ ጂኦፖለቲክሱም ወሳኝ ነው። ስር የሰደደው የቀጣናው ችግር ማለትም አንዱ የሌላኛውን ተቃዋሚ የመደገፍ (ፕሮክሲ ዋር) በስፋት አለ። የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች በሱዳን እና በሶማሊያዎች ሲደገፉ ቆይተዋል። ሌላው ኢትዮጵያ ስትራቴጂካዊ አካባቢ ላይ መሆኗ ነው። አካባቢዋ ትልቅ የንግድ መተላለፊያ መሆኑ፤ተሻግሮ መካከለኛው ምሥራቅ መኖሩ ፤ የስዊዝ ካናል ጉዳይ እና ቀጣናው የንግድ ኮሪደር መሆኑ የሚታወቅ ነው።

አካባቢው ከፍተኛ የነዳጅ ሃብት መተላለፊያ መሆኑ፤ ቀጣናው አካባቢ ያለው የፀጥታ እና የሽብርተኝነት ሁኔታን ለመዋጋት ስትራቴጂክ ቦታ መሆኑም በተመሳሳይ ለውጪ ተፅዕኖ የሚያጋልጥ ነው። ሶማሊያ አካባቢ ያለውን ሽብርተኝነት ለመግታት ካለው ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ በተጨማሪ አንዱ በሌላኛው አገር ላይ ጣልቃ የመግባት ሁኔታ መኖሩ ኢትዮጵያ ትኩረት እንድትስብ እና ውጫዊ ተፅዕኖ እንዲበረታባት ምክንያት ሆኗል።

ነገር ግን መረሳት የሌለበት ችግር የሚፈጠረው በውስጥ መዳከም ምክንያት ነው። የውጪ ኃይሎች የሆነ ክፍተት ወይም ቀዳዳ ሲያገኙ ያንን ይጠቀሙበታል። የውስጥ አንድነት የውጪ ጫናን ለመከላከል በጣም ወሳኝ ነው። ይሔንን ማሰብ ያስፈልጋል። ዋናው ችግር መነሻው ውስጥ ነው። የውስጡ እና የውጪው ሲቀናጅ ትልቅ ቀውስ ይፈጥራል። ከውስጥ ውዝግብ እና ንትርክ ሲፈጠር ልዩነቶች ሲጎሉ የውጪ ኃይሎችም በልዩነቱ መጠቀም ይጀምራሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ከችግሮቹ መንስኤዎች መካከል አንደኛው መዋቅራዊ ብለው በሁለተኛነት ደግሞ አስተሳሰብን ገልፀው ነበር። እስኪ አስተሳሰባችንም መንስኤ ሆኗል ሲሉ ምን ማለትዎ ነው ቢያብራሩት?**

**ዶክተር ቃለወንጌል፤-** አስተሳሰብ ሲነሳ ታሪክ አብሮ ይጠቀሳል። አንዱ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ጉዳይ የታሪክ ውዝግብ ነው። በዘመናዊት ኢትዮጵያ አመሠራረት ጊዜ የተፈፀሙ ክስተቶች አሉ። በሀገር ምሥረታ ሂደት ውስጥ በአንዳንድ የማኅበረሰብ ክፍሎች እንደጭካኔ እየተቆጠሩ የታሪክ ስህተቶች እየተባሉ የሚነሱ ነገሮች አሉ። ታሪክን መሠረት አድርገን የምናወራው የሚያወዛግብ ጉዳይ አለ። ይሔ መቋጫ ማግኘት አለበት። ከሀገራዊ ምክክሩ ተነስቶ መፍትሔ ማግኘት ይቻላል። በእንደዚህ ዓይነት ሂደት ውስጥ ችግሮች መኖራቸው አይቀርም።

የኢትዮጵያ የሀገርነት ምስረታ ከሌላው ዓለም የተለየ አይደለም። በኃይል አቢሲኒያ ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ ያልነበሩ ሕዝቦችን ለማካተት እና ወደ አንድ በማምጣት አገር ተመሥርቷል። በዚህ ጊዜ ውስጥ የተፈጠሩ ክስተቶች የሚታዩት እንዴት ነው? የሚለው ያነጋግረናል። እነዚህ የነበሩ የታሪክ ቁርሾዎች የሚያልቁት በንግግር ነው። እስከ አሁን ያንን አላደረግንም።

ሁለት ነገር ላይ ማተኮር እፈልጋለሁ። አንደኛው በትክክል የሆነው ምንድን ነው? በግልፅ መታወቅ አለበት። ለምሳሌ ምኒልክ ከሸዋ ተነስቶ ወደ ደቡብ ሲዘምት ያኔ በትክክል የተፈጠረው ምንድን ነው? በግልፅ አይታወቅም። ማንም ብድግ ብሎ እንደፈለገ ይከሳል። የተለያየ አረዳድ አለ። ሳይንሱ አንድ ነገር ሲል ታሪክ ደግሞ ሌላ ነገር ይላል።

የተፈጠረው ምንድን ነው? ተብሎ እውነት መውጣት አለበት። እውነት ሲወጣ ደግሞ በደል ከተፈፀመ በእርቅ እና በንግግር ያልቃል። ይህንን ከማድረግ አኳያ አሁንም እጥረቶች አሉ። አሁንም ይህ አልተፈታም። ሌላው በአብዛኛው በኢትዮጵያ ግጭቶችን የመፍታት ባሕል አለመኖሩ ነው። የተወሰኑ ጥሪቶች አሉ። ነገር ግን ተፅዕኖ ፈጥሮ ከላይ የሚታየው ግጭትን የመፍቻ መንገድ ኃይል ነው። የኃይል ባሕል የገነነ ነው። ከሰላም ባሕል ይልቅ የሚጎላው የግጭት ባሕል ነው። ይህኛው ሌላው ችግር ነው።

ከኢኮኖሚ አንፃርም እንየው ከተባለ የሰላም ሳይንስ ላይ የደህንነት ልማት የሚባል ፅንሰ ሃሳብ አለ። ድህነት በስፋት ካለ ወደ ግጭት የመግባት ዕድሉ ሰፊ ነው። ግጭት ደግሞ መልሶ ወደ ድህነት ያመራል። በዚህ አዙሪት ውስጥ መውደቅ ያጋጥማል። ኢትዮጵያ ውስጥ የሥራ አጥነት እየጨመረ መሄድ እና ድህነቱም ግጭት ይፈጥራል። ሥራ አጥ ሁሉ ድንጋይ ወርዋሪ ነው ማለት አይደለም። ነገር ግን ሥራ አጥነት ለድንጋይ ወርዋሪነት ተጋላጭነትን ያመጣል። ኦሮሚያ ላይ የሸኔ ታጣቂ ሆኖ የምናየው በየቦታው መኪና እያስቆመ የሚዘርፈው ከዩኒቨርሲቲ ዲግሪ ይዞ ወጥቶ ሥራ ያጣው ለእንደዚህ ዓይነት ፕሮፖጋንዳ የተጋለጠ ነው።

ሰላም ከሌለ ድህነት ይባባሳል፤ ድህነት ካለ ደግሞ ወደ ግጭት የመግባት እድላችን ይባባሳል። ይሔም ችግር መኖሩ መዋቅራዊ ችግር ነው። ይህንንም መሻገር አለብን። የተሻለ ኢኮኖሚ ያላቸው የተሻለ ሰላም ይኖራቸዋል መባሉ ትክክል ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አካታች ሀገራዊ ምክክሩ በአጠቃላይ ለሀገር ሰላም የሚበረክተው አስተዋፅዖን በተመለከተ ምን ይላሉ?**

**ዶክተር ቃለወንጌል፤-** ምክክር እንደንግግር አይደለም። ምክክር ከልብ ጋር ይያያዛል። ከልብ ታምኖበት ከአንደበት የሚወጣ ነው። አንዱ ሌላውን ለመረዳት የሚፈቅድበት ልባዊ ልውውጥ ነው። አሸናፊና ተሸናፊ እንዲኖር ወይም አንዱ ሌላው ላይ ሃሳቡን ለመጫን አይደለም። ከተራ ንግግር ይለያል። አንዱ ጥያቄው በዚህ መንገድ መካሔዱ ነው። ከልብ በመነጨ በውስጥ ፍላጎት ይካሄዳል ወይ? የሚል ጥያቄ አለኝ።

አንዱ ፅንፍ ይዞ የራሱን ሃሳብ ለመጫን በሚደረግ ጥረት ሊሳካ አይችልም። ምክክር ማለት አሸናፊና ተሸናፊ የሌለበት የጋራ ጥቅም ነው። ለአንተ ማንነት እውቅና እሰጣለሁ፤ ለእኔ ማንነት እውቅና ትሰጣለህ የምንባባልበት ነው። ያንተ ችግር የኔም ችግር ነው። ችግሩ የጋራችን ነው ብለን መነሳት አለብን።

አካታች የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ምክክሩ የሚመራበትን መመሪያ ማስቀመጥ አለበት። ውይይቱ መካሄድ ያለበት በዚህ መንፈስ ነው ማለት አለበት። አንዱ ፋይዳው በዚህ መንፈስ የሚካሄድ ከሆነ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ችግሮች በምሑራኑ አካባቢ የሚታዩ ከምሑራኑ አልፈው ሕዝቡ ላይ የሚታዩ ችግሮች መቋጫ እንዲያገኙ ያስችላል። እዚህ ላይ አካታች ሀገራዊ ምክክሩ ጥቅም ኢትዮጵያ ውስጥ ለዓመታት ሲንከባለል የነበረውን የታሪክና ሌሎችም ጉዳዮች መስመር ማስያዝ ያስችላል። ሕገመንግሥቱ ላይ ያሉ የሚነሱ ጥያቄዎች ላይ መፍትሔ የምናመጣበትን ዕድል ይሰጠናል።

ይህን በማድረግ ሀገረ መንግሥቱን ማጠናከር ይቻላል። የሀገረ መንግሥቱ መገለጫ ባንዲራችን ላይ ያለውን ጥያቄም ለመመለስ ይቻላል። ሁለት ስኬት ይኖረዋል። አንደኛ ሀገረ መንግሥቱ ላይ የሚነሱ ጉዳዮች ላይ መፍትሔ በመስጠት ሀገረ መንግሥቱን ያጠናክረዋል። ቀጣይነቱን ያረጋግጣል። ብሔራዊ መዝሙር ባንዲራ ላይ መፍትሔ ስለሚመጣ በሂደቱ አገረ መንግሥቱ የሚጠናከርበትን ዕድል ይፈቅዳል።

ሌላው ብሔረ መንግሥቱንም ያጠናክራል። ማለትም በሕዝቦች መካከል ወንድማማችነት የሚጠናከርበት ይሆናል። አንድ ኢትዮጵያዊ ያለምንም ችግር ሌላ ቦታ ሔዶ የሚሠራበትን ሁኔታ ይፈጥራል። በአጠቃላይ ያለምንም ችግር የመንግስት ግንባታ ሂደቱን በማጠናከር በተመሳሳይ መልኩ የአንድነት ስሜታችንን ለማሳደግ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል።

ንግግር ትልቅ የሰላም ግንባታ መሣሪያ ነው። ሰላምን የምንገነባበት ትልቅ ስትራቴጂ ነው። ያሉ የፖለቲካ ውዝግቦች ወደ ኃይል እርምጃ እንዳይሔዱ አስቀድሞ መከላከያ ሲሆን፤ ይህ ባህል እንዲሆን ትልቅ አጋጣሚ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም እናመሰግናለን።**

**ዶክተር ቃለወንጌል፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ዓለም አቀፍ

## ለኩባ ስትሰልል ነበር የተባለችው አሜሪካዊቷ ሰላይ ከ20 ዓመታት እስር በኋላ ተለቀቀች

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት ለኩባ ስትሰልል ነበር በሚል በቁጥጥር ስር የዋለችውና እውቅ እና ተጽእኖ ፈጣሪ ከነበሩ ሰላዮች መካከል አንዷ የነበረችው አና ሞንቴስ ከ20 ዓመታት እስር በኋላ ተለቀቀች።

አሁን ላይ 65 ዓመት የደፈነችው አሜሪካዊቷ ሰላይ በአሜሪካ የመከላከያ ደኅንነት ኤጀንሲ እየሰራች ለሁለት አስርት ዓመታት የአሜሪካ ባላንጣ ለሆነችው ኩባ ስትሰልል ነበር።

የአሜሪካ ባለስልጣናት እአአ 2001 ላይ አና ሞንቴስ በቁጥጥር ሥር ስትውል አሜሪካ በኩባ ስለነበራት እንቅስቃሴ ሙሉ መረጃ አሳልፋ ሰጥታለች ብለው ነበር።

አንድ ከፍተኛ ባለስልጣን በአሜሪካ ከተያዙ "ከፍተኛ ጉዳት ካደረሱ ሰላዮች" መካከል ሞንቴስ አንዷ ናት ብለው ነበር በወቅቱ።

እአአ 2012 ላይ በፕሬዚዳንት ጆርጅ ደብሊው ቡሽ አስተዳደር ስር ከፍተኛ የደኅንነት ኃላፊ የነበሩት ማይክል ባን ክሊቭ ለኮንግረስ ሲናገሩ፤ በኩባ ስለምናውቀው እና በኩባ እንዴት እንደምንሰራ ሙሉ በሙሉ አጋልጣለች ብለዋል።

"ኩባውያኑ ስለእርሱ የምናውቀውን ነገር በሙሉ ያውቁ ነበር። ስለዚህ ይህን ይጠቀሙበታል።" ሲሉም ተናግረው ነበር።

ሞንቴስ በቁጥጥር ሥር ስትውል በኩባ የሚገኙ አራት የአሜሪካ ሰላዮችን ማንነት እና ከፍተኛ ሚኒስትራዊ መረጃዎችን አቀብላለች ተብላ ተከሳ ነበር።

በእነዚህ ወንጀሎች የ25 ዓመት እስር የፈረዱባት ዳኛ፣ ሞንቴስ "መላ አገሪቱን አደጋ ላይ ጥላለች" ብለው ነበር።

ሞንቴስ ለኩባ ለመስራት የተስማማችው በጥቅማ ጥቅም ተደልላ ሳይሆን በምትከተለው ርዮተዓለም ነው ተብሎ ነበር። ሰላይዋ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሬጋን አስተዳደር በላቲን አሜሪካ ያለውን እንቅስቃሴ መቃወሟ ለኩባ የደኅንነት ተቋም እንድትሰራ ምክንያት ከሆኑት አንዱ ነው።



አና ሞንቴስ የአሜሪካ መከላከያ ደኅንነት ከፍተኛ ተንታኝ ሆና እየሰራች ከኩባ ሰላዮች ጋር ዋሽንግተን ዲሲ በሚገኙ ምግብ ቤቶች እየተገናኘች ጥብቅ ሚስጢር የያዙ መረጃዎችን ታቀብል ነበር። ከኩባ ደግሞ ትዕዛዝ የምትቀበለው በአጭር ሞገድ ራዲዮ ነበር ተብሏል።

በመጨረሻም የአሜሪካ የደኅንነት ተቋም በደረሰው ጥቆማ መሠረት ሞንቴስ እአአ 2001 ላይ በቁጥጥር ሥር ውላለች።

ሞንቴስ አሁን ላይ ከአሜሪካ እስር ቤት ብትለቀቅም ለቀጣይ አምስት ዓመታት በደኅንነት አባላት ጥብቅ ክትትል ስር የምትቆይ ይሆናል።

የኢንተርኔት አጠቃቀሟ ክትትል ይደረግበታል፤ የውጭ አገር ሰዎችን ከማግኘቷ በፊት ፍቃድ ያስፈልጋታል። እንዲሁም ለአሜሪካ መንግሥት መስራት አትችልም።

ከ20 ዓመታት በፊት ሞንቴስን በቁጥጥር ሥር ያዋለው የፌደራል ቢሮ መርማሪ (ኤፍቢአይ) ባልደረባ ሰላይዋ ከአሁን በኋላ ከኩባ ጋር የመስራቷ አጋጣሚ ያበቃለት ነው ብሏል።

ፒት ላፕ ለሲቢኤስ ሲናገር፡ "ያ የሕይወቷ አካል አብቅቷል። ለእነርሱ ያደረገችው ነገር አብቅቶለታል" ብሏል።

## የገና በዓል ዕለት ለምን ተለያየ?

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- አውሮፓ እና አሜሪካንን ጨምሮ በርካታ የዓለም አገራት ክርስቲያኖች የገና ወይም የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓልን የሚያከብሩት ከዘመን መለወጫቸው አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ ታኅሣሥ አጋማሽ ላይ ነው።

ከአፍሪካ ኢትዮጵያ፣ ኤርትራ እና ግብፅ እንዲሁም የተወሰኑ ሌሎች የአውሮፓ አገራት ግን የገና በዓልን ታኅሣሥ 29 ያከብራሉ።

እነዚህን አገራት የሚያመሳስላቸው አንድ ጉዳይ በርካታ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት እምነት ተከታይ ስላላቸው ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ የሚከተሉት የዘመን አቆጣጠር ነው።

የኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እምነት ተከታዮች ገናን በየዓመቱ ታኅሣሥ 29 በአራት ዓመት አንድ ጊዜ ደግሞ ታኅሣሥ 28 ያከብሩታል።

የገናን በዓል ቀደም ብለው የሚያከብሩት አብዛኞቹ ምዕራባውያን አገራት እና ሌሎችም የግሪጎሪን የቀን አቆጣጠር ቀመርን የሚከተሉ ናቸው። የቀን አቆጣጠሩ የተፈጠረው በ1582 በሊቀ-ጳጳስ ግሪጎሪ ነበር።

እንዲሁም አብዛኞቹ የቀድሞዋ ሶቪየት ኅብረት አካል የነበሩ አገራት፣ የምሥራቅ አውሮፓ እንዲሁም የመካከለኛው ምሥራቅ አገራት ደግሞ በጁሊየስ ቄሳር የተፈጠረውን የጁሊያን የዘመን አቆጣጠር የሚከተሉ ናቸው።

በተጨማሪም በርካታ አገራት በይፋ የሚገለገሉበትን የዘመን አቆጣጠር የግሪጎሪያውያኑን አድርገው፣ ለአገር አቀፍ በዓላት ግን የጁሊያንን የዘመን ቀመርን የሚጠቀሙም አሉ።

ናሽናል ጂኦግራፊክ እንደሚለው በዓለም ላይ ካሉ የክርስትና እምነት ተከታዮች መካከል ከ12 በመቶው የሚልቁት ክርስቲያኖች የልደት በዓልን ከቀሪው ዓለም በተለየ ቀን ያከብራሉ።

በግሪክ፣ በቆጵሮስ እና በሩሜኒያ የሚገኙ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት በዓል ያከበሩት በግሪጎሪያን የዘመን አቆጣጠር ከሁለት ሳምንት በፊት ነው።

በተጨማሪም ከሌሎቹ በተለየ ሁኔታ አርሜኒያ ገናን በራሷ የቀን አቆጣጠር በተለየ ቀን ነው የምታከብረው። አርሜኒያ ገናን ታኅሣሥ 28 (በአራት ዓመት አንዴ ደግሞ ታኅሣሥ 27) ታከብራለች።

ኢትዮጵያ የራሷ የዘመን አቆጣጠር ያላት አገር ናት። ይህ የጊዜ ቀመር ከኮፕቲክ ኦርቶዶክስ እምነት ቀን አቆጣጠር ጋር ተመሳሳይነት አለው።

ልክ እንደ ኢትዮጵያ ሁሉ የኮፕቲክ ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ገናን ከምዕራቡ ዓለም በሁለት ሳምንታት ያህል ዘግይተው ያከብራሉ። የጥምቀት እና የፋሲካ በዓልን የሚያከብሩበት ቀንም ከምዕራቡ ዓለም ጋር በተመሳሳይ ልዩነት ያለው ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የኦርቶዶክስ፣ የካቶሊክ፣ የኢቫንጀሊካል፣ እንዲሁም የጴንጤኮስታል እምነት ተከታዮች እና ሌሎች የክርስትና እምነት ተከታዮች የልደት በዓልን የሚያከብሩት በአንድ ቀን ነው።

ኤርትራ በበኩሏ ብሔራዊው የዘመን አቆጣጠሯ የግሪጎሪያውያኑን ብታደርግም የክርስትና እምነት ተከታዮች ግን የኦርቶዶክስ የዘመን አቆጣጠርን ይከተላሉ።

በዓለማችን ያሉ የኦርቶዶክስ እምነትም ሆነ የሌሎች ክርስትና ሃይማኖቶች ተከታዮች ገና ከመድረሱ በፊት ያሉትን ቀናት በፆም እንዲሁም በፀሎት ያስቧቸዋል።

የገና አከባበር ከአገር አገር የተለያየ ቅርፅ አለው። ለምሳሌ ሩሲያ ውስጥ ያሉ ክርስቲያኖች ከአዲስ ዓመት መባቻ እስከ ገና ዕለት ያሉትን 7 ቀናት፣ በቀን 12 የተለያዩ ዓይነት ምግቦችን በመመገብ ያሳልፋሉ። ዓላማው ደግሞ 12ቱን ሐዋሪያት ማሰብ ነው።

ዩክሬን ውስጥ ደግሞ የበዓሉ አክባሪዎች ከቤት ቤት በመዘዋወር ዝማሬ በማሰማት ነው ቀኑን የሚያሳልፉት።

ቤላሩሲያውያን ደግሞ ለዕለቱ ቂጣ እና ዓሣ ያዘጋጃሉ። በሞንቴንግሮ ውስጡ ሳንቲም ያለበት ድፎ ዳቦ ይደፋል፤ ዳቦው ሲቆረስም የሚገኘው ሳንቲም መልካም ዕድል ይዞ እንደሚመጣ ያስባሉ።

በሰርቢያ ውስጥ ገና የሚዘከረው ልክ እንደ ቡሄ ከጫካ ዛፍ ተቆርጦ ከተሰበሰበ በኋላ እሱን በማቃጠል በዙሪያው ተሰብስቦ እራት በመብላት ነው። ጆርጂያውያን ደግሞ ወደ አውራ ጎዳናዎች በመውጣት የኢየሱስ ክርስቶስን ልደት ይዘክራሉ።

በኢትዮጵያም ቢሆን የበዓሉ መሠረት አንድ ቢሆንም አከባበሩ ከቦታ ቦታ ይለያያል። የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ተከታዮች ከገና በፊት የጾም የሳምንታትን የሚያሳልፉ ሲሆን በበዓሉ ዕለት ጾሙ ይፈታል።

ነገር ግን አብዛኛው የክርስትና እምነት ተከታይ ምዕመን በዓሉን ወደ ቤተ እምነቶች በመሄድ፤ የጸሎት ሥነ ሥርዓቶችን በመታደምና በቤት ውስጥ በጋራ ማዕድ በመቁረስ ያከብረዋል።

**ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም**

# የልዩ ፍላጎት እና አካቶ ትምህርት በኢትዮጵያ

አካታች ፍትሃዊ እና ጥራት ያለው ትምህርት ማረጋገጥ እንዲሁም የዕድሜ ልክ የመማር ዕድሎች ለሁሉም ማሳደግ አንዱ የዘላቂ ልማት ግብ እንደሆነ ይገለጻል። የዓለም የጤና ድርጅት በፈረንጆቹ 2011 ባጠናው ጥናት መሠረት 15 በመቶ የሚሆነው የዓለም ሕዝብ አካል ጉዳተኛ እንደሚሆን ይገመታል።ከዚህ ጋር በተያያዘም በዓለማችን ሁለት መቶ 58 ሚሊዮን የሚጠጉ ህጻናት፣ወጣቶች እና ጎልማሶች የልዩ ፍላጎት የትምህርት ዕድል እንደማያገኙ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የትምህርት፣የሳይንስ እና የባህል ተቋም በግሎባል ኤዲኮሽን ሞኒተሪንግ ሪፖርቱ (GEMR) ላይ በ2020 ይፋ አድርጓል።

በኢትዮጵያ ልዩ ትምህርት እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1917 አካባቢ በሚስዮናውያን እንደተጀመረ መረጃዎች ያመለክታሉ።አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በጉዳት ዓይነታቸው በመለየት በልዩ ትምህርት ቤቶች ይማሩ የነበሩ ሲሆን፤እስከ 1998 ዓ.ም በሀገሪቱ ውስጥ 17 የሚደርሱ ልዩ ትምህርት ቤቶች እንደነበሩም ይገልጻል። ትምህርት ሚኒስቴር በ1998 ዓ.ም የልዩ ፍላጎት ትምህርት ስትራቴጂ በማዘጋጀት ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ ከመሥራት ባለፈ በ2004 ዓ.ም የአካቶ ትምህርት ስትራቴጂ ቀይሶ አካቶ ትምህርትን እንዲስፋፋ በርካታ ሥራችን ሠርቷል።

### አካታች የትምህርት ሥርዓት ለመገንባት የተቀመጡ የሕግ ማዕቀፎች

የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 41(5) ለአካል ጉዳተኞች እና አቅመ ደካሞች አቅም በፈቀደ መጠን ድጋፍ እንዲደረግ ይገልጻል። በአንቀፅ 9(4) ደግሞ ኢትዮጵያ ተቀብላ ያጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሕገ መንግስቱ አካል እንደሆኑም ያትታል። ለአካቶ ትምህርት ከፍተኛ አጽንኦት የሰጠውና ሀገራት አካታች የትምህርት ሥርዓት እንዲተገብሩ የሚያስገድደው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ2006 ያወጣው ስት የአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ



ኮንቬንሽንም ይጠቀሳል።

የአካቶ ትምህርት የአፈጻጸም ስልቶች በኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ አካታች ትምህርትን ለመተግበር የሚከተሉትን ስትራቴጂዎችን ስትተገብር ቆይታለች፡-

- በአካቶ ትምህርትና አካል ጉዳተኝነት ዙሪያ የማህበረሰብ ግንዛቤ ማሳደግ፣
- የትምህርት አመራርና አስተዳደሩን ስልጠና በመስጠት አቅም ማጎልበት፣
- የአካቶ ትምህርት የድጋፍ መስጫ ማዕከላትን ማቋቋም፣
- የመለያና ዳሰሳ መሳሪያዎችን ማዘጋጀትና ሥራ ላይ ማዋል፣
- የመረጃ አሰባሰብ እና ሥርዓት ማጠናከር እንዲሁም ለፖሊሲ ውሳኔ ማዘጋጀት፣
- ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር መሥራት እና
- የተጠናከረ ክትትልና ድጋፍ ማካሄድ ናቸው።

### የተመዘገቡ ውጤቶች

- ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ብዛትና የትምህርት ተሳትፎ ጨምሯል።
- በልዩ ፍላጎት ትምህርት ሙያ የሚያሰለጥኑ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቁጥር ጨምሯል።
- ከአንድ ሺ በላይ የአካቶ ትምህርት የድጋፍ መስጫ ማዕከላት ተቋቁመዋል።
- በአካል ጉዳትና አካቶ ትምህርት ዙሪያ የትምህርት ማሕበረሰቡ ግንዛቤ አድጓል።

### ተግዳሮቶች

- የትምህርት አመራሩ ለአካቶ ትምህርት የሚሰው ትኩረት አናሳ መሆን፣
- ወጥነት የጎደለው የመረጃ አሰባሰብ እና አስተዳደር መኖር፣
- የትምህርት ቤት አካባቢዎችና አገልግሎቶች ተደራሽ አለመሆን፣
- የልዩ ፍላጎት የድጋፍ ሰጪ መገልገያዎች በሀገር ውስጥ በበቂ ሁኔታ አለመገኘት
- በልዩ ፍላጎት ትምህርት የሰለጠኑ ባለሙያዎች ፍልሰት፣
- የቀድሞ ሥርዓተ ትምህርት ለልዩ ፍላጎት ተገቢውን ትኩረት ያለመስጠት፣
- መደበኛ መምህራን ለአካታች ክፍል በሚመጥን መልኩ አለመሰልጠን ከሚጠቀሱት ጥቂቶቹ ናቸው።

### የወደፊት አቅጣጫ

- በአካቶ ትምህርት ዙሪያ የሕብረተሰብ ተሳትፎን ማጠናከር፣
- የልዩ ፍላጎት እና አካቶ ትምህርት ባለሙያዎች እና ተዘዋዋሪ መምህራን መዋቅር ማስተካከል፣
- አካቶ ትምህርት ትግበራን የመደበኛ ሥራ አካል (ሜይንስትሪም) በማድረግ በቡድን መንፈስ፣በኃላፊነትና በተጠያቂነት መምራት፣
- ከአጋር ድርጅት ጋር ግንኙነትን ማጠናከር፣
- በሀገሪቱ ያሉ የጉድኝት ማዕከላትን በሙሉ ወደ አካቶ ትምህርት የድጋፍ መስጫ ማዕከላት ማሸጋገር፣
- ለልዩ ፍላጎት እና አካቶ ትምህርት ተግባራት ማከናወኛ በጀት በቋሚነት መመደብ፣
- ለሁሉም ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ህጻናት፣ የልየታና የድጋፍ አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት።

በአጠቃላይ በ2017ዓ.ም የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ተሳትፎ ለማሳደግ የታቀደ ሲሆን፤ በዚህም በ2012 ዓ.ም በቅድመ አንደኛ ደረጃ 0ነጥብ90 በመቶ የነበረውን በ2017 ዓ.ም 11 ነጥብ 10 በመቶ ፤በአንደኛ ደረጃ በ2012 ዓ.ም 11 ነጥብ 10 በመቶ የነበረውን ወደ 25 በመቶ ለማሳደግ እና በሁለተኛ ደረጃ በ2012 ዓ.ም 2 ነጥብ 80 በመቶ የነበረውን በ2017 ዓ.ም ወደ 11 ነጥብ40 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል።

# ስፖርት



## ፌዴሬሽኑ ከፍቅር ያሸንፋል በጎ አድራጎት ማኅበር ጋር ለመሥራት ተስማማ

ቦጋለ አበበ

በቀደሙት ኦሊምፒኮች ከአትሌቲክሱ ቀጥሎ ሀገሪቱ ትወከልበት እንደነበረ የሚነገርለትን ብስክሌት ወደ ቀድሞ ስምና ክብሩ ለመመለስ ከሚታትሩ የሀገሪቱ ክፍሎች አዲስ አበባ ይጠቀሳል። ከሜልቦርን እስከ ባርሴሎና ኦሊምፒክ ኢትዮጵያ በብስክሌት የነበራት ተሳትፎ እስከ ቅርብ ጊዜ ጠፍቶ ቆይቷል። ሆኖም በአውሮፓ በተለያዩ ሀገሮች አዘውትሮ በሚካሄዱ የብስክሌት ውድድሮች ላይ በወንዶችም ሆነ በሴቶች ተስፋ የሚሰጡ ተወዳዳሪዎች ታይተዋል። በዚህም ሪዮ ኦሊምፒክ ላይ በወንድ፣ ቶኪዮ ላይ ደግሞ በሴት ብስክሌተኞች ወደ ተሳትፎ መመለስ ተችሏል።

የአዲስ አበባ ብስክሌት ፌዴሬሽን ስፖርቱን ከፍ ወዳለ ደረጃ ለማሸጋገር ተስፋ የሚጣልባቸው እንቅስቃሴዎች እያደረገ የሚገኝ ሲሆን በከተማ አስተዳደር ደረጃም የተለያዩ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለከተማው ብስክሌት ስፖርት ውጤታማነት የተለያዩ ስትራቴጂካዊ ዕቅዶች ነድፎ በመተግበር ላይ ይገኛል። ከዕቅዶቹ መካከል ፌዴሬሽኑ ጠንካራ የፋይናንስ አቅም እንዲኖረው የሚደረገው የስፖንሰርሽፕ ስምምነቶች ቀዳሚውን ሥፍራ የሚይዝ ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ከመደበኛ የውድድር መርሐ ግብሮች ጎን ለጎን የታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክት ላይ የሚደረገው እንቅስቃሴ ነው።

ይሁን እንጂ የአዲስ አበባ ብስክሌት ፌዴሬሽን ብስክሌቱን በከፍተኛ በጀት እያንቀሳቀሱ ከሚገኙት የትግራይና የአማራ ክልሎች አንፃር ይህ ነው የሚባል ጠንካራ የበጀት ድጋፍ የለውም። በዚህ ረገድ




ስምምነቱ ለከተማዋ የብስክሌት ስፖርትና ለታዳጊ ብስክሌተኞች ወሳኝ በመሆኑ ተጠቁሟል፣

የከተማውን የብስክሌት ስፖርትና ውድድር በላቀ ደረጃ ለማሳደግ የአጋር ባለድርሻ አካላት ሚና የላቀ መሆኑ የተጠቆመ ሲሆን፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ብስክሌት ፌዴሬሽን የከተማዋን የብስክሌት ውድድር ደረጃውን ለማሳደግ ከፍቅር ያሸንፋል በጎ አድራጎት ማኅበር ጋር በጋራ ለመሥራት የሚያስችል የሁለትዮሽ የፊርማ ስምምነት ሰሞኑን አካሂዷል።

በፕሮግራሙ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ብስክሌት ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ረዘነ በየነ የከተማዋን የብስክሌት ስፖርት ወደ ቀድሞ ክብሩና ተወዳጅነት ለመመለስ ፌዴሬሽኑ በበጀት ዓመቱ በርካታ ዕቅዶችን አቅዶ ወደ ተግባር መግባቱን ተናግረዋል።

ፕሬዚዳንቱ አያይዘውም ከፍቅር ያሸንፋል በጎ አድራጎት ማኅበር ጋር የተደረገው ስምምነት ለከተማዋ የብስክሌት ስፖርትና ለታዳጊ ብስክሌተኞች ወሳኝ በመሆኑ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ አብራርተዋል።

የፍቅር ያሸንፋል የበጎ አድራጎት ማኅበር ፕሬዚዳንት አቶ ሚስባህ ከድር በበኩላቸው፣ በሀገራችን ብሎም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳጅ የሆነውን የብስክሌት ስፖርት ውድድር እንደ አዲስ አበባ ከተማ ውጤት እንዲመጣና ተተኪዎች በስፖርቱ እንዲሳቡ ከፌዴሬሽኑ ጋር በጋራ ለመሥራት የስምምነት ፊርማው ወሳኝ መሆኑን ጠቁመዋል።

የጋራ የስምምነት ሰነዱ መነሻ ሀሳቦች ይዘትን የአዲስ አበባ ብስክሌት ፌዴሬሽን የጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ ተረፈ አቅርበዋል ።

በፕሮግራሙ የተገኙት የአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የስፖርት ማኅበራት ማደራጃና ውድድር ዳይሬክተር አቶ አያሌው ታደለ በበኩላቸው፣ ስፖርት ሕዝባዊ መሠረትን ይዞ እንዲስፋፋ ከመንግሥት ድጎማ መላቀቅና የራሱን ገቢ ማስገኛ ዕቅዶች መንደፍ ተገቢ በመሆኑ በአዲስ አበባ ብስክሌት ፌዴሬሽንና በፍቅር ያሸንፋል በጎ አድራጎት ማኅበር መካከል የተደረገው ስምምነት ለሌሎች ፌዴሬሽኖችም አርአያነት እንዳለው አስረድተዋል።

የሁለትዮሽ የሥራ ውል ስምምነቱ በአዲስ አበባ ብስክሌት ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት በአቶ ረዘነ በየነና በፍቅር ያሸንፋል በጎ አድራጎት ማኅበር ፕሬዚዳንት በአቶ ሚስባህ ከድር መካከል ተፈርሟል።


## የጨረታ ሽያጭ ማስታወቂያ ቁጥር 11/2015

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን የሞያሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በቅ/ጽ/ቤቱ እና በስሩ የሚገኙ መ/ጣቢዎች ተይዘው እና ተወርሰው የሚገኙ አልባሳት የሞተርሳይክል እና የተሽከሪካሪ መለዋወጫዎች ልዩ ልዩ እቃዎች፤ ኮስሞትክስ ፤ ኤሌክትሮኒክስ እቃዎች፤ ሞባይል ቀፎዎች በግልጽ እና በሃራጅ ጨረታ ተጫራቾችን አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል። በዚህ መሠረት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የጨረታ ቅድመ ሁኔታዎች እና መስፈርቶች ሟሟላት የሚችሉ ተጫራቾች መወዳደር የሚትችሉ መሆኑን እንገልጻለን።

1. ለጨረታ የቀረቡት ዕቃዎች ላይ ለመወዳደር የሚፈልግ ማንኛውም ተጫራች በጨረታ ከሚሸጠው ዕቃዎች ጋር ተዛማችነት ያለው የታደሰ የንግድ ፈቃድ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሰርትፍኬት የዘመኑን ግብር የከፈለ ስለመሆኑ ክሊራንስ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ እንቅስቃሴያቸውን ያሳወቁበት በቅርብ ጊዜ የተሰጣቸው የምስክር ወረቀት እና መለያ ቁጥሩን ከመጫረቻ ሰነዱ ጋር አያይዞ በኤንቨሎፕ በማሸግ ለጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል።
2. ተጫራቾች የግልጽ ጨረታ ሰነድ ዘውትር በስራ ሰዓት ከሰኞ እስከ አርብ ከ2፡00- 12፡00 ሰዓት እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 2፡00-6፡00 ሰዓት የማይመለስ ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር) (መክፈል በጽ/ቤታችን የእለት ገቢ ገንዘብ ሰብሳቢ ቢሮ ቁ.ር 16 በመገኘት ይህ የጨረታ ማስታወቂያ አየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ እስከ መዝጊያው ቀን ድረስ የጨረታ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ።
3. በግልፅ ጨረታው ለመሳተፍ ተጫራቾች ለሚወዳደሩባቸው ዕቃዎች የሰጡትን ዋጋ አምስት በመቶ (5%) ዋስትና (CPO) እንዲሁም በሃራጅ ጨረታ ለመሳተፍ 100000 ብር(አንድ መቶ ሺህ ብር) የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ሲ.ፒ.ኦ በጉምሩክ ኮሚሽን በሞያሌ ቅርንጫፍ ስም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማስያዝ ይኖርባቸዋል።
4. ጨረታው ሚካሄደው በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት ሲሆን ተጫራቾች (ህጋዊ ወክሎቻቸው) ባሉበት ወይም ታዛቢ ፊት ይከፈታል።
5. ተጫራቾች ማስታወቂያ በጋዜጣው ከታተመበት ቀን ጀምሮ የሚቆጠር እሰከ 7ተኛው ቀን ድረስ ለጨረታ የቀረቡ ዕቃዎች ናሙና በሞያሌ እና በሁሉም መ/ጣቢያ የሚገኙ መጋዝኖቻችን እየሄዱ መመልከት አለባቸው።
6. ጨረታው የሚካሄደው ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የሚቆጠር በ8ኛው ቀን ሲሆን ጨረታው ከጠዋቱ 3:45 (ሶስት ሰዓት ከአርባ አምስት ደቅቃ) ተዝግቶ 4፡00 (አራት ሰዓት) ላይ ይከፈታል።
7. ከላይ በተራ.ቁጥር 6 በተገለጸው ጋዜጣው ከታተመበት ቀን ጀሚሮ የምቆጠር 8ኛው ቀን የስራ ቀን ሳይሆን ስቀር ጨረታው መዝጊያ እና መከፈቻ ቀን በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ይሆናል።
8. ለጨረታው አሸናፊ ተጫራቾች ለጨረታው ያስያዙት ሲ.ፒ.ኦ (C.P.O) ከሚከፍሉት ዋጋ ጋር የሚታሰብላቸው ሲሆን ለተሸናፍ ተጫራቾች ደግሞ የጨረታውን ውጤት ከተገለጸ በ 3 ቀናት ውሰጥ ተመላሽ ይደረግላቸዋል።
9. አሸናፊ ተጫራች ማሸነፋቸውን በደብዳቤ ወይም በማስታወቂያ ከተገለጸላቸው ቀን ጀሚሮ በ 5 ቀናት ውስጥ ያሸነፉበትን ገንዘብ ገቢ በማድረግ ዕቃውን መረከብ ይኖርባቸዋል።
10. ከላይ በተራ ቁጥር 9 በተገለጹት ቀናት ውስጥ ክፍያውን ገቢ ያላደረገ ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዙት C.O.P ለመ/ቤቱ ገቢ ሆኖ ዕቃው በድጋሚ ለሽያጭ ይቀርባል።
11. ጽ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

**ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር 046 444 0383/ 046 444 0375/046 444 1564 ደውሉ መጠየቅ ይችላሉ።**

## በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን የሞያሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት